# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## በደቡብ ምዕራብ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና


በ

አንሻ መሃመድ



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በደቡብ ምዕራብ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ
# የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር

## ትምህርት ክፍል

ለ በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

አንሻ መሃመድ

አማካሪ

አቶ ደረጀ ገብሬ

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር

## ትምህርት ክፍል

እኛ ከዚህ በታች የፈረምነው በደቡብ ምዕራብ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና በሚል ርዕስ፣ በ አንሻ መሃመድተዘጋጅቶ አማርኛን በማስተማር ለአርት ማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሚያነት የቀረበው ይህ ጥናት ከዩኒቨርሲቲው ደንብ ጋር የሚጣጣም እና የአዲስነትና ጥራትደረጃን የሚያሟላ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

### የፈተና ቦርድ አባላት

የቦርድ ሰብሳቢ …………………………… ፊርማና ቀን …………………..

የውጭ ፈታኝ ……………………………. ፊርማና ቀን …………………..

የውስጥ ፈታኝ …………………………… ፊርማና ቀን …………………..

አማካሪ…………………………………..ፊርማና ቀን…………………..

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የአሰራር አቅጣጫን በማመላከት፣ የጥናቱን ረቂቅ በማረም፣ ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠትና በማበረታት ጥናቱ የአሁኑን ቅርጽ እንዲይዝ ለረዱኝ፣ እንዲሁም በዚህ ወቅት እንዳደርስና እንዳቀርብ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ  ላቅ ያለ  ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም የጽህፈት ሥራው እንዲቀላጠፍልኝ ጊዜዋን መስዋት አድርጋ ላገዘችኝ እህቴ ሃያት አሊ ምስጋናዬ ይድረሳት፡፡በተጨማሪ ለዚህ ጥናት የሚያስፈልገኝን ወጪ ድጋፍ ላደረገልኝእና ላስተማረኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም ትምህርቴን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ድጋፍና ብርታት ለሆናችሁኝ ጓደኞቼ ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ እላለሁ፡፡

# ማውጫ


ምስጋና ........ I

ማውጫ ........ II

የሰንጠረዥ ማውጫ ........ VI

አጠቃሎ ........ VII

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 5

1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ........ 5

1.4. የጥናቱ ዓላማ ........ 6

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 6

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

የተዛማች ጽሁፍ ቅኝት ........ 8

2.1. የቃላት ምንነት ........ 8

2.2. የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ........ 9

2.3. የቃላት ትምህርት አመራራጥ ........ 10

2.3.1. የቃላት ድግግሞሽ መጠን ........ 11

2.3.2. የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ ........ 12

2.3.3. ተስተማሪነት (learnability) ........ 13

2.3.4. የፍቺ ሽፋን ........ 14

2.3.5. በቅርበት መገኘት ........ 15

2.4. የቃላት ትምህርት አደረጃጀት ........ 15

2.4.1. ቃላት በሚያወሱት ርዕስ ጉዳይ ማደራጀት (Topic) ........ 17

2.4.2. ቃላትን በፍቺ ተዛምዶ ማደራጀት (Meaning) ........ 17

2.4.3. ቃላትን በቅርጽ ተመሳስሎ ማደራጀት (Form) ........ 18

2.5.የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች ........ 19

2.5.1. ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ ........ 20

2.5.2. ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ ........ 22

2.5.2.1.ቃላትን በተመሳስሎና በተቃርኖ ፍቻቸው ማቅረብ ........ 23

2.5.2.2.የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት ........ 23

2.5.2.3.የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ........ 24

2.5.3.የቃላትን የእርባታና ምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ ........ 25

2.5.4.ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ ........ 26

2.5.5.ቃላትን ከቋንቋ ክህሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ ........ 29

2.5.6.የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ........ 30

2.5.7.የቃላት ትምህርትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ ........ 31

2.6. የቋንቋ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ ተጣጥሞሽ ........ 31

2.7. የቀደም ጥናቶች ቅኝት ........ 33

ምዕራፍ ሶስት ........................................................................................................ 37
የአጠናን ዘዴ.......................................................................................................... 37
3.1. የጥናቱ ንድፍ .................................................................................................. 37
3.2. ጥናቱ መረጃ ምንጮች ...................................................................................... 37
3.3. መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ .............................................................................. 38
3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..................................................................................... 38
ምዕራፍ አራት ....................................................................................................... 39
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ .......................................................................... 39
4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና.................................................................................... 39
4.1.1.የተተኳሪው መጽሀፍ አጭር ቅኝት...................................................................... 39
4.1.2.የቃላት ትምህርት አመራረጥን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና........................ 41
4.1.3.የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና.......................... 45
4.1.4.የቃላት ትምህረት አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ............................ 48
4.1.4.1.ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ............. 48
4.1.4.2.ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና....... 56
4.1.4.3. የቃላት እርባታና ምስረታን መሰረት ያደረጉ የቃላት ትምህርቶችን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና57
4.1.4.4. ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ................................................................................................. 61
4.1.4.5. ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና61
4.1.4.6. የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ............................................................................................................ 65

4.1.4.7. የቃላት ትምህርት መመሪያዎች አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና..... 66

4.1.5.የቃላት ትምህርትን በተመለከተ የመማሪያ መጽሃፉና የመርሃ ትምህርቱ ተጣጥሞሽ የሚያሳዩ መረጃዎች ትንተና ........ 68

4.2.የውጤት ማብራሪያ ........ 73

ምዕራፍ አምስት ........ 76

ማጠቃለያና አስተያየት ........ 76

5.1.ማጠቃለያ ........ 76

5.2. አስተያየት ........ 78

ዋቢ ጽሁፎች ........ 80

አባሪዎች ........ 85

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፡ በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ የቋንቋ ተግባራትና ቃላትን የሚመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ........ 40

ሰንጠረዥ 2፡ መጽሃፉ የተካተቱ የቃላት ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ........ 42

ሰንጠረዥ 3፡ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ... 46

ሰንጠረዥ 4፡ ቃላት በአውድ አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ......... 49

ሰንጠረዥ 5፡ ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ........ 56

ሰንጠረዥ 6፡ የቃላትን እርባታና ምስረታ ሥርዓትን መሰረት አድርገው የቀረቡ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ........ 58

ሰንጠረዥ 7፡ ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ ........ 62

ሰንጠረዥ 8፡ በመርሃ ትምህርቱ ተካተው በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ የቃላት ተግባራት ብዛት በቁጥር ........ 70

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ በ2015 ዓመተ ምህረት ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ታስቦ በተዘጋጀው አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው:: እንዲሁም መማሪያመፅሀፋ መርሀትምህርቱን መሰረት አድርጎ ስለሚዘጋጅ የቃላት ምህርቶችን መርጦና አደራጅቶ ለማቅረብ የራሱ አስተዋፅኦ ስለሚኖረው የሁለቱን ተጣጥሞሽ ይቃኛል:: ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ምሁራን ስለቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ አደረጀጀትና አቀራረብ ባነሷቸው ንድፍ ሀሳባዊ መርሆች ላይ በመመርኮዝ ጥናት ተካሄዷል:: በጥናቱም ተተኳሪው መፅሀፍና ለክፍል ደረጃውየተዘጋጀው መርሀትምህርት በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል:: ከነዚህ ሁለት ሰነዶች መረጃውን ለመሰብሰብ የሰነድ ፍተሻ በጥቅምላይ ውሏል:: ከሰነድ ምርመራው የተገኙ መረጃዎችን በቁጥርና በመቶኛ በማስቀመጥ በገለፃ ስልት ተተንትነዋል::ጥናቱ ቅይጥ የትንተና ዘዴን ተከትሎ የተሰራ በመሆኑ በዋናነት አይነታዊ ዘዴን በአጋዥነት ደግሞ መጠናዊ የአጠናን ዘዴን ለትንታኔ ተጠቅሟል::በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በመማሪያ መፅሀፋ ውስጥ ለቃላት ትምህርት ሰፊ ሽፋን ትኩረት ተሰጥቷል:: ይሁን እንጂ የቃላትመረጣው የተከናወነው የመስኩ ምሁራን ለዚህ ተግባር እንዲውሉ ከሰነዘሯቸው መስፈርቶች አንዱን ብቻ በመጠቀም ነው::እሱም አንድ ቃል ሰፊ አገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ባይኖረውም እኳን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርበው ምንባብ ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት በቅርበት የመገኘት መስፈርትን የተመለከተ ነው:: ሌሎቹ የቃላት ድግግሞሽ መጠን የፍቺ ሽፋን ተስተማሪነትና የተማሪዎች ፍላጎት ከግምት በማስገባት መምረጥ የሚሉት ትኩረት አልተደረገባቸውም:: አደረጃጀትን በተመለከተ የቃላት ትምህርቶቹ የመማር ሂደቱ በጠበቀ መልኩ ከቀላል ወደ ከባድ እንደተደራጁ ጥናቱ ያመላክታል:: ከአንድ ቃል ጋር አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ ቃላዊ ሀረጎች ማለትም ጥምር ቃላትን፥ በጥመራ የሚፈጠሩ ፈሊጦችን የመሸጋገሪያ ቃላትንመርጦና አደራጅቶ ለትምህርትነት ከማቅረብ አንፃር ትኩረት እንደተሰጠባቸው በጥናቱ ተረጋግጧል:: ከፍቺ ተዛምዶ አንፃር የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነትን ለማስተማር የቀረቡተግባራት በመማሪያ መፅሀፋ አልተካተቱም:: ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብና በፍቺ ተዛምዷቸው ማቅረብ ሰፊ ሽፋን ተሰጥቷቸው ቀርበዋል:: የቃላትን ትምህርት ከማድመጥና ከመናገር ክሎሎች ጋር አጣምሮ ከማቅረብ አንፃር ውስንነት ታይቷል:: ተማሪዎች የመዝገበ ቃላትን አጠቃቀም ጥበብ እንዲያውቁ የሚያግዙ ተግባራት እንደተካተቱ የጥናቱ ውጤት ያሳያል:: መማሪያ መፅሀፋና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሀ ትምህርት አብዛኛው በታላይ ተጣጥሞሽ ያላቸው ሲሆን በተወሰነ መልኩ የማይጣጣሙበት ሁኔታ እንዳለ በጥናቱ ተጠቁሟል:: በመጨረሻም ከጥናቱ ግኝት ጋር በተያያዘ መልኩ ከተጠቀሱት አስተያየቶች መካከል ለምሳሌ የቃላት መረጣ ሲካሄድ በተቻለመጠን ቋንቋንለጠቅላላ አላማ ለማስተማርታስቦ ለሚነደፍ መርሀግብር እንዲውል በመስኩምሁራን ለተሰነዘሩት የቃላትመምረጫ መስፈርቶች ተገቢትኩረት ቢሰጥ፥እንዲሁም ለትምህርት የሚቀርቡየቃላት ተግባራት የማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ ባይወሰኑ፥ ከምንባቡ ውጪም ተገቢየሆነ አውድ ተፈጥሮላቸው ቢቀርቡ፥ የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተ ደግሞ ከሚያነሱት ርዕሰጉዳይ አንፃር ቃላትን ማደራጀት የሚለው መስፈርት የተሰጠው ሽፋን አነስተኛ በመሆኑ ሚዛናዊ አድርጎ ለማደራጀት ቢሞከርና የመሳሰሉትን አስተያየቶች በመስጠት ተጠናቋል::*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ከቋንቋ ትምህርት መሳሪያዎች አንዱ ሲሆን ለአንድ የክፍል ደረጃ መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ Ur (2006፡183) ሲገልጹ ‹‹መማሪያ መጽሀፍ የምንለው በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ይዘቶችን አጠቃሎ የሚይዝ ነው›› ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ተስፋዬ (1981፣89) ‹‹የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ፣ እድሜና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጅ ለተወሰነ ክፍል ማስተማሪያነት የሚያገለግል መሳሪያ ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንዲሁም Dubin and Olishtian (1992፡45) ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚዘጋጁ መማሪያ መጽሀፎች አስመልክተው ሲገልጹ ‹‹ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚዘጋጁ መማሪያ መጽሀፎች የታላሚውን ቋንቋ ክህሎት ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶችን አቀናብረው የያዙና የቋንቋ ሥነልሳናዊ፣ ሥነትምህርታዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል›› ይላሉ፡፡

ሥነ ልሳናዊ ይዘቶች ሥንል በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ድምጾች፣ ምዕላዶች፣ ቃላት፣ አረፍተ ነገሮች ወዘተ የሚሉትን ጉዳዮች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ይህም አንድ ድምጽ ከሌላ ድምጽ ጋር ሲቀናጅ ምን አይነት ባህሪ እንደሚያሣይ፣ አንድ ቃል በአረፍተ ነገር ውስጥ ያለውን አገባብና አገልግሎት ምን እንደሚመስልና የመሳሰሉት ጉዳዮች ይመለከታል፡፡ እንዲሁም ከምን ተነስተን ምን ላይ መድረስ እንዳለብን፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ምን ላይ ማተኮር እንደሚገባን ለመወሰን ይረዳናል፡፡ ሥነ ትምህርታዊ ይዘት ስንል ደግሞ ተማሪው ቀድሞ ምን ተምሯል? አሁን ምን አይነት ይዘት ይፈልጋል? በቋንቋው ምን መጠቀም ይፈልጋል? ይዘቶቹስ እንዴት መቅረብ አለባቸው የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች እንደሚያጠቃልል (Dubin and Olishtian, 1992) አክለው ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው የሚዘጋጁት መማሪያ መጽሀፎች የተማሪዎችን ዕድሜ፣ ፍላጎትና ችሎታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡ እንዲሁም ሥነ

ልሳናዊና ሥነ ትምህርታዊ ግንዛቤዎችን ከግምት ውስጥ አስገብተው የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህ ሁኔታ የተዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍትም በውስጣቸው የተለያዩ ይዘቶችን አካተው ይይዛሉ፡፡ ከነዚህም ይዘቶች መካከል አንዱ ቃላትን የሚመለከት ይዘት ነው፡፡

ስለ ቃላት ትምህርት ሲነሳ በትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት የሚመረጡና የሚደራጁት አይነትና ብዛታቸው እንዲሁም የሚቀርቡበት የክፍል ደረጃ የሚወሰነው በመርሀ ትምህርት ነዳፊዎችና በመማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ምን አይነት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሀፍት ይካተቱ? እንዴት ባሉ አኳኋን ተደራጅተው ይቅረቡ? የሚሉ ጥያቄዎች በሌሎች አካላት (በመርሀ ትምህርት ነዳፊዎችና በመማሪያ መፅሀፍት አዘጋጆች) የሚመለስ ይሁን እንጂ የመማሪያና የማስተማሪያ መሳሪያዎች እንዴት እንደተነደፉ ይዘቶችን ለመምረጥ ምንምን አይነት መስፈርቶች በስራላይ እንደዋሉ መረዳቱ ከሌሰ መርሀ ትምህርቱንም ሆነ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመገምገም አዳጋች ይሆናል፡፡

ለቃላት ትምህርት አስመልክተው Allen (1983) ሲገልጹ ለብዙ ዓመታት ይሰጥ የነበረው ትኩረት በጣም አነስተኛ ነበር፡፡ ቃላትን የሚጠቀሙባቸው ሌሎች ክሂሎችን (ማድመጥ፣ መናገር፣ መጻፍና ማንበብን) ለማስተማር እንጂ ቃላትን ለማስተማር ታስቦ አልነበረም፡፡ ቃላትን ለማስተማር በስርዓት የተዘጋጀና የታወቀ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ የለም፡፡ ይህም ለቃላት ትምህርት ይሰጥ የነበረው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ እንደነበር ያስረዳል፡፡ ቀስ በቀስ ግን ለቃላት ትምህርት ትኩረት እየተሰጠ የማስተማር አስፈላጊነቱም እየታመነበት እንደመጣ ይናገራሉ፡፡

የቃላትን ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክተው Harmer (1991) ሲያስረዱ ማንኛውም ቋንቋ የቃላት ድምር ውጤት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ነባራዊ ዕሳቤዎችን ወክለው የሚገኙትም ቃላት ናቸው፡፡ የቃላት እውቀት ደግሞ መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ሊገኝ ይችላል፡፡ መደበኛ በሆነ መንገድ የሚገኝ የቃላት እውቀት በመርሃ ትምህርት ውስጥ ተቀርጸው፣ በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሚያስተምርና የሚማር አካል ተገኝተው በሚያከናውኑት የመማር ማስተማር ሂደት የሚገኝ እውቀት ነው፡፡ በርግጥ በሁለቱም መንገድ የቃላት እውቀት የሚገኝ ቢሆንም መደበኛ በሆነ መንገድ የሚማሩት ቃላት ካላቸው መደበኛ አጠቃቀም አንጻር በተሻለ ሁኔታ ሃሳብን ለመግለጽ እንደሚያስችላቸው ይናገራሉ፡፡

እንደ McCrostie (2007፡5) ገለጻ ‹‹በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ትምህርት በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምክንያቱም በተግባቦት ሂደት ተማሪዎች አላማቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ድርጊታቸውንና ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ ለሌሎች ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል የቃላት እውቀታቸው ቁልፍ ሚና አለው›› ብለዋል፡፡ በተጨማሪም McCarthy (1990፡viii) ‹‹ሃሳብን በንግግር ሆነ በጽሁፍ ለመግለጽ፣ ሃሳቦችን አዳምጦና አንብቦ ለመረዳት እንዲሁም ለተግባቦታዊ ክንውን መሳካት የቃላት እውቀት መኖር ወሳኝ ነው›› በማለት ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም Rajaee (2013፡3) ‹‹ተግባቦታዊ ክንውን ዘወትር የሚደናቀፈውም ተገቢ ቃላትን በትክክል በተገቢው አውድ ባለመጠቀም ነው፡፡ ያለ በቂ የቃላት እውቀት በአግባቡ መግባባት እጅግ ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም የቃላት እውቀት ለስኬታማ ተግባቦት ዋነኛ መሳሪያ ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት የሙህራን ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ቃላትን በተፈለገው ቦታ እስካልተጠቀምን፣ ሀሳባችንን በትክክል የሚገልጽ ቃላትን እስካላወቅን ድረስ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ተግባቦትን ለመፍጠር ከባድ መሰናክል ሊገጥመን እንደሚችል ነው፡፡ ይህም የቃላትን ትምህርት ምን ያክል አስፈላጊ እንደሆነና በቋንቋ ትምህርትም ለቃላት ቅድሚያ ትኩረት መስጠት እንዳለበት እንረዳለን፡፡

የቃላት ትምህርት ሊያካትታቸው የሚችሉ ጉዳዮችን አስመልክተው McCarthy (1990፡3) ሲጠቅሱ ‹‹ቃላት ትርጉም ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ነጠላ ቃላት፣ በተለያዩ የዕርባታና የምስረታ ምዕላዶች የረቡና የተመሰረቱ ቃላት፣ ጥምር ቃላት፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችና የተለመዱ አገላለጾችን የያዘ ቃላት ማለታችን ነው›› በማለት ገልጸዋል፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣193) ቃል አንድ ጽንስ ሃሳብ በመወከል በድምጽ የተነገረ ወይም በጽሁፍ የሰፈረ የድምጽ ምልክቶች ቅንብርና አነስተኛ የአረፍተ ነገር ክፍል እንደሆነ ያስረዳል፡፡

እንደ Pikulski and Templeton (2004፡49) ገለጻ ‹‹ተማሪዎች በዓለም ላይ ከሚገኙ ተዋናዮች እረድፍ መሰለፍ እንዲችሉ ተገቢ የቃላት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በዚህ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውስብስብነት በሞላበት ዓለም የሚኖራቸው ዓቅም የሚወሰነው ባላቸው የቋንቋ ችሎታና የቃላት እውቀት ነው›› ብለዋል፡፡

አንድ ሰው የአንድን ቋንቋ ቃላት አወቀ ለመሰኘት ደግሞ ለመናገርና ለመጻፍ ተገቢ የሆነ ቃላት ከመረጠ፣ በተፈለገ ግዜ አስታውሶ መጠቀም ከቻለ፣ የቃላት ፍቺ ስፋትና ጥበት ካወቀ እና መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል እውቀት ካለው፣ እንዲሁም ከሁኔታና ከአገልግሎት አንጻር የቃሉን አጠቃቀም ውስንነት ከለየ ተገቢ የሆነ የቃላት እውቀት አለው ማለት ይቻላል (Pikulski and Templeton, 2004) በማለት አክለው ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው ቃል ማለት ትርጉም አልባ ድምፆች በሥርዓት ሲቀናጁ የሚፈጠር፣ በራሱ ፍች ያለውና በንግግር ወይም በጽሁፍ የሚገለፅ እንደሆነ ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ሰው የቃላት  እውቀት አለው ማለት የሚቻለው ከሁኔታና ከአገልግሎት አንጻር የቃሉን ውስንነት አውቆ መጠቀም ከቻለ፣ ቃሉ አንድ ወይም ብዙ ፍቺ ያለው መሆኑን ካወቀ፣ ለመናገርና ለመጻፍ ተገቢ የሆነ ቃላትን መርጦ የተጠቀመ እንደሆነ ነው፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች በቋንቋ ለሚፈጥሩት መስተጋብር የጠራና የተቀላጠፈ ተግባቦት ይኖር ዘንድ ቃላት የጎላ ሚና እንዳላቸው ምሁራን ከሰጡት አስተያየት መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም እስካሁን ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉት መማሪያ መጽሀፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ሲሆን አሁን ላይ ግን አስማምቶ ማዘጋጀት ተጀምሯል፡፡ በዚህም የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የተስማማ በሚል ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ተጠቃሽ ነው፡፡

የዚህ ጥናት አብይ ትኩረትም በደቡብ ምዕራብ ክልል በ2015 ዓ.ም በሥራ ላይ የዋለው አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው፡፡ እንዲሁም መማሪያ መጽሃፉ መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ ስለሚዘጋጅ የቃላት ይዘቱን ለመምረጥ፣ ለማደራጀትና ለማቅረብ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው በተተኳሪው መጽሃፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽም ይቃኛል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ በዚህ ርዕስ ጥናት እንድታደርግ ያነሳሳት ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ቀድሞ በዚህ ክፍል ደረጃ ስታስተምርበት የነበረው መማሪያ መጽሃፍ የቃላት ትምህርት ይዘት በተወሰነ ነጥብ ላይ የሚያተኩርና በአብዛኛው በአውድ ያልተደገፈ ይመስላት ስለነበር አሁን አዲሱ ተተኳሪው መጽሃፍ በምን አይነት መልክ ተዘጋጅቶ ይሆን የሚለው ለመፈተሽ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ አዲስ እንደመሆኑ መጠን እንደ አጥኚዋ እውቀት ጠንካራና ደካማ ጎኑ በሰነድ በመፈተሽ በጥናትና ምርምር ተደግፎ ግምገማ ያልተካሄደበት በመሆኑ እንድታይ ተነሳስታለች፡፡ ስለሆነም መማሪያ መጽሃፉ በውስጡ ያካተታቸው የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት መምረጫ፣ ማደራጃና ማቅረቢያ መስፍርቶችን ተከትለው የተዋቀሩ መሆን አለመሆናቸውን ትፈትሻለች፤ የታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በመለየት ጥቁምታም ትስጣለች ፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ጥናቱ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ምን ይመስላል? የሚለውን አብይ ጥያቄ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ትመልሳለች፡፡ እነሱም፡-

ሀ. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች ሙሀራን በጠቆሟቸው ዋና ዋና የቃላት መምርጫ ዘዴዎች መሰረት በማድረግ ተመርጠው ይሆን?

ለ. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት ቃላት ትምህርቶች ሙሀራን በጠቆሟቸው ዋና ዋና የቃላት ማደራጃ መንገዶች መሰረት በማድረግ ተደራጅተው ይሆን?

ሐ. በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች የማቅረቢያ መንገዶችን መሰረት በማድረግ ቀርበው ይሆን?

መ. በተተኳሪው በመጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ተጣጥሞሽ ይኖራቸው ይሆን? የሚሉት ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በደቡብ ምዕራብ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት፡፡

ሀ. የመማሪያ መፅሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥን መመርመር፣

ለ. የመማሪያ መፅሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀትን መፈተሽ፣

ሐ. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት የማቅረቢያ መንገዶችን መመርመር፣

መ. በተተኳሪው መጽሃፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ. በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚካተቱት የቃላት ትምህርቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ምን መምሰል እንዳለበት ለቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ለ. በመጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ላይ ወደፊት ለሚደረግ ማሻሻያ ሀሳቦችን ይጠቁማል፡፡

ሐ. በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ አካላት እንደ መነሻ ሀሳብ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው፡፡ በተጨማሪም መማሪያ መጽሀፍ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያለው የቃላት ትምህርት ይዘት ተጣጥሞሽ ትቃኛለች፡፡

መማሪያ መጽሀፉ ‹‹በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ ትምህርት ቢሮ እና በዲላ መምህራን ት/ኮሌጅ የተስማማ›› በሚል ቀርቧል፡፡

ይህ ጥናትም በክልሉ በ2015 ዓመተ ምህረት በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በሌሎች ክልሎች ተስማምተው የቀረቡ መጻሕፍት በዚህ ጥናት አይዳሰሱም፡፡ እንዲሁም በቃላት ትምህርት አሰጣጥ የመምህር ተማሪ መስተጋብር፣ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የመምህራንን የቃላት ትምህርት አተገባበር አይመረምርም፡፡

ከዚህም ሌላ በጥናቱ የተተኳሪው መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ለመመርመር በመረጃ ምንጭነት በዋናነት ያገለገሉት መመማሪያ መጽሃፉና መርሃ ትምህርቱ ሲሆኑ በአጋዥነት ደግሞ ለመማሪያ መጽሃፍ አዘጋጆች የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ ነበር፡፡ ነገር ግን አዘጋጆችን ማግኘት ስላልተቻለ ከአማካሪ ጋር በመነጋገር ቃለ መጠይቁ እንዲቀር ተደርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሰነድ ፍተሻ ላይ ብቻ ተገድቧል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማች ጽሁፍ ቅኝት

## 2.1. የቃላት ምንነት

የቃላት ምንነትን በሚመለከት ወጥነት ያለው አንድ ብያኔ ባይገኝም የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ለመሰንዘር ሞክረዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Ur (2006፡60) ‹‹ቃል በግርድፉ ሲታይ አንድ ጽንሰ ሀሳብ የሚወክል የድምጾች ቅንጂት ነው›› በማለት ያብራራሉ፡፡ በተጨማሪም ባዬ (2000) ድምፆች በራሳቸው ትርጉም አልባ መሆናቸውና እነዚህም ፍቺ አልባ ድምጾች ስርዓት ባለው መንገድ ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ፍቺ አዘል ምዕላድ ቃል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ስለጥምር ቃል ጌታሁን (1990፣68) ሲገልጹ ‹‹ጥመራ ቃላትን በማጣመር ሌላ አዲስ ቃል የመፍጠር ዘዴ ወይም ስርዓት ነው፡፡ የጥምር ቃል አፈጣጠር ሲመረመር በአጣማሪ ምዕላድ አማካይነት ወይም ተጣማሪ ቃላቱን በአንድ ላይ በማሰለፍ /ያለአጣማሪ/ ሊከናወን ይችላል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Wallace (1988) ጥምር ስሞችና ጥምር ግሶች የአመሰራረት ሂደታቸውን በመከተል ማቅረብና ተማሪዎች ሂደቱን ተከትለው ጥምር ቃላቱን እንዲመሰርቱ፣ እንዲሁም በአውድ አቅርቦ ጥምር ቃላቱን በሌላ እንዲተኩ፣  እንዲሁም ተማሪዎች ቃላትን በማጣመር አዳዲስ ቃላት እንዲመሰርቱ በማድረግ ማቅረብ እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡

Diedrichs (2005፡25) Lewis & Hill (1992)ን በመጥቀስ ቃል ከቃል ግንድ እና ቅጥያ ምእላድ ብቻ የሚመሰረት ሳይሆን ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት ጥምረት ሊፈጠር ይችላል ብለዋል፡፡ ይህም ከአንድ ቃል በላይ የሆኑ ቃላዊ ሀረጎች በቃላት ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ:(ብረት ድስት) የሚለው ቃል ስንመለከት ከሁለት እራሳቸውን ችለው ከሚቆሙ ምዕላዶች የተመሰረተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ብረት ድስት የሚለው የሁለት ቃላት ቅንጅት ሁኖ የቆመው ለአንድ ነጣላ ፍች በመሆኑ እንደ አንድ ቃል ይቆጠራል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ቃል ማለት ትርጉም አልባ ድምጾች ስርአታዊ ቅንጂት ሁኖ ራሱን ችሎ የሚቆም፣ አንድ ጽንሰ ሀሳብ በመወከል

ፍቺ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ነው። እንዲሁም ከአንድ ቃል በላይ የሆኑ ቃላዊ ሀረጎች በቃላት ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን።

## 2.2. የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በዚህም ምክንያት ለቃላት ትምህርት ትኩረት መስጠት እንዳለበት የተለያዩ ምሁራን ይናገራሉ። ከነዚህም ውስጥ Harmer (1991:53) የቃላትን ትምህርት ወሳኝነት ሲገልጹ ‹‹የቋንቋ መዋቅር (Structure) የቋንቋን አጽም የሚፈጥር ከሆነ መሰረታዊ ብልቶቹና ስጋው የሚደራጀው ከቃላት ነው›› በማለት ያብራራሉ።

እንደ Wallace (1988:9) ገለጻ ‹‹የአንድ የቋንቋ ስርዓት እንዴት እንደሚሰራ በጥሩ ሁኔታ ማወቅ እየተቻለ በቋንቋው ለመግባባት የሚያስችል እውቀት ላይኖር ይችላል። የምንፈልጋቸው ቃላት የሚኖሩን ከሆነ ግን ብዙውን ጊዜ እንደነገሩም ቢሆን በቋንቋው መግባባት ይቻላል›› በማለት ስለ ቃላት አስፈላጊነት ተናግረዋል።

ከላይ ከቀረቡት ሙህራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በቋንቋ ትምህርት ቅድሚያ ለቃላት ትኩረት መስጠት እንዳለበት ሲሆን በየትኛውም ደረጃ ያሉ የቋንቋ ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸው መዳበር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ነው። ምክንያቱም በአራቱ ክህሎች አቀላጥፎ ለመጠቀም ቃላት አውቀት ቁልፍ ሚና አለው። ነገር ግን በቂ የቃላት እውቀት ከሌላቸው በቋንቋው በአግባቡ ለመግባባት ይቸገራሉ። ስለሆነም ለስኬታማ ተግባቦት የቃላት እውቀት መኖር ዋነኛ መሳሪያ መሆኑን እንረዳለን።

ቃላት በቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አስፈላጊነት አስመልክተው Su(2010፡19) Cruse(2000)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ‹‹በቋንቋ ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ ከሰዋሰው ይልቅ ለቃላት ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው። ምክንያቱም ቃላት በአግባቡ መጠቀም እስካልተቻለ ድረስ የቋንቋን ሰዋሰዋዊ መዋቅር ማቀናበር መቻል ብቻውን መልዕክት ለማስተላለፍ አያበቃም›› በማለት ያብራራሉ።

በቋንቋ ትምህርት ለተግባቦት እንደመሰረተ ድንጋይ የሚቆጠሩት የሰዋሰው ይዘቶች ሳይሆኑ ቃላት ናቸው። በመዋቅር ውስጥ የትኛው ነው ትክክል የሆነው ሰዋሰውና ትክክል ያልሆነው

ሰዋሰው ለሚሉት ጥያቄዎች መለስ የሚወስኑት ቃላት እንደሆኑም (Diedrichs, 2005) ይናገራሉ። እንዲሁም Ur (2006፡62) ‹‹ተማሪው በቋንቋው የቃላት እውቀት ባለቤት እንዲሆን ከተፈለገ የቀደመ እውቀቱን ያገናዘበ የቃላት ትምህርት ይዘት ሊካተተ ይገባል። ይዘቱም የቃላትን ንበት፣ የንግግርና የፅህፈት ቅርፅ እንዲሁም ፍችን መለየት የሚስችል መሆን አለበት›› በማለት ይገልፃሉ።

እስካሁን ከተነሱት የሙህራን ገለጻ የቃላትን ትምህርት አስፈላጊነት መረዳት ይቻላል። በቋንቋው መዋቅር የጠለቀ እውቀት ቢኖረንም እንኳን ቃላትን በተፈለገው ቦታ እስካልተጠቀምንና ሀሳባችንን በትክክል የሚገልጽ ቃላትን እስካላወቅን ድረስ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ተግባቦትን ለመፍጠር ከባድ መሰናክል ሊገጥመን ይችላል። የቃላት እውቀት በቋንቋ ለሚከናወን ተግባቦት ወሳኝ በመሆኑ በቋንቋ ለመዳ ሂደት ከሰዋሰዋዊ አገባብ እውቀት በፊት በቅድሚያ መዳበር እንዳለበት እንረዳለን። ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት መሰረቱ የቃላት እውቀት በመሆኑ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ከቀረቡት ገለጻዎች መገንዘብ ይቻላል።

ስለቃላት እውቀት Wallace (1988) ሲገልጹ አንድ ሰው የቃላት እውቀት አለው ለማለት የሚቻለው በንግግር ወቅት የቃላትን ትክክለኛ ቅላፄ አውቆ መጠቀም ከቻለ፣ የቃላትን እማራዊና ፍካራዊ ፍቻቸውን ከተገነዘበ፣ ቃላት ከሚወክሉት ቁስና ጽንስ ሃሳብ ጋር ማዛመድ ከቻለ፣ የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም ከለየ፣ የቃላትን የንግግር ወይም የፅህፈትን ቅርፅ መለየት ከቻለ፣ እንዲሁም ተገቢውን የመደበኛነት ደረጃ ጠብቆ መጠቀም ከቻለ የቃላት እውቀት አለው ለማለት ይቻላል።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ጥሩ የቋንቋ ተጠቃሚ ለመሆን ስለ ቃላት እውቀት የተዘረዘሩትን ባህሪያት ማሟላት አስፈላጊ መሆኑን ነው። ስለዚህ እነዚህን የቃላት እውቀት ለማላበስ የሚያበቁ የቃላት ትምህርት ይዘቶች በትምህርትነት መቅረብ እንዳለባቸው ይታመናል። ይዘቶቹ እንዴት ተመርጠው ተደራጅተው ይቅረቡ የሚለው ቀጥሎ የሚታይ ይሆናል።

## 2.3. የቃላት ትምህርት አመራራጥ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡት ቃላት በይዘታቸውም ይሁን በቅርፃቸው የተማሪዎችን አቅም፣ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ ያገናዘቡ መሆን አለባቸው። ይህን አስመልክቶ Ferreira

(2007፡13) እንደገለጹት ‹‹በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ስለሚካተቱት የቃላት ትምህርት ሲነሳ ለተማሪዎች ባላቸው ጠቀሜታ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቃላት እንዴት መመረጥ አለባቸው? የሚለው አብይ ጥያቄ ነው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም Pikulski and Templeton (2004፡62) በበኩላቸው ‹‹የቃላት ትምህርት ለዕለት ተለት መግባቢያነት የሚያገለግሉ ቃላትን መሰረት አድርጎ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ይህም ቀስ በቀስ የቃላትን የአገልግሎት ደረጃና ተገቢነት ተከትሎ ለማስተማር ያግዛል›› በማለት ያብራራሉ፡፡

ስለሆነም ለትምህርትነት የሚውሉ ቃላትን ስንመርጥ የተለያዩ መምረጫ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን እንዳለበት ነው፡፡ እነዚህንም መስፈርቶች በተመለከተ Harmer (1991:154) የቃላት የድግግሞሽ መጠንና የፍቺ ሽፋን መሰረት አድረጎ መምረጥ እንደሚቻል ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም Udaya (2015፡47) የቃላት ድግግሞሽ፣ የስርጪት መጠን፣ በቅረበት መገኘትና የፍቺ ሽፋን መሰርት አድርጎ መምረጥ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

Gairns and Redman (1986:57) and McCarthy (1990:79) ደግሞ የቃላት ድግግሞሽ መጠን፣ የተማሪዎች ፍላጎትና የብስለት ደረጃ፣ ተስተማሪነት፣ በቅርበት መገኘት፣ የፍቺ ሽፋን ወዘተ የሚሉትን ከግምት በማስገባት መምረጥ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ዋና ዋና መምረጫ መስፈርቶችን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፡፡

### 2.3.1. የቃላት ድግግሞሽ መጠን

የቃላት ድግግሞሽ በውሁድ አሃድ ስብስቦች ላይ ያተኮረ የቃላት አጠቃቀም ጥናትን መሰረት በማድረግ በጣም ተደጋገመው የተከሰቱ ቃላትን መለየት የሚቻልበት ስልት ነው Biber, Conard and Reppen (1998:53)፡፡ እንዲሁም Nunan (1998:118) ለዕለት ተዕለት ተግባቦት ሂደት የሚያገለግሉ ተዘውታሪ ቃላትን ለይቶ ማስተማር ተማሪዎችን በቋንቋ ለመጥቀም የሚያስችል ውጤታማ የማስተማር ስልት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም Udaya(2015፡48) ተዘውታሪ ቃላት ለማንኛውም ቋንቋ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን እና የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ እነዚህን ቃላት አስቀድሞ ማስተማር ጠቃሚ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

ለቋንቋ ማስተማሪነት የሚቀርቡ ቃላት ተዘውታሪ ቃላት ሊሆኑ ይገባል፡፡ እነዚህን ቃላት መርጦ ቅደም ተከተላቸውን ለመወሰን በዕለት ተዕለት በሚደረግ ተግባቦት ያላቸው የድግግሞሽ

መጠን (Frequency)፣ ዝርዝር (Word List) አዘጋጅቶ መወሰን ይቻላል፡፡ የአሃድ ስብስብ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትን በመምረጥ ረገድ የትኞቹ ቃላት ወይም የተለመዱ አገላለጾች ተዘውታሪ እንደሆኑ ለመለየት፣ የንግግርና የጽሁፍ ቃላትን ለመለየት፣ እንዲሁም የቃላትን አውዳዊ አጠቃቀምና የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውን ቃላት ለመለየት ያስችላል (McCarten, 2007) በማለት ያብራራሉ፡፡

እንዲሁም Nunan (1998:119) ‹‹ቋንቋን ለአጠቃላይ ዓላማ ማስተማር ሲፈለግ ተዘውታሪ ቃላትን በድግግሞሽ ቆጠራ ላይ ተመርኩዞ መምረጥ ተገቢ ሲሆን ተፅዕኖ የሚያደርሱ ተለውጦዎችን በመቆጣጠር ከተከናወነ የቆጠራው ውጤት ከጠቃሚነት ጋር አወንታዊ የሆነ ግንኙነት ይኖረዋል›› ብለዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው የቃላት የድግግሞሽ መጠን ማለት የተለያዩ ውህድ አሀዶችን በመውሰድ የተወሰነ ቃል በተደጋጋሚ የተከሰተበትን ቁጥር በመለየት የተደጋጋሚነቱ መጠን የሚገለጽበት እንደሆነ ነው፡፡ ለትምህርትነት የሚያገለግሉ ቃላት ምርጫ ሲካሄድ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ያሉ መሆኑንና ከዚህ ውስጥ መረጣው የሚካሄድበት ውህድ አሀድ አንዱ እንደሆነም እንገነዘባለን፡፡ ነገር ግን ይዘቱ በተወሰነ ሙያ ላይ የሚያተኩር ከሆነ በድግግሞሽ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት የተለመዱ አገላለጾችና ሙያን የሚገልጹ ቃላት ብቻ ይሆናሉ፡፡ በጥቅሉ እነዚህን ተዘውታሪ ቃላት ለይቶ ማስተማር የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ከማሳደግ አንጻር ውጤታማ የማስተማር ስልት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.3.2. የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ

ተማሪዎች እንዲማሩ የሚቀርብላቸው ቃላት ሲመረጥ ፍላጎታቸውና የእውቀት ደረጃቸውን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም ምን እንደሚወዱና እንደሚጠሉ በመለየት ከእምነታቸውና ከታሪካዊ ዳራቸው ጋር የማይጋጩ (የማየጣረሱ) ይዘቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን አስመልክተው McCarthy (1990:69) ሲገልጹ ‹‹የቃላት ትምህርት ይዘቱ የተማሪውን እድሜና የትምህርት ደረጃ እንዲሁም የቀደመ እውቀቱን አገናዝበው አዲስ ነገር ሊጨምሩለት የሚችሉ መሆን አለባቸው›› ብለዋል፡፡

እንዲሁም ምንውየለት (2005፣15) Atkins (1996)ን ጠቅሶ እንደገለጸው ‹‹የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች ቃላትን ለመምረጥ ሲነሱ በመምህራን የተካሄዱ የተማሪዎች ፍላጎት ዳሰሳዎች

መሰረት በማድረግ በግል ደረጃ እያንዳንዱን ተማሪ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ፍላጎት በመተንበይ ማካተት አለባቸው›› በማለት ያስረዳሉ::

በተጨማሪም Allen (1983:108) የተማሪዎችን ፍላጎት ለመተንበይ ተማሪዎች በአካባቢቸው ስላሉ ሰዎች፣ ሥለነገሮችና ክስተቶች መናገር እንዲችሉ የትኞቹ ቃላት ያስፈልጓቸዋል? ሲማሩ በተደጋጋሚ ለሚያጋጥሟቸው መመሪያዎች ምላሽ ለመስጠትስ የትኞቹን ቃላት ማወቅ ይኖርባቸዋል? እንዲሁም የተወሰነ ‹‹አካዳሚዊ›› ብቃታቸውን ለማሟላት የትኞቹን ቃላት ማወቅ ይጠበቅባቸዋል? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመመለስ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተማሪዎችን ፍላጎት በመተንበይ በቃላት መረጣው ማካተት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት የሙህራን ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ለትምህርትነት የሚርቡት ቃላት ሲመረጡ የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ ከግምት ማስገባት አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ መምረጥ እንደሚቻልና የሚመረጡት ቃላትም የተማሪውን የቀደመ እውቀት መሰረት አድርገው አዳዲስ ነገሮችን ሊጨምሩለት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.3.3. ተስተማሪነት (learnability)

ተስተማሪነት አንድ ቃል ወይም ቃላዊ ሃረግ ለመማር ከባድ ወይም ቀላል ሁኖ መገኘቱን የሚያመለክት ነው፡፡ ለመማር ቀላል ሁኖ ሲገኝ የተስተማሪነት ደረጃው ከፍ ሲል በአንጻሩ ደግሞ ከባድ ሁኖ ሲገኝ የተስተማሪነት ደረጃው ዝቅ ያለ ይሆናል (ምንውየለት፣ 2005) በማለት ገልጸዋል፡፡ ተስተማሪነት የቃላት ድግግሞሽ መጠን ጋር ተያዥነት እንዳለው ያስባሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ተዘውታሪዎቹ ቃላት በተደጋጋሚነት ሊያጋጥሙ በመቻላቸው ለመማር ይቀላሉ ተብሎ ስለሚገመት ሲሆን ተስተማሪነት ግን ከዚህም በላይ እንደሆነ (Richards, 2009) ይናገራሉ፡፡

ቃላትን ለመማር አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምክንያቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ቃላት ውስብስብ ባህሪ ሲኖራቸውና ቃላቱ ከተማሪዎች ህይወትና የህይወት ልምድ ሲርቁ እንዲሁም ተማሪዎች የተለያዩ ቃላት በፍች ተመሳሳይ እንደሆኑ ሲያስቡ ቃላትን ለመማር ይቸገራሉ፡፡ በመሆኑም በጣም ተደጋግመው በአገልግሎት ላይ የሚውሉ ቃላት የተስተማሪነት ደረጃቸው ከፍተኛ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ለትምህርትነት የሚቀርቡት ቃላት ከተማሪዎች ልምድ ህይወት ጋር

የማይገናኙ እና አገባባዊ ባህሪያቸው ውስብስብ ከሆነ የተስተዋይነት ደረጃቸው ዝቅተኛ እንደሚሆን (McCarthy,1990) ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ለትምህርት የሚቀርቡት ቃላት ተደጋግመው አገልግሎት ላይ የሚውሉ ከሆነ የተሰተማሪነት ደረጃቸው ከፍተኛ እንደሆነ፣ ነገር ግን ቃላቱ የሚወክሉት ጽንሰ ሀሳብ ከተማሪው ልምድ የራቀ ከሆነ ደግሞ ሊከብድ እንደሚችልና በቃላት ተስተማሪነት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ቃላት ለትምህርትነት ሲመረጡ በዋናነት ለትምህርት ምቹ መሆናቸውን በማረጋገጥ ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ እያለ እያደጉ የሚሄዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

## 2.3.4. የፍቺ ሽፋን

የፍቺ ሽፋንን አስመልክተው Udaya(2015፡10) ‹‹በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ፍቺን በማስተላለፍ እረገድ እኩል የአገልግሎት ሽፋን የላቸውም፡፡ አንዳንድ ቃላት በርካታ ፍቺን በመሸከም በተለያዩ አውዶች ሰፋ ያለ ፍቺን ያስተላልፋሉ፡፡ ጠባብ ፍቺ ያላቸው ደግሞ ሰፊ ፍቺ ባላቸው ቃላት ሊተኩ ስለሚችሉ እነዚህን ታሰቢ አድርጎ መምረጥ ያስፈልጋል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

እንደ Wallace (1988) ገለጻ አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍቺ ስላላቸው ሀሳብን አምቆ የመያዝ ችሎታ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ጠባብ ፍቺ በመያዛቸው ሰፊ ፍቺ ባላቸው ቃላት ሥር ይጠቃለላሉ፡፡ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንፃር እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይኖራቸዋል፡፡ሰፊ ፍቺ ያላቸው ቃላት ሚስጥር አምቆ የመያዝ ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ የተለየ ትርጉም የመስጠት ባህርያቸው ፍካሬያዊ ትርጉም ሲሆን እማራዊ ደግሞ ቃላቱ በቀጥታ የቆሙለትን ጽንሰ ሀሳብ ለመጠቆም በሚያስችል ሁኔታ ስራ ላይ የሚውልበትን እሳቤ እንደሚጠቁም ገልጸዋል፡፡ ከቃላት እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በተጨማሪ የቃላት ጥመራ፣ የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት፣ የፈሊጦችን ፍቺ ወዘተ ታሳቢ አድርጎ በመምረጥ ለትምህርትነት ማቅረብ ይገባል፡፡

### 2.3.5. በቅርበት መገኘት

ቃላት መማር ማስተማሩን ያግዛሉ ተብሎ ሲታመንባቸው በትምህርት ውስጥ ይካተታሉ፡፡ እነዚህ ቃላት ሙያን የሚገልጹ ወይም ወቅታዊ ቃላት ሊሆኑ ይችላሉ (Gairns and Redman, 1986) በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም Richards (2009) ቃላት በቅርበት በመገኘታቸው ይመረጣሉ ሲባል አንዳንድ ቃላት ተዘውታሪ ሳይሆኑ ነገር ግን በአጋጣሚ ለማስተማሪያነት በሚውለው ውህድ አሀድ ውስጥ በመገኘቱ ለትምህርትነት የሚውሉበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም Wallace (1988) በቅርበት የመገኘት መስፈርት የሚያመለክተው በተወሰኑ የመማር ሁኔታዎች ውስጥ ያልተለመዱ (በተደጋጋሚ በአገልግሎት ላይ ያልታዩ) ቃላት በጽሁፍ ውስጥ በመገኘታቸው ብቻ የሚካተቱበት ሁኔታ ነው፡፡ አንድ ቃል ሰፊ ግልጋሎት፣ ሽፋንና ስርጪት ሳይኖረው ቋንቋን ለማስተማር በሚቀርብ ውህድ አሃድ ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ቃሉ ተመርጦ በይዘትነት እንዲካተት ይደረጋል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ለትምህርትነት የሚመረጡት ቃላት የተለያዩ መምረጫ መስፍርቶች መሰረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ አንዱ ለብቻ ብቁ የመምረጫ መስፈርት ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲሁም ቃላቱ ለመማርና ለማስታወስ እንዲመቹ ሁነው መደራጀት ያለባቸው ሲሆን ቀጥሎ ስለ ቃላት ትምህርት አደረጃጀት በተወሰነ መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

## 2.4. የቃላት ትምህርት አደረጃጀት

ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ የሚውሉ የቃላት ትምህርት ይዘቶች መምረጫ መስፈርቱን መሰረት በማድረግ በጥንቃቄ መምርጥ እንዳለባቸው ከላይ ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የተመረጡት ቃላት በመማሪያ መጽሀፍት ዝግጅት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በዕለት ተለት ተግባራቸው ሊጠቀሙባቸው በሚያስችል መልክ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ የቃላት ትምህርትን መምረጡ ብቻ በቂ ውጤት ያስገኛል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ምክንያቱም ቃላቱ በሚገባ እንዲለመዱና በሚፈለግ ጊዜ ያለ ችግር እንዲታወሱ አደረጃጀታቸውም የታቀደ መሆን አለበት (Gairns and Redman, 1986) ብለዋል፡፡

በተጨማሪም Nation (2000:6) ‹‹በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የቋንቋ አሀዶች እድገት ባለው አካሄድ፣ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲማሩ በሚስችላቸው ሁኔታ፣ የቃላት ትምህርት ማስታወስን የሚፈልግ መሆኑን ባገናዘበ መልኩ፣ እንዲሁም በተወሰነ ጊዜ ርቀት በመደጋገምና በተለያዩ አውዶች ለመማር እድል በሚሰጥ መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም Nation (2000) አክለው ስለቃላት ትምህርት አደረጃጀት ሲገልጹ ‹‹ቃላት በቋንቋ ክንውኖች ውስጥ የድግግሞሽ መጠናቸውና እድገታቸውን ጠብቀው መደራጀት አለባቸው›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ Richards (2009) ገለጻ ቃላትን ለትምህርትነት ለማቅረብ አደረጃጀታቸው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅነት እንዲሄዱ ሊደረግ ይገባል፡፡ የቃላት ትምህርቱ በዚህ ሁኔታ የሚደራጁ ከሆነ ተማሪው ላውቀው እችላለሁ የሚል ስሜት ስለሚፈጥርለት የመማር ስሜቱን ከመቀስቀስ አንፃር ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው ይናገራሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት የሙህራን አባባል የምንረዳው የቃላት ትምህርት ለማቅረብ በሚገባ ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ አደረጃጀቱም ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲማሩ በሚስችላቸው ሁኔታ፣ የቃላት ትምህርት ማስታወስን የሚፈልግ መሆኑን ባገናዘበ መልኩ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም አደረጃጀታቸው ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ እያሉ እያደጉ እንዲሄዱ ሊደረግ ይገባል፡፡

አደረጃጀታቸውን በተመለከተ አንበሴ (1993፣38) Laufer (1986)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ቃላት ካላቸው ዝምድና አንጻርና የቃላትን የጋራ ባህሪ መሰረት በማድረግ ማደራጀት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ጽንሰ ሃሳባዊ ዝምድና ያላቸው ቃላት በአንድነት የሚታወሱ እንደሆኑም ይናገራሉ፡፡

በተጨማሪም McCarthy (1990:90) ‹‹ቃላትን በተለያዩ አሃዶች ከፋፍሎ ለማቅረብ በሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ፣ የቅርጽ መመሳሰልና በሚኖራቸው የፍቺ ዝምድና ማደራጀት ይቻላል›› ብለዋል፡፡ እነዚህን ዋና ዋና የማደራጃ መንገዶችን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፡፡

## 2.4.1. ቃላት በሚያወሱት ርዕስ ጉዳይ ማደራጀት (Topic)

ይህንን አስመልክተው Gairns and Redman (1986:89) ሲገልጹ ‹‹በአንድ ርዕስ ጉዳይ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ለአንድ ደረጃ የተመረጡ ቃላት የሚያገናኛቸውን ርዕስ ጉዳይ በመግለፅ እንዲያገለግሉ ከተደረገ በኋላ ቃላቱ በተግባራት መልክ ተደራጅተው ይቀርባሉ›› ብለዋል፡፡

ቃላት በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አደራጅቶ ማቅረብ የራሱ የሆነ ችግር አለው፡፡ ይኸውም ርዕሰ ጉዳይን በተጨባጭ ለማወቅና የትኛው ርዕሰ ጉዳይ ለተማሪ ጠቃሚ እንደሆነ ለመለየት ማስቸገሩ፣ እንዲሁም የርዕሰ ጉዳዩን ምንነት ማወቅ የሚሉትና የመሳሰሉት ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አደራጅቶ የማቅረብ ችግር ቢኖርም ቃላትን አቧድኖ ማቅረብ ጠቃሚ ዘዴ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የቋንቋ ተማሪው ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ሲያስብ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የሚያያዙና የሚጠቀምባቸውን ቃላት ሊያስታውስ ስለሚችል አንድ ላይ መቅረባቸው ጠቀሜታ ይኖረዋል (Alizadeh, 2016) በማለት ያብራራሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ቃላት ከሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ አንፃር ማደራጀቱ ጠቀሜታው ተማሪው ከርእሰ ጉዳዩ ጋር አብረው ሊነሱ የሚችሉ ጉዳዮችን አብሮ ሊስታውሳቸው እንደሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ ስለትምህርት ቤት ሲወሳ መማሪያ ክፍል፣ መምህር፣ ተማሪ፣ መማሪያ መጽሐፍ ወዘተ የሚሉ ቃላት ከርዕስ ጉዳይ ጋር ተያይዘው ይነሳሉ፡፡ የቃላቱ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ከሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ ጋር በመዛመድ አንድ ላይ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህም ቃላቱ በምን ሁኔታ ስራ ላይ እንደሚውሉ ለመለየት ከማስቻሉም በላይ በተወሰነ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ በመሆናቸው በጋራ የመታወስ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

## 2.4.2. ቃላትን በፍቺ ተዛምዶ ማደራጀት (Meaning)

በሁለተኛነት የሚጠቀሰው የቃላት ትምህርት ማደራጃ መንገድ ቃላት ከሚኖራቸው ፍቻዊ ተዛምዶ አንጻር የማደራጀት ሂደት ነው፡፡ ይህንን አስመልክተው አንበሴ (1993፣39) ሲገልጹ ‹‹ቃላትን በፍቺ ተዛምዶ ማደራጀት ሲባል ቃላቱ ከሌሎች ቃላት ጋር በፍቺ መመሳሰል፣ መቃረን ወይም የአንደኛው ቃል ፍቺ በሌላኛው ውስጥ መጠቃለል ምክንያት የሚፈጠረውን ዝምድና ይመለከታል፡፡ ከነዚህ ተዛምዶች አንጻር አንድ ላይ ማቅረቡ በተቀራራቢ ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት በግልጽ ለማወቅ ያስችላል›› ብለዋል፡፡

እንደ Carter and McCarthy (1988:18) ገለጻ ‹‹አንዳንድ ቃላት በርካታ የፍቺ አካባቢዎችን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የሚወክሉትን በቀጥታ ሊጠቁሙ የሚችሉ ጠባብ ፍቺ አላቸው›› በማለት ይናገራሉ። በተጨማሪም Gairns and Redman (1986) ቃልን በሚገባ ለመረዳት ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸው ቃሉ የሚወክለውን ፍቺ ብቻ ሳይሆን ተዛማጅ ፍቺ ካላቸው ቃላት የሚለየውንም ጭምር ነው። ስለሆነም ቃላትን በፍቺ ተዛምዶቸው ለማደራጀት መጀመሪያ ቃላቱ የሚቀርቡበትን ተገቢ አውድ መፍጠር ይኖርብናል። ሁለተኛው የቃላቱን ፍቺ ከአውድ ለመገመት የሚያስችሉ የትንበያ ስልቶችን ከግምት በማስገባት ትምህርቱን ማደራጀት አለብን። ስለዚህ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ቃላትን ማደራጀት ከቻልን ተማሪዎች በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው የቃላትን ፍቺ ከአውድ የመረዳት አቅም እንደሚያዳብሩ ይገልጻሉ።

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው የፍቺ ተዛምዶ የሚለው እሳቤ የአንደኛው ቃል ፍቺ በሌላኛው ውስጥ መጠቃለል ምክንያት የሚፈጠረውን ዝምድና የሚመለከት ሲሆን ዝምድናው በተቃራኒ ወይም በተመሳሳይ ሊሆን እንደሚችል ነው። ቃላትን በፍቺ ተዛምዶቸው ለማደራጀት መጀመሪያ ቃላቱ የሚቀርቡበትን ተገቢ አውድ መፍጠር ያስፈልጋል። እንዲሁም የቃላቱን ፍቺ ከአውዱ በመነሳት እንዲገምቱ በሚያስችል ሁኔታ ትምህርቱን ማደራጀት እንዳለብን እንረዳለን።

### 2.4.3. ቃላትን በቅርጽ ተመሳስሎ ማደራጀት (Form)

ቃላትን በትምህርትነት ለማደራጀት የሚረዳ ሌላው መንገድ ቃላትን በቅርጽ ተመሳስሎ ማደራጀት ነው። ተመሳሳይ ነገሮች በቀላሉ ሊታወሱን እንደሚችሉ ሁሉ ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸው ቃላትም አንድ ላይ ቢቀርቡ የትምህርት ሂደቱ ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል።

እንደ McCarthy (1990:99) ገለጻ ‹‹ቃላትን ለማስተማር ቃላቱ ያላቸውን ውስጣዊ አደረጃጀት ለማየት በሚያስችል አኳኋን ማደራጀት ሌላው የቃላት ማደራጃ ስልት ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላት ለመመስረት በመደበኛነት ጥቂት ቁጥር ያላቸው የአመሰራረት ሂደቶች በጥቅም ላይ ይውላሉ። በመሆኑም የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ የቃላቱን አወቃቀር ስልት ለማሳየት የሚያስችል አደረጃጀት መከተል ተገቢ ነው›› ብለዋል።

በአጠቃላይ እስካሁን በቃላት ትምህርት አደረጃጀት ዙሪያ በሙህራን የተነሱ ሀሳቦች ለማሳየት የተሞከረ ሲሆን ቃላትን በተለያዩ አሃዶች ከፋፍሎ ለማቅረብ በሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ፣ የቅርጽ መመሳሰልና በሚኖራቸው የፍቺ ዝምድና ማደራጀት እንደሚቻል ቀርቧል፡፡ ቃላቱ በሚገባ እንዲለመዱና በሚፈለግ ጊዜ ያለ ችግር እንዲታወሱ አደረጃጀታቸውም የታቀደ መሆን እንዳለበት ተገልጻል፡፡ እንዲሁም እድገታቸውን ጠብቀው ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ እያሉ እያደጉ እንዲሄዱ በማድረግ የቃላት ተግባራቱን አደራጅቶ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

## 2.5. የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች

የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ሲባል በመጽሃፉ ለትምህርትነት የቀረቡት የቃላት መልመጃዎች ወይም ተግባራትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ እንደ Gairns and Redman (1986) ገለጻ ከሁሉ አስቀድሞ ለትምህርት የሚቀርቡ የቃላት ተግባራት በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ሰርፀው በሚገቡበትና በሚታወሱበት አኳኋን መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ የሚቀርቡት ቃላት የተማሪዎችን እድሜ፣ የትምህርት ዳራ፣ የትምህርቱን ዓላማ ወዘተ ያገናዘቡና ቃላቱን ለመጠቀም በሚያስችሉ ስልቶች የዳበሩ የቋንቋ ተግባራትን መሰረት ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ እንዲሁም ምንውየለት (2005፣39) Morgan and Reinlucri (1986:3)ን ጠቅሶ እንደገለጸው፡-

> *‹‹ቃላት አንድ ነጠላ ትርጉም ብቻ ይዘው የምናገኛቸው ብቻ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ፣ በትስስሮሹ ሳቢያም የተለያዩ ቅርፆችና ፍቺዎችን የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ የሚቀርቡት የቃላት ተግባራት ተማሪዎቹ አዳዲሶቹን ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ፣ የማሰብና የመተንበይ ችሎታቸውን እየተጠቀሙ፣ ቅርፃቸውን ከፍቻቸው ጋር ማወቅ በሚችሉበት አኳኋን ሊቀርቡ ይገባል›› በማለት ይናገራሉ፡፡*

በተጨማሪም Jill and Charles (2008፡42) እንደገለጹት ‹‹የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተነጣጠለ ሳይሆን አንዱ ተግባር ቀጥሎ ካለው ጋር የተቆራኘና ደረጃ በደረጃ የተዋቀረ ሊሆን ይገባል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎች የሚቀርቡበት ሁኔታ ላይ የሚያተኩር ሲሆን በመቀጠል ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት መረዳታቸውን የምናረጋግጥበት ሂደት ነው›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ለትምህርት የሚቀርቡት የቃላት ተግባራት የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ በራሳቸው ጥረት ቃሉን እንዲያውቁ የሚገፋፉና ተሳትፎአቸው የሚያጎለብቱ ሁነው ከቀረቡ ቃላቱ አይረሴ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከሙህራኑ ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር የተለያዩ የቃላት ማቅረቢ ዘዴዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ስልቶች መካከልም ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ፣ በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ፣ የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን ተመርኩዞ ማቅረብ፣ ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፣ ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርትን በመዝገብ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ እና የቃላት ትምህርቱን ግልጽ በሆኑ መመሪዎች ማቅረብ የሚሉትን ቀጥሎ ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡

## 2.5.1. ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ

የቃላት ትምህርት አውዳዊ መሆን እንዳለበት የተለያዩ ድርሳናት ያስገነዝባሉ፡፡ ቃላትን በአውድ ስለማቅረብና በአውድ አስደግፎ መማር ስለሚያስገኘው ጥቅም ከማየታችን በፊት አውድ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተከታዩን ገለፃ የተቃና ያደርገዋል፡፡ Nation and Coady (1988:2) አውድ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ‹‹አውድ በአጠቃላይ ገጽታዎች ሊከፋፈልና ሊገለጽ የሚችል ሆኖ በአንድ በተሰጠ ውህድ አሀድ (ፅሁፍ ወይም ንግግር) ውስጥ እንደ ሥነ-ምዕላዳዊ፣ ሥነ አገባባዊና ዲስኩራዊ መረጃ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ የውህድ አሀዱ አንባቢ ወይም አድማጭ ውህድ አሀዱ ስለሚናገረው ጉዳይ የራሱ የሆነ ዳራዊ እውቀት ይኖረዋል›› በማለት ያብራራሉ፡፡ በተጨማሪም Harmer (1991:57) ‹‹አውድ ማለት ቋንቋ በጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚያመቻች የመረጃ ጥንቅር ነው›› በማለት ከላይ ከቀረበው ጋር ተቀራራቢ ብያኔ ይሰጣሉ፡፡

Lewis (1993) በበኩላቸው የአውድን ምንነት ዘርዘር በማድረግ በሁለት መንገድ ይመለከቱታል፡፡ የመጀመሪያው አውድ አንድ ንግግር የፈለቀበትን ሁኔታ የሚያሳይ በመሆኑ ሁኔታዊ አውድ እንለዋለን፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አንድ ንግግር የፈለቀበትን ሥነ ልሳናዊ አካባቢ የሚመለከት በመሆኑ ሥነ ልሳናዊ አውድ ይባላል፡፡ እነዚህ ሁለትም አውዶች ቃላትን መርጦ ሀሣብን በማስተላለፍ ሂደት ላይ የራሳቸው ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው በተለያየ

ሁኔታ የተለያየ ቋንቋ ይጠቀማል፡፡ እንደዚህ እንዲያደርግ የሚያስገድደውም የሚነገርበት አውድ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው አውድ ቃሉ ከሚሰጠው ትርጉም በተለየ መልኩ ሌሎች ከጎኑ በሚቆሙ ቃላት አማካኝነት ትርጉሙ ተወስኖ የሚቀርብበት ሁኔታ ነው፡፡ አውድን ሁኔታዊና ስነ ልሳናዊ በማለት በሁለት የሚከፈል ሲሆን ይህም ንግግሩ የቀረበበትን ሁኔታና የፈለቀበትን ስነ ልሳናዊ አከባቢ የሚያካትት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በጥቅሉ አውድ አንድ ቃል ሊኖሩት ከሚችሉት በርካታ ፍቺዎች ውስጥ በውስን ፍቺዎች ላይ እንዲያነጣጥር ማድረጊያ መንገድ ተደርጎ መታየት ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ቃላትን በአውድ አስደግፎ የማቅረብ አስፈላጊነትና እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል መመልከት ይገባል፡፡ እንደ Jill and Charles (2008፡44) ገለጻ ‹‹አውድ ለቃላት ትምህርት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይኸውም ቃላት ከሥነ ልሳናዊም ሆነ ከሥነ ልቦናዊ እይታ አንፃር ፍቻቸው ግልፅ የሚሆነው በተገቢው አውድ ውስጥ ሲገቡ ብቻ ነው›› በማለት ያብራራሉ፡፡ አንድን ቃል በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ ተማሪዎች በድርጊት እየተሳተፉ በሚማሩበት አውድ ውስጥ ማቅረብ ትምህርቱን እንዳይረሳ ከማድረግ አኳያ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም የቃላት ትምህርት አቀራረብ ቃላትን በገቡበት አውድ መገመት በሚያስችል መንገድ መሆን እንዳለበት (Didrichs, 2005) ያስረዳሉ፡፡

Hunt and Belgar (2002:83) በበኩላቸው ‹‹ተማሪዎች በራሳቸው እንዲጥሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው በመገመት በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላቸዋል›› በማለት ገልጸዋል፡፡ እንደ Curtis and Longo (2001:10) ገለጻ ‹‹ለትምህርትነት የሚመረጡት ቃላት ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ መወሰን የለባቸውም፡፡ ከምንባቡ ውጪም ቃላት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ዋናው ነገር ተገቢ ስነ ልሳናዊና ሁኔታዊ አውድ ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡ ማለትም ቃላት ሌጣቸውን ‹‹ይህ ቃል ምን ማለት ነው›› በሚል ስልት መቅረብ እንደሌለባቸው ይጠቁማሉ፡፡

እንዲሁም Didrichs (2005) ፈሊጣዊ አነጋገሮች የተዋቀሩባቸው ቃላት በተናጥል ከሚያስተላልፉት መልዕክት ውጪ በህብረት የሚይዙት ፍቺ ስላላቸው ሊወሳሰቡ ይችላሉ፡፡ ይህንን ውስብስብነት ለመቀነስ ፈሊጦችን በአውድ አስደግፎ ማቀርብ የተሻለ እንደሚሆን ይገልጻሉ፡፡

ቃላት በአውድ አስደግፎ ከማቅረብ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ቃላቱ የሚገኙባቸው አረፍተ ነገሮች ርዝማኔ ነው። ምክንያቱም ቃላቱ የሚቀርቡባቸው አረፍተ ነገራዊ አውዶች ከመጠን በላይ አጥረው ወይም ረዝመው የቃላቱን ፍቺ ለመገመት የሚያስቸግሩ መሆን የለባቸውም። አረፍተ ነገሮቹ ከአምስት እስከ አስር የሚደርሱ ቃላትን የያዙ ቢሆኑ የቃላትን ፍቺ ለመገመት ያመቻሉ። በአንጻሩ ደግሞ ከአምስት በታች ወይም ከአስር በላይ ቃላት የሚይዙ ከሆኑ የቃላቱ ቁጥር እያነሰ ወይም እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለትንበያ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል (Nation and Coady, 1988) በማለት ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ የቃላትን ትምህርት በአውድ አስደግፎ ማቅረብ በቀላሉ ፍቺውን እንዲረዱ ከማድረግ አንጻር ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ለትምህርትነት የሚመረጡት ቃላት ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ መወሰን እንደሌለባቸው ከምንባቡ ውጪም ሊቀርቡ እንደሚችሉም እንገነዘባለን። እንዲሁም ቃላቱ የሚቀርቡባቸው አረፍተ ነገሮች ርዝማኔ የተስተካከለ ከሆነ ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው በመገመት በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላቸዋል። ስለሆነም ተማሪዎች በቋንቋው ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ አስፈላጊ መሆኑን ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት ይቻላል።

## 2.5.2. ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ

ይህንን አስመልክተው Richards (2009) ሲገልጹ ተማሪዎች የቃላትን ንበት መመሳሰል መሰረት አድርገው ቃላት ቢያከማቹም፣ በትምህርት እየገፉ ሲሄዱ ቃላትን በአእምሮ ሰሌዳቸው ቀርፀው የሚያስቀምጡት በፍቻቸው አማካኝነት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው መነሻነት በማቅረብ እንዲማሩባቸው ማድረግ በቀላሉ ፍቻቸውን እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል ብለዋል።

ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ጽንስ ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶችን በሚሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል። የቃላት ትምህርትን ከፍቺ ተዛምዶ አንጻር አደራጅቶ ማቅረብ የጠለቀ የቃላት እውቀት ለማላበስ ያስችላል። በመሆኑም የተለያዩ የፍቺ ዝምድናዎችን ለማሳየት ቃላትን በከታች ተከታች ግንኙነታቸው፣ አብሮ ተሰላፊነታቸው፣ በተመሳስሏቸውና በተቃርኗቸው ለይቶ ማቅረብ እንደሚቻል (Bauer,1998)

ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን የቃላት የፍቺ ዝምድናዎች ቀጥሎ ባጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 2.5.2.1. ቃላትን በተመሳስሎና በተቃርኖ ፍቻቸው ማቅረብ

በቃላት መካከል በጣም የታወቀው ትስስሮሽ የቃላት በፍቺ መመሳሰልና መቃረን ነው፡፡ ሁለት ቃላት በአንድ በተወሰነ አውድ ገብተው ተመሳሳይ የሆነ ፍቺን ሲያስገኙ ተመሳሳይ ቃላት ሲባሉ፣ በአንፃሩ ሁለት ቃላት በፍቺ ተፃራሪ ሆነው ሲገኙ ተቃራኒ ቃላት ይባላሉ፡፡ በቃላት መካከልም ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ ወይም ተቃርኖ የለም፡፡ ምክንያቱም በማንኛውም አውድ አንዱ ቃል ሌላውን ሊተካ አይችልም፡፡ በርግጥ ቃላት በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት መጠነኛ ባህሪ አላቸው፡፡ ለዚህም የአንዱ ቃል የሰፋ ፅንስ ሀሳብ መያዝ፣ አንዱ በገባበት ሌላው አለመግባት፣ ሰዋሰዋዊ ባህሪቸው መለያየት ወዘተ የሚሉት በምክንያትነት እንደሚጠቀሱ (Allen, 1983) ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Gairns and Redman (1986:23) እንደሚገልጹት ‹‹ሁለት ቃላት ፍጹም በሆነ ተመሳሳይነት ማገልገል የሚችሉ ቢሆን ኖሮ በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት አጠያያቂ ይሆን ነበር›› በማለት ከላይ ያለውን ሀሳብ ያጠናክሩታል፡፡

እንደ Wallace (1988) ገለጻ የቃላትን ፍቺ ለማስተማር ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በማቅረብ ማለማመድ ይቻላል፡፡ የቃላትን ፍቺ በተመሳሳይም ሆነ በተቃራኒ ለማስተማር ሲፈለግ ትምህርቱ አውዳዊ አቀራረብን የተከተለ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ፍቻቸውን ከአውዳቸው ለመተንበይ ያስችላል ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ አውድን መሰረት ያደረጉ የቃላት ተመሳሳያና ተቃራኒ ፍቺን የሚጠይቁ ተግባራት ቀርጾ በማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲማሩባቸው በማድረግ ይቻላል፡፡ ይህም ቃላቱ ያሏቸው የፍቺ ግንኙነት እንዲረዱ ለማድረግ ያመቻል፡፡

### 2.5.2.2. የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት

ከፍቺ አንፃር የቃላት ዝምድና የሚገለፅበት ሌላው መንገድ የቃላት ተዋረዳዊ ቁርኝት ነው፡፡ አንድ ቃል ሰፋ ያለ ፅንስ ሀሳብ በመወከሉ የተነሳ በስሩ በርካታ ቃላትን በፍቺ ሊያቅፍ ይችላል፡፡ ይህንን አስመልክቶ Alizadeh (2016) ሲገልጹ የአንድ ቃል ፍቺ በሌላ ቃል ፍቺ

የሚጠቃለል ሆኖ ሲገኝ ሁለቱ ቃላት ዝምድና የከታችና ተከታች የፍቺ ግንኙነትን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ እንስሳት የሚለውን ቃል ብንወስድ በስሩ ድመት፣ ፍየል፣ ፈረስ፣ ዉሻ፣ ወዘተ የሚሉትን ቃላት ፍቺ ይጠቀልላል፡፡ እነዚህም ቃላት በተራቸው ሌሎች ቃላትን በስራቸው ሊያቅፉ ይችላሉ፡፡ በጥቅሉ እንሳሳት የሚለው ከታች ቃል ሲሆን የቀሩት (ድመት፣ ፍየል፣ ፈረስ፣ ዉሻ) ግን እንስሳት በሚለው ቃል ውስጥ ተከታች እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

እንደ Carter and McCarthy (1988) ገለጻ የከታች ተከታች ቃላት የፍቺ ዝምድ አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው በስሞች መካከል ሲሆን ልክ እንደ ተመሳሳይና ተቃራኒ የቃላት ትምህርት ሁሉ ፍቺን መሰረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ተደራጅቶ ከሚቀርብባቸው ስልቶች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ከታችና ተከታች ቃላትን ባንድ ላይ እያቀረቡ ተማሪዎች የቃላቱን የፍቺ ዝምድና እስከምን ድረስ እንደሆነ እንዲፈተሹ በማድረግ ማስተማር ጠቀሜታ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት ማለት አንድ ቃል ሰፋ ያለ ፅንስ ሀሳብ በመወከሉ የተነሳ በስሩ በርካታ ቃላት ሊያቅፍ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ከታችና ተከታች ቃላትን ባንድ ላይ በማቅረብ ተማሪዎች የቃላቱን የፍቺ ዝምድና እስከምን ድረስ እንደሆነ እንዲፈተሹ በማድረግ ማስተማር ጠቀሜታ እንዳለው ከቀረበው ገለጻ እንረዳለን፡፡ ይህም ከታች ቃልን ሰጥቶ ተማረዎች በስሩ ተከታች ቃላትን ተጠቅመው ንግግር ወይም ፅሁፍ እንዲዘጋጁ የሚጠይቁ ተግባራትን በመቅረፅ ሆነ በሌሎች ስልቶች ሊከናወን ይችላል፡፡

### 2.5.2.3. የቃላት አብሮ ተሰላፊነት

ይህንን አስመልክተው McCarthy (1990) እንደጠቆሙት በቋንቋ ውስጥ በቃላት መካከል ዝምድናን መፍጠሪያ ሌላው መንገድ የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ሲሆን የአንዱ መኖር ለሌላው መኖር ግድ የሚስፈልግና እርስ በርሳቸው በፍቺ የተሳሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ይህ የቃላት ዝምድና አይነት በማንኛውም ቋንቋ የቃላት ጥናት ውስጥ ቃላትን አደራጅቶ ማቅረቢያ ዋና መርህ በመሆን እንደሚያገለግል ይናገራሉ፡፡

በተጨማሪም ምንውየለት (2005፣25) Nattinger (1988)ን በመጥቀስ የቃላት አብሮ ተሰላፊነትን ለመረዳት የሚያስችሉ ሁለት መሰረታዊ ባህሪያት አሉ፡፡ አንደኛው አንድ ቃል አዘውትሮ አብሮት ከሚሰለፈው ሌላ ቃል ጋር በመሆን ሰፊ የፍች ይዘት ማስገኘት መቻሉ ነው፡፡ ይህም አብሮ ተሰላፊ ቃላቱን በትውስታ ማህደር ለማከማቸት የሚረዳ ከመሆኑም በላይ

የአንድ ቃል የፍቺ አካባቢን ለመበየን ያግዛል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ ቃላትን እንዲለዩና ከአንድ ቃል ጋር አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ ሌሎች ቃላት ይኖራሉ የሚል ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያስችላቸዋል በማለት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ Biber et al. (1998) እንደገለፁት የቃላቱ ቁርኝት የቅርብ ወይም የሩቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹ዉሻው ጮኸ›› በሚለው አውድ ‹‹ዉሻው አናፋ›› ማለት ያልተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ዉሻው›› እና ‹‹ጮኸ›› የሚሉት ቃላት ምንም አንኳን ጎን ለጎን ባይቀመጡም የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው ግን መገንዘብ ይቻላል፡፡ አብሮ ተሰላፊ ቃላትን ለማስተማር አንዱን ቃል በአውድ ውስጥ በማቅረብ የሌላውን ቦታ ክፍት ትቶ ተማሪዎች እንዲሞሉት በማድረግ ማለማመድ እንደሚቻል (McCarthy, 1990) ይናገራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ሊያሳዩ የሚችሉ ተግባራት የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ መቅረጽ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ በአረፍተ ነገራዊ አውድ ተገቢውን አብሮ ተሰላፊ ቃል በሌላ ቃል ተክቶ በማቅረብ ተማሪዎች አረፍተ ነገሩን በመመርመርና ተገቢ ያልሆነውን ቃል በመለየት በተገቢ ቃል እንዲተኩ በመጠየቅ፣ እንዲሁም ቃሉን በማቅረብ አብሮ ሊስለፍ የሚችለውን እንዲሞሉ በማድረግ ወዘተ ሊከናወን ይችላል፡፡

## 2.5.3. የቃላትን የእርባታና ምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ

የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታመንበት የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ሌላው ስልት የቃላትን የእርባታና ምስረታ ስርአት በመከተል ማቅረብ ነው (Ur,2006) በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም Jill and Charles (2008፡46) ‹‹በቃላት ላይ የተለያዩ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመጨመር በቋንቋ ውስጥ አዳዲስ ቃላት መፍጠር ይቻላል›› ብለዋል፡፡ እንደ ጌታሁን (1990፣50) ገለጻ ‹‹በአማርኛ ቋንቋ ቅጥያዎች ቃላትን የማርባትና የመመስረት ተግባር አላቸው፡፡ የእርባታ ሂደት የቃሉ መሰረታዊ ባህሪ ሳይለወጥ በቅጥያዎች አማካኝነት የሚደረግ ሂደት ሲሆን በቅጥያ አማካኝነት ከነበሩበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለዋወጡበት ሂደት ደግሞ ምስረታ ይባላል›› በማለት ያብራራሉ፡፡

በተያያዘም ባየ (2000) በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ቃላትን ለማርባትና ለመመስረት የሚስችሉ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቅጥያዎች አሉ፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች በሰዋሰዋዊ ተግባራቸው መነሻነት የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ የእርባታ ቅጥያዎች በቃል አምድ

ላይ እየተቀጠሉ ቃሉን ለመደብ፣ ለቁጥር፣ ለሙያ፣ ለእምርት ወዘተ በማርባት የተለያየ ቅርጽና ተጨማሪ ፍቺ እንዲኖረው የሚያደርጉ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም Gairns and Redman (1986) በቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች ማቅረቡ የቃሉን ትርጉም ለመረዳትም ሆነ አፍልቆ ለመጠቀም እንዲችሉ መሰረት እንደሚጥልላቸው ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም ying (2001) በቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች ማቅረቡ የማያውቁት ቃል ሲገጥማቸው የቃሉን ስነ ምዕላዳዊ አወቃቀር በመመርመር ፍቺውን መገመት እንዲችሉ ፍንጭ እንደሚሰጣቸው ይናገራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የቃላትን የእርባታና ምስረታ ስርአት በመከተል የቃላት ትምህርትን ለተማሪዎች ማቅረብ የቃላቱን ትርጉም ለመረዳትም ሆነ አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችል መሰረት ይጥልላቸዋል፤ በቃላት ላይ የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን በመመስረት የቃላት እውቀታቸውን ማስፋት የሚችሉ መሆኑን እንረዳለን፡፡

## 2.5.4.ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ

ቃላዊ ሀረጎች የሚባሉት በቃላት ቅንጅት የሚፈጠሩ፣ ከአንድ ቃል በላይ የሆኑና አንድ ፍቺን ይዘው የሚከሰቱ ሲሆኑ በመድብለ ቃላትና በስነ አገባብ መሀል የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት ሁለትና ከዚያ በላይ ቃላት በመጣመር የሚመሰርቷቸው በመሆናቸው ከአብሮ ተሰላፊ ቃላት ጋር የሚያመሳስላቸው ገጽታ ቢኖርም የተለያዩ ናቸው (Nattinger and Decarrico, 1992) በማለት ይናገራሉ፡፡

እንዲሁም Larsen (2017) ብዙ የቋንቋ ብቃት ትወራዎች የሚጠቁሙት ቃላት በትውስታ ማህደር የሚቀመጡት ነጠላ ብቻ ሳይሆኑ የሀረግ አካል ሁነው ጭምር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ቃላዊ ሀረጎች በቀላሉ ሊታወሱ ከመቻላቸውም በላይ ተማሪዎች በነጠላ ቃል ላይ ብቻ እንዳያተኩሩና ሀሣባቸውን በዲስኩር መዋቅር ላይ እንዲሳርፉ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸው፣ እንዲሁም በቋንቋው በሚገባ መግባባት እንዲችሉ እገዛ እንደሚያደርግላቸው ገልጸዋል፡፡

እነዚህ ቃላዊ ሀረጎች አስቀድሞ ቅርጽና ተግባራቸው የሚታወቅ በአንድ በተወሰነ ማህበራዊ መስተጋብር አንድ ፍቺን ይዘው የሚከሰቱ ከአንድ ቃል በላይ የሆኑ አውዶች ናቸው። እነሱም ጥምር ቃል፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችና የተለመዱ አገላለጾች (መሸጋገሪያ ቃላት) ሲሆኑ እንደሚከተለው በዝረዝር ቀርበዋል።

### ሀ. ጥምር ቃል

ጌታሁን (1990፣68) ሲገልጹ ‹‹ጥመራ ቃላትን በማጣመር ሌላ አዲስ ቃል የመፍጠር ዘዴ ወይም ስርዓት ነው። የጥምር ቃል አፈጣጠር ሲመረመር በአጣማሪ ምዕላድ አማካይነት ወይም ተጣማሪ ቃላቱን በአንድ ላይ በማሰለፍ /ያለአጣማሪ/ ሊከናወን ይችላል›› በማለት ያስረዳሉ። በተጨማሪም Wallace (1988) ጥምር ስሞችና ጥምር ግሶች የአመሰራረት ሂደታቸውን በመከተል ማቅረብና ተማሪዎች ሂደቱን ተከትለው ጥምር ቃላቱን እንዲመሰርቱ፣ እንዲሁም በአውድ አቅርቦ ጥምር ቃላቱን በሌላ እንዲተኩ፣ እንዲሁም ተማሪዎች ቃላትን በማጣመር አዳዲስ ቃላት እንዲመሰርቱ በማድረግ ማቅረብ እንደሚቻል ይገልጻሉ።

### ለ. ፈሊጣዊ አነጋገሮች

ፈሊጣዊ አነጋገሮች የተለያዩ ነገሮችን ለመግለጽ እንደተራ /ነጠላ/ ቃላት በቀጥተኛ ፍቺ ሳይሆን በተለያየ መንገድ የምንጠቀማቸው ናቸው። ፈሊጣዊ አባባሎችን ምንነት በተመለከተ Lewis (1993:98) ሲገልጹ ‹‹የፈሊጦች ፍቺ ቃሉን ከመሰረቱት ተጣማሪ ቃላት ፍቺ ጋር የማይገናኙ ናቸው›› ይላሉ። እንዲሁም Gairns and Redman (1986:35) ‹‹የፈሊጦች ትርጉም ከተጣመሩት ቃላት ተናጥላዊ ፍቺ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም›› በማለት የLewisን ሃሳብ ያጠናክሩታል።

ፈሊጣዊ ቃላትን ለትምህርት ማቅረብን በተመለከተ Larsen (2017:19) ሲገልጹ ‹‹በፈሊጣዊ አነጋገሮች ውስጥ ተጣምረው የሚገኙ ቃላትን በመነጣጠል ለመፍታት መሞከርና ፍቻቸውን ለመረዳት ማሰብ ብሎም በዚህ መንገድ ለተማሪዎች ማቅረብ የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፍቺ ለማወቅ አያስችልም›› በማለት ይናገራሉ።

እንደ Wallace (1988) ገለጻ ፈሊጦቹ የሚመሳሰሉት በቅርጽ እንጂ በፍቺ አይደለም። በመሆኑም ፈሊጦችን ለማስተማር የተሻለ ዘዴ የተለየ የፍቺ ገጽታዎችን ያገናዘበ ትርጉም ያለው አውድ በመፍጠር ቅርፃቸውን፣ ፍቺቸውንና አጠቃቀማቸውን ግልጽ በማድረግ መከናወን

እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም በቋንቋ ውስጥ ካላቸው የተለየ ባህሪና ከሚሸከሙት የተለየ ፍቺ አንጻር በክፍል ውስጥ አምጥቶ ተማሪዎችን ማለማመድ ተገቢ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም Lewis (1993) ፈሊጦችን በአፈጣጠራቸው ላይ በማተኮር የተገነቡባቸውን ቃላት በመነጣጠል ውስጣዊ አወቃቀራቸውን ለመመርመር በሚስችል አኳኋን ማቅረብም ተገቢ እንደማይሆን ይጠቁማሉ፡፡ ምክንያቱም የፈሊጣዊ ቃላት አገባባዊ ባህሪ ከጥምር ቃላት አገባባዊ ባህሪ የተለየ እንደሆነና ፍቺቸውም ከተጣማሪ ቃላት የተናጥል ፍቺ ሊገኝ እንደማይችል ያስረዳሉ፡፡

እሳካሁን ከቀረቡት የሙህራን ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ፈሊጦች ሁለት ቃላት ለየብቻቸው ሆነው ሲነገሩ ከሚሰጡት ትርጓሜ ውጪ ባንድ ላይ ሲጣመሩ የሚሰጡት የተለየ ሀሣብ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በርግጥ የአማርኛ ፈሊጦች መድብል ብዙውን እጅ የሚይዙት ከጥምረት የተፈጠሩ ቢሆንም በነጠላ ቃል የሚፈጠሩ ፈሊጦች እንዳሉ መዘንጋት የለበትም፡፡ በመሆኑም ፈሊጦችን ለማስተማር የተሻለ ዘዴ የተለየ የፍቺ ገጽታዎችን ያገናዘበ ትርጉም ያለው አውድ በመፍጠር ቅርፃቸውን፣ ፍቺቸውንና አጠቃቀማቸውን ግልጽ በማድረግ መከናወን ይገባዋል፡፡

### ሐ. የተለመዱ አገላለጾች

እንደ Lewis (1993) ገለጻ የተለመዱ አገላለጾች (መሸጋገሪያ ቃላት) በተግባቦት ሂደት ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ሊገልፀው የፈለገውን ጉዳይ አስቀድመው ይጠቁማሉ፡፡ ዋና አገልግሎታቸውም ተግባቦት ስኬታማ ፍሰት እንዲኖረው አድማጭ ወይም አንባቢው፣ ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ሊገልጽ የፈለገውን በፍጥነት መለየት ማስቻል እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም Larsen (2017፡20) ‹‹የተለመዱ አገላለጾችን ለአፍልቆትም ሆነ ለመረዳት በሚስችሉ የተለያዩ መንገዶች ማቅረብ ይቻላል፡፡ ክፍት ቦታ እንዲሞሉ ወይም ቃላቱን እንዲተኩ የሚያደርጉ ተግባራትን በመቅረጽ ማቅረብ፣ እንዲሁም ከንግግርና ከፅህፈት ጋርም በማያያዝ ተማሪዎች ሲጽፉና ሲናገሩ እንዲጠቀሙባቸው የሚስችሉ ተግባራትን መቅረጽ ይቻላል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የተለመዱ አገላለጾች በተግባቦት ሂደት ተናጋሪው ከአድማጩ፣ ፀሀፊው ከአንባቢው ጋር በሚደርገው መስተጋብር ውስጥ የመስተጋብሩን አካሄድ መንገድ የሚሲዙ የቃላት ጥምረቶች ናቸው፡፡ የተለመዱ አገላለጾች (መሸጋገሪያ ቃላት) የሚባሉት ነገር ግን፣ በሌላ አነጋገር፣ በሌላ በኩል፣ ከዚህም ሌላ፣ በዚህ ረገድ፣ ከዚህ አኳያ፣ እንደኛ እምነት፣ ለማጠቃለል ያህል፣ በነገራችን ላይ ወዘተ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ቃላት የጥምርነት ባህሪ ጎልቶ ይታይባቸዋል፡፡

## 2.5.5. ቃላትን ከቋንቋ ክህሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ

እንደ Eyraud (2000:2) ገለጻ አብዛኛው የቃላት እውቀት የሚጨበጠው በክህሎች (በማንበብ፣ በማዳመጥ፣ በመናገርና በመፃፍ) እንደሆነ የገለጹ ሲሆን በተለይ ከንባብ ጋር አጣምሮ ማቅረብ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ እንደሆነ የቀደሙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱ ጠቁመዋል፡፡

ተማሪዎች የተረዷቸውን አዳዲስ ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚጀምሩት የቅበላ ክሂላቸውን ተጠቅመው ባገኙት እውቀት ነው፡፡ የተገነዘቧቸውን ቃላት አፍልቀው መጠቀም ማለት ደግሞ በተለያዩ አውዶች ስልታዊና ፈጠራ በተሞላበት መንገድ መገልገልን ይመለከታል (ሞላ፡2003) በማለት ያብራራሉ፡፡

እንዲሁም Lewis (1993:114) ‹‹ተማሪዎች መግባባት እንዲችሉ በተገቢው ሁኔታ በቃላት ትምህርት መታገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ቃላትን ከሌሎች ክህሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ የመማር ሂደቱን የተቃና ያደርገዋል፡፡ ይህም የተማሪዎች የተግባቦት አቅም መጠኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን እንዲታገዝ ያደርጋል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ Lewis (1993) አክለው ሲገልጹ ተማሪዎች ቃላትን እንዲረዱ ፍቻቸውን አውቀው እንዲጠቀሙ ከተፈለገ ከሌሎች ቃላት ጋር አብረው የሚገኙባቸውን አውድ በማቅረብ እንዲያነቡ ወይም እንዲያዳምጡ ማደረግ ያስፈልጋል፡፡ አንብበው ወይም አዳምጠው የተረዱትን ደግሞ እንዲጽፉና እንዲናገሩ በማድረግ የተግባቦት አቅማቸውን ማጎልበት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Nurellah (2014) እንደገለጹት ቃላትን እያፈለቁ የመጠቀም እውቀትን ለመገንባት የጥያቄና መልስ ስልትን፣ እንዲሁም ያነበቡትንና የሰሙትን እንደገና የመናገር ስልትን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ስልት በቅድሚያ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ያለበትን አንድ ታሪክ በየግላቸው ያነባሉ ወይም ያዳምጣሉ፡፡ በመቀጠል ያነበቡትን ወይም ያዳመጡትን

መልሰው በጥያቄና መልስ መልክ እንዲናገሩ ይደረጋል፡፡ ለጥያቄዎቹ የሚሰጡ መልሶችም አዳዲሶቹን ቃላት እንዲጠቀሙ የሚደርጉና በትረካው የተካተቱ ነጥቦች ጭምቅ ሀሳብ እንዲሆኑ አድርጎ ጥያቄዎቹን መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የሙህራን ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የቃላትን ትምህርት ከክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ የመማር ሂደቱን የተቃና እንደሚያደርገው ነው፡፡ በተለይ ከንባብ ክህል ጋር አጣምሮ ማቅረብ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን የያዙ ውህድ አህዶችን ካነበቡ ወይም ካዳመጡ በኋላ እንደገና እንዲናገሩ ወይም እንዲጽፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን በጥንቃቄ በመቅረጽና በማቅረብ የቃላት ቃላትን ማስተማር  እንደሚቻል እንረዳለን፡፡

## 2.5.6. የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

በመዝገበ ቃላት የተደገፈ የቃላት ትምህርትን በተመለከተ Gairns and Redman (1986፡71) ሲገልጹ ‹‹በመማር ሁኔታ ውስጥ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም የተመለከተ ትምህርት በማንኛውም ቋንቋ መርሀ ትምህርት ዋና አካል መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ተማሪው መምህሩን ወይም ጓደኛውን ጠይቆ መረዳት በማይችልበት ወቅት መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ችግሩን ሊፈታ ይችላል›› ብለዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም Hunt and Belgar (2002:6) ‹‹የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ተማሪዎች የአንድን ቃል የተለያየ ፍቺ እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡ የቃሉን ትክክለኛ ፍቺም ከአውድ እንዲገነዘቡ በማድረግ በኩል ጉልህ ድርሻ አለው›› በማለት ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም Scrivener (1998፡73) በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የቃላት ትምህርትን ማቅረብና ማለማመድ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የጎላ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የቃላት ትምህርትን ማቅረብና ማለማመድ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በመማሪያ መጻህፍ ውስጥ የሚካተተው የቃላት ትምህርት መዝገበ ቃላትን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

በማሳየትና የአጠቃቀም ጥበቡን በማለማመድ ላይ ትኩረት ማድረግ ያለበት መሆኑን ጭምር እንረዳለን፡፡

### 2.5.7. የቃላት ትምህርትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የተለያዩ የቃላት ተግባራት ተዘጋጅተው ለተማሪዎች ሲቀርቡ ሊተገብሩትና ሊለማመዱበት ይችሉ ዘንድ በተብራራ ሁኔታ የሰፈረ መመሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንን አስመልክተው ምንውየለት (2005፣34) Alderson (1995)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ‹‹ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የአመለካከትና የአሰራር (የባህሪ) ለውጥ እንዲያመጡ ከተፈለገ የቋንቋ ተግባራቱን እንዲከናወኑ የሚያዙት መመሪዎች ቋንቋ ነክ ጉዳዮችን የሚያወሱና በማያሻማ ሁኔታ ለልምምድ የሚያበቋቸው ሁነው ሊቀርቡ ይገባል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Eyraud (2000:3) ‹‹ግልፅ ማብራሪያ የታከለባቸው የቃላት ትምህርት ተግባራት ለማዘጋጀት በቃላት ትምህርት ላይ ያተኮሩ ምርምሮችን መቃኘት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የቃላት ትምህርት ተግባራት ግልፅና በተብራራ መመሪያዎች ተደግፈውና አስፈላጊውን ምሳሌ የያዙ ሁነው ሊቀርቡ ይገባል›› በማለት ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የቃላት ተግባራት እንዲከናወኑ የሚያዙት መመሪያዎች ተማሪዎች ሰርተው እውቀት እንዲቀስሙበት ከተፈለገ አቀራረባቸው ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ ትዕዛዙ ተማሪዎች ተረድተው ሊሰሩት ወይም ሊተገብሩት በሚያስችል መልክ መቀረጽ አለበት፡፡ እንዲሁም ከመመሪያው ግልጽነት በተጨማሪ የሚሰጡ ምሳሌዎችም ካሉ ተማሪዎች እንዲሞክሩት መንገድ የሚከፍቱላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.6. የቋንቋ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ ተጣጥሞሽ

መርሃ ትምህርት (Syllabus) ለአንድ የትምህርት አይነት በየክፍል ደረጃው ተመጥነው የሚቀርቡ አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን፣ ይዘቶችን፣ ክንዋኔዎችን፣ የክፍል ጊዜ መጠን፣ ይዘቱን ለማቅረብ አመች ሊሆኑ የሚችሉ ስልተ ትወራዎችን ወይም ስነ-ዘዴዎችን፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ወይም መርጃ መሳሪያዎችን እና የመገምገሚያ ስልቶችን የሚጠቁም ወይም በዝርዝር የሚያስረዳ ሰነድ እንደሆነ Ur (2006) ይገልጻሉ፡፡

እንዲሁም Cunningsworth (1984፡58) ስለ መማሪያ መጽሃፍ ምንነት ሲያስረዱ ‹‹የመማሪያ መጽሃፍ ተማሪው የቋንቋን በራሱ ጥረት ለተፈለገው አላማ እንዲጠቀምበት ወደሚያስችል ደረጃ የሚያደርስ አይነተኛ መሳሪያ ነው›› ብለዋል::

በተጨማሪም ተስፋዬ (1981) የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ፣ እድሜና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተወሰነ ክፍል ደረጃ እንዲያገለግል ተደርጎ የሚዘጋጅ መሳሪያ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

መማሪያ መጽሃፉና መርሃ ትምህርቱ ያላቸውን ተጣጥሞሽ አስመልክተው Dubin and Olishtian (1992) ሲገልጹ የመማሪያ መጽኃፍ ሲዘጋጅ የሚመሰረተው በመርሃ ትምህርቱ አላማ ላይ ነው፡፡ አላማውን ተግባራዊ ማድረግ ካልቻለ ግን በሁለቱ ሰነዶች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ መሆኑን ያመላክታል፡፡ የዚህም ውጤት በትምህርቱ ስኬታማነት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ይናገራሉ፡፡

እንደ Richard (1987፡21) ገለጻ ‹‹መርሃ ትምህርት በተግባር ሊገለጽ የሚችል የመማር ማስተማር ክንውን ማሳያና የስርአተ ትምህርት አካል ሲሆን በተግባር የሚታየውም መገለጫው በሆነው መማሪያ መጽሃፍ አማካኝነት ነው፡፡ ይህም የመርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሃፉ የጠበቀ ግንኙነት መኖር ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ማሳያ ነው›› ይላሉ፡፡

እንዲሁም Dubin and Olishtian (1992፡168) ‹‹የማስተማሪያ መሳሪያዎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች መማሪያ መጽሃፉ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር መጣጣሙን ወይም መስማማቱን ማረጋገጥን እንደዋነኛ ስራቸው አድረገው መውሰድ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም መርሃ ትምህርት ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስለሚጠቁም መማሪያ መጽሃፉ በዚያ ላይ ካልተመሰረተ የመማር ማስተማሩን ሂደት በስርአት ለመምራት ያስቸግራል›› በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከቀረቡት የሙህራን ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው መርሃ ትምህርት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የመማር ማስተማር ክንውን ማሳያ የስርአተ ትምህርት አካል መሆኑ ነው፡፡ በውስጡም ርእስ፣ አላማ፣ ይዘት፣ የክፍለ ጊዜ ብዛት፣ የክህሎት ብቃት፣ የመማር ማስተማር ክንውንና ግምገማን እንዳስፈላጊነቱ አካቶ የሚይዝ ሲሆን ወደተግባር የሚለወጠው ደግሞ

በመማሪያ መጽሃፍ አማካኝነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም መማሪያ መጽሀፍ በመርሃ ትምህርቱ የተዘጋጁትን ይዘቶችና አላማዎች ወደ ተግባር እንዲለወጡ የሚያደርግ የትምህርት መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም መማሪያ መጽሃፉ የመርሃ ትምህርቱን ገጽታ ቁልጭ አድርጎ ሊያሳይ በሚያስችል ሁኔታ ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት እንረዳለን፡፡

## 2.7. የቀደም ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ በፊት በቃላት ላይ ያተኮሩ፣ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ግኙኑነት ያላቸውና ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች ተገኝተዋል፡፡ እነሱም፣ አንበሴ በቀለ (1993)፣ ንጋቱ አሰፋ (2000) ሞላ አጽባሃ (2003)፣ ምንውየለት ደነቀ (2005) እና አፍወርቅ ይስሀቅ (2008) ሲሆኑ ይህ ጥናትም በስም ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

የንጋቱ እና የአፍወርቅ ጥናት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ለመፈተሽ የተደረጉ ጥናቶች ሲሆኑ ንጋቱ አሰፋ (2000) ‹‹በሲዳመኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላት የመማር ብልሃቶች ምርመራ›› በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናታቸው ነው፡፡

የጥናቱ አላማም በሲዳመኛ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት የመማር ብልሃቶች መመርመር ነው፡፡ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶችን መሰረት ያደረገ እንዳልሆነ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም ስለብልሀቶቹ ያላቸው ግንዛቤና የቃላት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን በጥናቱ አመላክተዋል፡፡

አፍወርቅ ይስሀቅ (2008) ደግሞ ‹‹በጋሞ ጎፋ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፊ ፊትና ኢ-አፊ ፊት ተማሪዎች በአማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ትንተና›› በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለ ተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛ ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናታቸው ነው፡፡

አላማው  አፊ ፊትና ኢ-አፊ ፊት ተማሪዎች ቃላት ለመማር የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች መመርመር ነው፡፡ በጥናታቸውም ኢ-አፊፊት ተማሪዎች ከአፊፊቶቹ በተሻለ በርካታ ቃላት የመማር ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ አረጋግጠዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው በቃላት ላይ መሰራታቸው ብቻ ሲሆን በአላማም፣ በተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያም፣ በክፍል ደረጃም፣ በጊዜም ከዚህ ጥናት ጋር የተለያዩ ናቸው፡፡

ሶስተኛው ጥናት አንበሴ በቀለ (1993) ‹‹በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና›› በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ1990 ዓ.ም በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡

በጥናቱም የተገኘው ውጤት በተተኳሪው መጽሀፍ ውስጥ ቃላት በተገቢው መንገድ አለመመረጣቸውንና አለመደራጀታቸውን እንዲሁም አዳዲስ ቃላት በተደጋጋሚ አለመቅረባቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ጥምር ቃላት፣ የቃላት አብሮነት ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርቶች በመማሪያ መጽሃፉ ትኩረት ተሰጥቷቸው የቀረቡ ተግባራት እንደሆኑ በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡

የአንበሴ በቀለ ጥናት በቃላት ላይ ማተኮሩ፣ 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ ላይ መሰራቱ እና በተተኳሪው መጽሃፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብን መፈተሹ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ በተረፈ በክልልም፣ በጊዜም፣ በትኩረት አቅጣጫም ከዚህ ጥናት ጋር የተለያዩ ናቸው፡፡ እንዲሁም የአንበሴ ጥናት የቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ ብቻ ሲያተኩር ይህ ጥናት ደግሞ ለቃላት ትምህርት አመራረጥም አደረጃጀትም ትኩረት የሰጠ በመሆኑ ይለያያሉ፡፡

ሌላው ሞላ አጽበሃ (2003) ዓ.ም ‹‹በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና›› በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ በማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፋቸው ነው፡፡

በጥናቱ የተገኘው ውጤትም መማሪያ መጽሀፉ ለቃላት ትምህርት ተገቢ ትኩረት የሰጠ፣ በተቻለ መጠን ቃላትን በተለያዩ መንገዶች ተጠቅሞ ለማስተማር የሞከረ፣ ይዘቶቹም ተከታታይና ተዋረዳዊ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ መሆናቸውን መረዳት የቻለ ቢሆንም ይዘቶቹ የቴክኒክ ችግር ያለባቸው መሆናቸውን በጥናቱ ጠቁመዋል፡፡ በቃላት ትምህርት መረጣው ተስተማሪነትንና በቅርበት መገኘት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ጥናታቸው ያመላክታል፡፡ አብዛኛው የሚያነሱትን ርእሰ ጉዳይን መሰረት አድርገው እንደተደራጁም አሳይተዋል፡፡ በመማሪያ መጽሃፉ ግማሽ ያህሉ የቃላት ትምህርት አውድን መሰረት ያላደረጉ መሆናቸውን በጥናቱ ውጤት አረጋግጠዋል፡፡

የሞላ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም በ8ኛ ክፍል ላይ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውና የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መተንተን ዓላማ ማድረጋቸው ከርዕስም ከአላማም አንጻር ተመሳስሎ ይታይባቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት የቃላት ትምህርት ይዘት አስመልክቶ ተተኳሪው መጽሃፍ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተጣጥሞሽ የሚፈትሽ በሆኑ ይለያያሉ፡፡ በተጨማሪም የሞላ ጥናት አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ታስቦ በ1991 ዓ.ም በተዘጋጀው መማሪያ መጽሀፍ ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ደግሞ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ታስቦ በ2007 ዓ.ም በተዘጋጀው ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከጊዜ አንጻርም ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡

የመጨረሻው የምንውየለት ደነቀው (2005) ‹‹በአማራ ክልል በስራ ላይ የዋሉት የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ›› በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክለር ትምህርት ክፍል ለ ተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናታቸው ነው፡፡

በጥናቱ ግኝትም በመስኩ ምሁራን ከተሰነዘሩት መስፈርቶች ሁለቱን ብቻ ማለትም ተስተማሪነትና በቅርበት የመገኘት መስፍርትን መሰረት በማድረግ መጽሀፉ የተደራጀ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን የድግግሞሽን መጠን፣ የተማሪዎች አቅምና ደረጃ፣ የፍቺ ሽፋንን ወዘተ የሚሉትን መስፈርቶች የዘነጋ ወይም ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ ቀርቧል፡፡ ይህም

በመጽሀፎቹ ቃላት ትምህርት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደረ በጥናቱ የተደረሰበት መሆኑን አመልክቷል፡፡

የምንውየለት ጥናት በቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ ላይ መሰራቱና የ8ኛ ክፍል መጽሀፍ አንዱ የትኩረት አቅጣጫው መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ ነገር ግን የምንውየለት ጥናት በአማራ ክልል በ1997 ዓ.ም ታትመው በስራ ላይ የዋሉት የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የተሰራ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ላይ የተሰራ መሆኑ በክልልም በጊዜም የተለያዩ ያድርጋቸዋል፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተገለጹት ልዩነቶች በተጨማሪ ለየት የሚያደርገው መማሪያ መጽሃፉ በአዲስ አቀራረብ የተዘጋጀ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቀደመት መጽሃፎች ያልታዩ የይዘቶች አደረጃጀት ተካተው የተገኙበት መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም የቃላት ጥናት፣ አንብቦ መረዳት፣ ቃላት፣ መጻፍ፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ቃላዊ ክፍሎች (ማድመጥና መናገር) እና ሰዋሰው ራሳቸውን ችለውና ተለይተው የቀረቡ በመሆኑ ከላይ በተገለጹት ጥናቶች ላይ የታዩ ችግሮች የተሻሻሉ መሆን አለመሆናቸውን ለመፈተሽም በማሰብ ጭምር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ  በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው። ይህንን አላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ ቅይጥ ምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ የተጠና ሲሆን በአቀራረቡ ገላጭ ምርምር ስልትን ተከትሏል። በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች ከመምረጫ፣ ከማደራጃና ከማቅረቢያ መንገዶች አንጻር ምን እንደሚመስሉ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል። ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በገለፃ (Descriptive) አጻጻፍ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል።

## 3.2. ጥናቱ መረጃ ምንጮች

የተተኳሪውን መማሪያ መጽሃፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ዋነኛ አላማው ሲሆን በተጨማሪም መማሪያ መጽሀፍ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸው የቃላት ትምህርት ይዘት ተጣጥሞሽ ይቃኛል። በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍና መርሃ ትምህርቱ በመረጃ ምንጭነት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

ክልሉ ሊመረጥ የቻለበት ምክንያት አጥኚዋ ለአስራ ሰባት ዓመት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ክልል በስራ ላይ የቆየችና አሁንም እያገለገለች ያለች በመሆኑ ነው። የክፍል ደረጃው የተመረጠው ለስድስት ዓመት 8ኛ ክፍል ላይ ተመድባ ስታስተምር የቆየች ሲሆን በተጨማሪም በዚህ ክፍል ደረጃ ቀድሞ ስታስተምርበት የነበረው መማሪያ መጽሃፍ የቃላት ትምህርት ይዘት በተወሰነ ነጥብ ላይ የሚያተኩር፣ እንዲሁም በአብዛኛው በአውድ ያልተደገፈ ይመስላት ስለነበር አዲሱ ተተኳሪው የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሃፍ በምን መልክ ተዘጋጅቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ በማሰብ ጭምር የክፍል ደረጃው ሊመረጥ ችሏል።

## 3.3. መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ያሉት የቃላት ትምህርቶች አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም አላማው ነው፡፡ በተጨማሪም መማሪያ መጽሀፍ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸው የቃላት ትምህርት ይዘት ተጣጥሞሽ የሚቃኝ ስለሆነ ሰነድ ፍተሻ (Document Analysis) የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ከነዚህ ሁለት ሰነዶች መረጃ ለማግኘት የሰነድ ፍተሻን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅማለች፡፡ ስለሆነም በተተኳሪው መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት መምረጫ፣ ማደራጃና ማቅረቢያ ስልቶችን መሰረት አድርገው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን ለመለየት የሰነድ ፍተሻ ተድርጓል፡፡ በሰነድ ፍተሻው የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ጥቅም ላይ የዋለው ቅይጥ ምርምር ዘዴ ነው፡፡ ቅይጥ ምርምር ዘዴ (Mixed Research Method) የጥናቱን መነሻ መሰረት በማድረግ የሚመረጥና ሁለቱን ማለትም አይነታዊና መጠናዊን በአንድ ቀይጦ የመጠቀም ሂደት እንደሆነ (Creswell, 2012) ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ምን እንደሚመስሉ በሰነድ ፍተሻ ያገኛቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ በገለፃ (Descriptive) አጻጻፍ ስልት ተተንትነው በመቅረባቸው አይነታዊ የምርምር ዘዴ (Qualitative Research Method) በዋናነት ሊመረጥ ችሏል፡፡ በተጨማሪም መረጃዎቹ በሰንጠረዥ ቀርበው በቁጥርና በመቶኛ ስለተገለጹ በአጋዥነት መጠናዊ የምርምር ዘዴ (Quanitative Research Method) በጥምረት በጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን ገምግማ ገላጭ ስልትን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የቃላት ትምህርት ተግባራት ቆጠራም ተካሂዷል፡፡ ቆጠራውም የተካሄደው የቃላት ትምህርቶቹን አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ለማወቅ ሲሆን ከቀረቡት መስፈርቶች አንፃር ምን ያህል ተመርጠውና ተደራጅተው እንደቀረቡ በየመስፈርቶቹ የቃላት ተግባራት ቆጠራ በማካሄድ በሰንጠረዥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተገኙ መረጃዎች በአስረጅነት እየተወሰዱ ተተንትነዋል፡፡ የመማሪያ መጽሀፉና የመርሀ ትምህርቱ የቃላት ትምህርት ይዘት ተጣጥሞሽ በመቃኘት ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1. የጥናቱ ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተተኳሪውን መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መገምገም ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ በሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች በገላጭ ስልት እየተነተኑ የተገኘውን ውጤት ከነማብራሪያው በዚህ ምዕራፍ ስር ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 4.1.1.የተተኳሪው መጽሀፍ አጭር ቅኝት

ይህ የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ በ2015 ዓ.ም የታተመ ሲሆን መማሪያ መጽሃፉ በፊት ገጽ ሽፋኑ ላይ በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ምዕራብ/ኢ/ህ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ የተስማማ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ተማሪዎች ወደ ዋናው የትምህርት ክፍሎች ከመግባታቸው በፊት በመግቢያው ላይ የስርዐተ ትምህርቱ መሰረታዊ መርሆዎች፣ ከትምህርት ቤት ውጪ የተማሪዎችና የወላጆች ትምህርታዊ ተግባራት፣ እንዲሁም የመጽሃፉን የይዘት አደረጃጀት በማስተዋወቅ ይጀምራል፡፡

መማሪያ መጽሃፉ 134 ገጾች ያሉት ሲሆን 10 ዋና ማስተማሪያ ምንባቦችን በአስር ምእራፎች በመከፋፈል አቅርቧል፡፡ እያንዳዱ ምእራፍ በሶስት ሳምንት፣ አንዱ ሳምንት ደግሞ በሶስት ቀናት ተከፋፍሎ በጠቅላላው በዘጠኝ ቀናት እንዲቀርቡ የተደረጉ ምራፎች ማለትም ምዕራፍ አንድ፤አምስት፤ስድስት፤ሰባት፤ስምንት፤ዘጠኝ ሲሆኑ ከዚህ ዉጪ ያሉት ደግሞ በአራት ሳምንት በአስራሁለት ቀናት እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ መማሪያ መጽሃፉ በአመት ውስጥ በሰላሳ አራት ሳምንትና መቶ ሁለት ቀናት ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ በውስጡ ስድስት ዋና ዋና የቋንቋ ይዘቶችን ከፋፍሎ የያዘ ሲሆን የተለያዩ የቋንቋ ተግባራት በስራቸው ተካተዋል፡፡ ይዘቶቹም ቃላት፣ አንብቦ መረዳት፣ መጻፍ፣ ማድመጥ፣ መናገርና ሰዋሰው ናቸው፡፡ እንዲሁም በመማሪያ መጽሃፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ

የተለያዩ የቃላት ፍቺን የሚያሳዩ ሙዳዬ ቃላት፣ ዋቢዎች፣የአማረኛ የፊደል ገበታ እንዲሁም የኢትዮጲያ ቁጥሮች ተካተውበታል፡፡

በመማሪያ መጽሃፉ ለትምህርትነት የቀረቡ 616 የቋንቋ ተግባራት ሲኖሩት ከነዚህም ውስጥ 233ቱ ቃላትን የሚመለከቱ እንደሆኑ በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በየምዕራፉ ያሉ አጠቃላይ የቋንቋ እና ቃላትን የሚመለከቱ ተግባራት በመለየት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡ በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ የቋንቋ ተግባራትና ቃላትን የሚመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ**

| ምዕራፍ | አጠቃላይ በመጸሃፉ የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ተግባራት ብዛት | በመጸሃፉ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ተግባራት ብዛት | የቃላት ትምህርት ተግባራት በመቶኛ ሲሰላ |
|---|---|---|---|
| 1 | 46 | 14 | 30.43 |
| 2 | 52 | 16 | 30.77 |
| 3 | 62 | 40 | 64.52 |
| 4 | 51 | 17 | 33.33 |
| 5 | 44 | 17 | 38.64 |
| 6 | 46 | 13 | 28.26 |
| 7 | 92 | 56 | 60.87 |
| 8 | 99 | 25 | 25.25 |
| 9 | 76 | 21 | 27.63 |
| 10 | 48 | 14 | 29.17 |
| ጠቅላላ ድምር | 616 | 233 | 37.82 |

ከላይ በሰንጠረዥ1 የቀረቡት አጠቃላይ በየምዕራፉ ያሉ የቋንቋ እና ቃላትን የሚመለከቱ ተግባራት ማሳያ ሲሆኑ በመማሪያ መጽሀፉ ወስጥ ተግባራቱ በስድስቱም ይዘቶች (በአንብቦ መረዳት፣ በመፃፍ፣ በማድመጥ፣ በመናገር፣ በሰዋሰውና በቃላት) ስር ተካተው እናገኛለን፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ትምህርት በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምክንያቱም በተግባቦት ሂደት ተማሪዎች አላማቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ድርጊታቸውንና ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ ለሌሎች ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል የቃላት እውቀታቸው ቁልፍ ሚና አለው (McCrostie, 2007፡5)፡: እንዲሁም Pikulski and

Templeton (2004:36) ቃላት እለት ተለት በምናደርገው አጠቃላይ መስተጋብር ማለትም ሀሳብ መለዋወጥን፣ መልዕክት ማስተላለፍን፣ ጥያቄ ማቅረብንና የመሳሰሉትን ነገሮች ለማሳካት የምንጠቀምባቸው ሁለገብ የቋንቋ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም በመናገር፣ በማድመጥ፣ በማንበብና በመጻፍ ለመግባባት ቃላት ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል።

ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ከጠቅላላው 616 የቋንቋ ተግባራት ውስጥ 233 (37.82%) ቃላትን የሚመለከቱ መሆናቸው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ የተግባራት ክንውን መጠን አኳያ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው የቃላት ትምህርት እንደሆነ እንረዳለን። ይህም ለቃላት ትምህርት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ያሳያል። እንዲሁም መማሪያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት ራሱን አስችሎ በይዘትነት ለብቻ ማቅረቡ በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው።

በተጨማሪም በመማሪያ መጽሃፉ በሁሉም ምዕራፎች በቅድመ ምንባብ ላይ ልክ እንደ ማነቃቂያ በቃላት ትምህርት ይጀምራል። ማለትም በቀረቡት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን፣ ቅጥያዎችንና ዋና ቃላትን በመነጣጠል እንዲሁም በማጣመር በተገቢው ሁኔታ እንዲያነቡ ውይም እንዲጽፉ በማድረግና ውስብስብ መዋቅር ያላቸውን ቃላት እንዲያነቡ በማድረግ እንደሚጀምር ለማረጋገጥ ተችሏል። እንዚህም ቃላት ለማስተማሪያነት ከቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ በቅድመ ምንባብ ጥያቄነት ተካተው እናገኛለን። ይህም የቃላት ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በጣም አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት መማሪያ መጽሃፉ ለቃላት ትምህርት ቅድሚያ ትኩረት እንደተሰጠ ያሳያል።

## 4.1.2. የቃላት ትምህርት አመራረጥን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ለትምህርትነት የሚውሉ ቃላትን ለመምረጥ የተለያዩ መምረጫ መስፈርቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን እንዳለበት ከነዚህም መስፈርቶች መካከል የቃላት ድግግሞሽ መጠን፣ የተማሪዎች ፍላጎትና የብስለት ደረጃ፣ ተስተማሪነት፣ የፍቺ ሽፋንና በቅርበት መገኘት ወዘተ የሚሉትን ከግምት በማስገባት መምረጥ እንደሚቻል (Gairns and Redman,1986 and McCarthy, 1990) ገልጸዋል። ከዚህ አንጻር በመማሪያ መጽሃፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች የተመረጡበት መስፍርት ለመለየትና ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል። በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሃፉ ለማስተማሪያነት የቀረቡት ቃላት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 2፡ መጽሃፉ የተካተቱ የቃላት ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | የቃላት ተግባራት አይነት | ተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ለማስተማሪያ ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ አውድን መሰረት አድርገው የወጡ የቃላት ተግባራት | 50 | 21.46 |
| 2 | ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች | 16 | 6.87 |
| 3 | ተዘውታሪና ኢተዘውታሪ ቃላት | 25 | 10.73 |
| 4 | የቃላት ርባታ ስርአትን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ የቃላት ተግባራት | 17 | 7.29 |
| 5 | ወስብስብ ቃላትን የተመለከቱ የቃላት ተግባራት | 8 | 3.43 |
| 6 | የቃላትእማራዊ እና ፍካራዊ ፍቺ | 11 | 4.72 |
| 7 | አያያዥ ቃላት(መሸጋገሪያ ቃላት) | 15 | 6.44 |
| 8 | የቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺ | 51 | 21.89 |
| 9 | ጥምር ቃላት | 7 | 3 |
| 10 | መዝገበ ቃላት | 27 | 11.59 |
| 11 | ዘይቤያዊ ቃላት | 6 | 2.58 |
| ድምር | | 233 | 100 |

ከላይ ከቀረበው አስረጅ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛው ለማስተማሪያነት የቀረቡት የቃላት ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ ከተካተቱት 20 ምንባቦች የተውጣጡ ናቸው፡፡ በእያንዳዱ ምዕራፍ ስር ሁለት ዋና ዋና ምንባቦች አሉ፡፡ ከነዚህ ምንባቦች የሚወጡት ቃላት ሙያውን ወይም ርዕሰ ጉዳዩን መሰረት ያደረጉና ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ስለመሆናቸው ከርእሳቸው መረዳት ይቻላል፡፡ የሁሉም ምንባቦች አውደ ርዕስ በመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች ስር ሰፍሮ ስለሚገኙ አባሪ ሁለትን ይመልከቱ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት የቃላት ተግባራት 50(21.46%) ምንባቦችን መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል፡፡

ለአብነት ያህል በምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበውን የአውራምባ ማህበረሰብና መገለጫዉ ፤ሰውለስራ ምንባቦች ለማስተማሪያነት ቀርበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር ከቀረቡት 14 የቃላት ተግባራት 14ቱም ምንባቦቹን መሰርት ያደረጉ ናቸው፡፡

*አስረጅ 1*

***ተግባር አንድ፡ ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበዋል፡፡ በአረፍተነገር ውስጥ በማስገባት አውዳዊ ፍቻቸዉ አመልክቱ፡፡***

ሀ.ባተለ          መ.መና

ለ. ማነቆ          ሠ. ማሰላሰል

ሐ.መጎናጸፍ          ረ. እዉን          (ገጽ፣ 9)

ከላይ በአስረጅነት የተጠቀሰው ተግባር ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ያዛል፡፡ ሁሉም ቃላት በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸዉ፡፡

ለትምህርትነት የሚቀርቡት ቃላት ከተማሪዎች የህይወት ልምድ ጋር የማይገናኙ ከሆነ እና አገባባዊ ባህሪያቸው ውስብስብ ከሆነ የተስተዋይነት ደረጃቸው ዝቅተኛ እንደሚሆን (McCarthy, 1990) ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ተዘውታሪ ቃላት ለማንኛውም ቋንቋ እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ፣ የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ እነዚህን ቃላት አስቀድሞ ማስተማር ጠቃሚ እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ኢተዘውታሪ የቃላት ጥያቄዎች ከተማሪው ባህልና ማህበራዊ ዳራ አንጻር ታስበው አልወጡም፡፡እነዚህም ኢተዘውታሪ ቃላት በአራተኛው እና በዘጠነኛው ምዕራፍ ሲገኙ ምንባቡን መሰረት ያደረጉ አይደሉም ይሁንእንጂ በምዕራፍ ሦስት ላይ ኢተዘውታሪ(አዳዲስ ቃላት) ሆነው ምንባቡን መሰረትአድርገውእንደተቀመጡ ግልጽ ነው፡፡ እንዲሁም የተስተማሪነት ደረጃቸው ማለትም ክብደትና ቅለታቸው ተፈትሾ እንዳልተዘጋጁ ማሳያ ነው፡፡

በርግጥ የመማሪያ መጽሃፉን አዘጋጆችን አግኝቶ በምን መስፈርት እንዳዘጋጁት መጠየቅና ማወቅ ባይቻልም በምንባቡ ውስጥ ብቻ በመገኘታቸው ለትምህርትነት እንደቀረቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ቃል ሰፊ አገልግሎት ሽፋንና ስርጪት ባይኖረውም እንኳን ለቋንቋ

ማስተማሪያነት በሚቀርበው ምንባብ ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት በቅርበት መገኘት መስፍርት ነው። ይህም ሌሎች መስፍርቶች ታሳቢ እንዳልተደረጉ መረጃው ያሳያል።

መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የሚካተቱት የቃላት ትምህርቶች መረጣ መርሃ ትምህረቱን በመመርኮዝ የቋንቋ ሳይንስን መሰረት ባደረጉ መስፈርቶች አማካኝነት መከናወን እንደሚገባው ይታመናል። ስለሆነም ሌሎች መስፍርቶችን ከግምት አስገብቶ የቃላት መረጣውን ከማድረግ አንጻር ይቀረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ Curtis and Longo (2001:10) ለትምህርት የሚመረጡት ቃላት ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ መወሰን እንደሌለባቸው ገልጸዋል። ይህም ከምንባቡ ውጪም ቃላት ሊቀርቡ እንደሚችሉ፣ ዋናው ነገር ተገቢ ስነ ልሳናዊና ሁኔታዊ አውድ ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ ጠቋሚ ነው።

### *አስረጅ 2*

***ተግባር አንድ፡- በቀረበው ምንባብ መሰረት በ "ሀ" አምድ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸዉን በ "ለ" አምድ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።***

| "ሀ" | "ለ" | |
|---|---|---|
| 1. መባከን | ሀ. መሰናክል | |
| 2. እጽብ ድንቅ | ለ. ወጣት | |
| 3. መደመም | ሐ. መልፋት | |
| 4. ማጋበስ | መ. መሰብሰብ | |
| 5. ጉብዝና | ሠ. ወጣ ያለ | |
| 6. አረጋዊ | ረ. መደነቅ | |
| 7. አፈንጋጭ | ሰ. አስገራሚ | |
| 8. እንቅፋት | ሸ. ወጣትነት | |
| | ቀ.የድመ ባለጸጋ | ገፅ (9 ) |

ከላይ በአስረጅ 1 እና 2 ላይ የቀረቡት የቃላት ክንውኖች ከአንድ ምንባብ የተዘጋጁ ሲሆኑ ሁለቱም ፍቺን ከማስተማር አንጻር ቀርበዋል።ይህም በተመሳሳይ በዚህ መልክ በመማሪያ መጽሃፉ የተካተቱ ሌሎች ተግባራት እናገኛለን። አስረጅ 5 እና 27 በድግግሞሽ የቀረቡ ናቸው።

በርግጥ የቋንቋ መማሪያ መጽሃፎች በተቀየሩና በተሻሻሉ ቁጥር የዘመን መንፈስ እንደሚያርፍባቸውና ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ትኩረት አድርገው እንደሚያወሱ ይታወቃል፡፡ ጽሁፎቹ የሚቀርቡበት ዋናው አላማ ግን ቋንቋን ለማሰተማር ታስቦ የተዘጋጁ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በስነ ጽሁፍ መልክ የተዘጋጁ ጽሁፎች ብቻ ለማስተሪያነት ይመረጡ ሳይሆን ቋንቋን ለማስተማር በሚመች መልክ እያዋዙ የሚያቀርቡ የተለያዩ ጽሁፎችን፣ መጣጥፎችን፣ ወጎችን፣ ግለ ታሪኮችን፣ የተማሪውን ባህልና ወግ መሰረት ያደረጉ ጽሁፎችን ወዘተ ለማስተማሪያነት እንዲውሉ አድርጎ መምረጥ ቢቻል ችግሮችን ማስወገድ ይቻላል፡፡

ሌላው የቃላት እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺን፣ የቃላት ጥመራን፣ የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነትን፣ የፈሊጦችን ፍቺ ወዘተ ታሳቢ አድርጎ በመምረጥ ለትምህርትነት ማቅረብ እንደሚገባ (Wallace, 1988) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ የቃላት እማሬያዊ ፍካሬያዊ ፍቺ ለማሳወቅ፣ ከአንድ ቃል ጋር አብረው ሊሰለፉ የሚችሉ ቃላዊ ሀረጎች ማለትም ጥምር ቃላት፣ በጥመራ የሚፈጠሩ ፈሊጦች፥ የተለመዱ አገላለፃች (መሸጋገሪያ ቃላት) ትኩረት እንደተሰጣቸው ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡ ነገርግን የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነትን ለማስተማር የሚሉት ጉዳዮች በይዘት መረጣው እንዳልተካተተ ማወቅ ትችላለህ ይህም መማሪያ መጽሃፉ በዚህ ረገድ ያለበትን ድክመት ያሳያል፡፡

በመማሪያ መጽሃፉ የቀረቡት አብዛኞቹ ቃላት በማስተማሪያ ምንባቦች ላይ የተመረኮዙ ሲሆኑ የተማሪዎችን ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ ከማገናዘብ፣ ተዘውታሪ ሁነው የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ ታስበው እንዳልተመረጡ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የቃላት ተግባራቱ ተዘውታሪነታቸው በድግግሞሽ ጥናት ተለይቶ፣ የቃላቱን የፍቺ ሽፋን የማወቅና የስርጪት ባህሪያቸውን የመለየት ስራ ተሰርቶ፣ የተማሪዎች ፍላጎት ላይ ዳሰሳ ጥናት አካሂዶ ከመምረጥ አንጻር ይቀረዋል፡፡

### 4.1.3. የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ተገቢ የሆኑ የቃላት መምረጫ መስፈርቶችን በመጠቀም ለአንድ ደረጃ እንዲመጥኑ ታስበው የተመረጡ ቃላት በአንድ ላይ ለማደራጀትና በተግባራት መልክ ለመንደፍ የሚያስችሉ የተለያዩ

የማደራጃ ስልቶች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ በፍቺ ተዛምዶና በቅርጽ ተመሳስሎ የሚሉትን መሰረት በማድረግ ማደራጀት እንደሚቻል በዋናነት ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም እንደ አስፈላጊነቱ በአያያዥነታቸው፣ በድርብ ቃልነታቸው፣ በፈሊጥነታቸው ወዘተ ማደራጀት ለቃላት ትምህርት ስኬት ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ተገልጿል፡፡

ከዚህ አንጻር በመማሪያ መጽሃፉ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች እንዴት እንደተደራጁ ለመመርመር የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ አደረጃጀታቸውም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ**

| ተ.ቁ | ተግባራቱ የተደራጁበት ሁኔታ | ተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ከፍቺ ተዛምዶ አንጻር የተደራጁ | 51 | 75 |
| 2 | ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳያ አንጻር የተደራጁ | 0 | 0 |
| 3 | ቅርጽን መሰረት አድርገው የተደራጁ | 17 | 25 |
| ጠቅላላ ድምር | | 68 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ 3 ላይ እንደምንመለከተው ቅርጽን መሰረት አድርገው የተደራጁት 17 (25%) የቃላት ተግባራት እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ ተግባራት ቃላትን በተለያየ ቅረጽ ማራባትን የተመለከቱ፣ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን መመስረት እና ነጠላስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር መለወጥን የተመለከቱ ተግባራት በዚህ ስር ተካተዋል፡፡ በመሆኑም ቅርጽን መሰረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር ሁለተኛ ደረጃ በመያዙ ትኩረት እንደተሰጠው ያሳያል፡፡ አባሪ አንድ አስረጅ 9፣ 10 እና 16 በዚህ መልክ የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት አስረጅዎች በቅርጽ ስር እንዲደራጁ ያስቻላቸው የተለያዩ ቅጥያዎችን ማስቀጠል መቻላቸው፣ በቅጥያዎች አማካኝነት ነጠላ ቁጥሮች ወደብዙ ቁጥርመለወጣቸው እንዲሁም አዳዲስ ቃላት መመስረታቸው ነው፡፡

ፍቺን መሰረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር ደግሞ 51 (75%) ተግባራት የቀረቡ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ ትኩረት እንደተሰጣቸው መረጃው ያመላክታል፡፡ እነዚህ የቃላት ትምህርቶች መሰረት

ያደረጉት የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን የተመለከቱ፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ የተተወ ባዶ ቦታ ተገቢ ፍቺ ባለው ቃል ማሟላትና መተካትን የተመለከቱ፣ በአርፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺ መስጠትን የተመለከቱ፣ ከፍቺ አንጻር አብሮ ተሰላፊ ቃላትን ማሟላት የተመለከቱ ወዘተ የሚሉት በዚህ ስር ተካተዋል፡፡ አባሪ አንድ አስረጅ 4፥6፣7 ፣ 8፣ 9፣ 11፥ 12፥19፣ 20፣ 22፣ 23፥ 24፥ 26፥ 30 እና 32 ለዚህ ማሳያ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ፍቺን መሰረት ያድርጉ እንጂ አብዛኞቹ ለማስተማሪያነት ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ በመገኘታቸው የተደራጁ ናቸው፡፡

ሌላው ቃላትን በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት የተመለከተ 0 (0%) ተግባራት በዚህ ስር አልቀረቡም ፡፡ ቃላትን በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት ተማሪው ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ሲያስብ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የሚያያዙ ቃላትን ሊያስታውስ ስለሚችል አንድ ላይ መቅረባቸው ጠቀሜታ እንዳለው በምዕራፍ ሁለት 2.4 ላይ ተገልጿል፡፡በመሆኑም ከዚህ አንጻር የተደራጁ ተግባራት ባለመኖሩ ትኩረት እንዳልተሰጠው መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑምበነዚህ ዙሪያ የተደራጁ አንድም የቃላት ተግባራት እንደሌሉ በመረጣው ላይ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መጽሃፉ እነዚህን የቃላት ተግባራት በይዘትነት አደራጅቶና ተግባር ቀርጾ ከማቅረብ አንጻር ድክመት ይታይበታል፡፡

ሌላው የቃላት ትምህርት አደረጃጃት የመማር እድገቱን የጠበቀና ትርጉም ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ ይኸውም አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ከሚደጋገሙ ወደ ዝቅተኛ ሁኔታ ወደ ሚደጋገሙ ቀስ በቀስ እያደጉ የሚሄዱ መሆን ይኖርባቸዋል (Richards, 2009) በማለት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር መማሪያ መጽሃፉን ሲታይ ከቃላት ንበት ጀምሮ የቃላትን ፍቺ እስከማሳወቅ፤ ብሎም በፍቻቸው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ የሚያድረጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ በቀስ እያደጉ የሚሄዱ እንደሆኑ በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## *አስረጅ 3*

***መልመጃ አንድ፡ ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ አውድ መሰረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡***

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. ጓዳ | ለ. እማወራ | ሐ. አባወራ | መ. ማበርከት | ሠ.ዝና |
| ረ. መጠለል | ሰ. ባልትና | ሸ. ሙልሙል | | (ገጽ፣ 21) |

*አስረጅ 4*

*መልመጃ ሁለት፡- ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ተጠቅማችሁ አረፍተነገር ስሩ።*

1.ባህል 2.ጠላት 3.ንዋይ 4.አሸን 5.አዛውንት 6.ፋይዳ 7.ሀሴት 8.ሙስና 9.ዋና 10.አባይ ገፅ 97.

ከላይ በአስረጅ 3 ላይ የሚገኘው ተግባር ከምዕራፍ ሁለት የተወሰደ ሲሆን በምንባቡ መሰረት ለቃላቱ ተቃራኒ ፍቺ ብቻ እንዲሰጡ ያዛል፡፡ በአስረጅ 4 ላይ ያለው ግን አውዳዊ ፍቺ ተጠቅመው አረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ ሰለሚያደርግ ከላይኛው አንጻር ሲታይ ጠጠር ይላል፡፡ በተመሳሳይ በዚህ ሁኔታ የተደራጁ በምዕራፍ ስምንት ላይ እናገኛለን፡፡ አስረጅ 30 ለዚህ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ እነዚህ በመጨረሻዎቹ ምዕራፍ ላይ የሚገኙ ተግባራት ሲሆኑ እስከ ምዕራፍ 5 ድረስ በዚህ አይነት የተደራጁ የቃላት ተግባራት የሉም፡፡ይህ የሚያሳየን አደረጃጀቱ ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ በቀስ እያደጉ የሚሄዱ እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ ይህም መማሪያ መጽሃፉ በዚህ ረገድ ጥንካሬ እንዳለው ያሳያል፡፡

## 4.1.4. የቃላት ትምህረት አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በምዕራፍ ሁለት በ2.5 ላይ የተለያዩ የቃላት ማቅረቢያ ዘዴዎች እንዳሉ እነሱም ቃላትን በአውድ አሰደግፎ ማቅረብ፣ በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ፣ የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን ተመርኩዞ ማቅረብ፣ ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ፣ በመዝገብ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ እንዲሁም የቃላት ትምህርትን ግልጽ በሆኑ መመሪዎች ማቅረብ የሚሉት በማቅረቢያ ስልቶች ስር ቀርበዋል፡፡ እነዚህን የማቅረቢያ ስልቶች መሰረት አድርገው የቀረቡት ምን ያህል እንደሆኑ ለማየት ተሞክሯል፡፡

### 4.1.4.1. ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

አንድ ቃል በቁሙ የተለያየ ፍቺ ሊኖረው ይችላል፡፡ የቃሉ ፍቺ ግልጽ የሚሆነው በአውድ ውስጥ ሲቀርብ ነው፡፡ ስለሆነም ቃላትን በቁማቸው ለትምህርትነት ከማቅረብ ይልቅ በአረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ፍቻቸውን ለመገመት በሚያስችል ሁኔታ ማቅረቡ የበለጠ ለመማርና

ለመረዳት ምቹ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲጥሩና ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው በመገመት በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላቸዋል (Hunt and Belgar, 2002:83) በማለት ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ቃላትን በአውድ አስደግፎ ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠው ለማወቅ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል፡፡ ይህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡ ቃላት በአውድ አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ**

| ተ.ቁ | የተግባራት አይነት | የተግባራ ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የቃላት ፍቺ በአረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ የሚያደርጉ | 23 | 14.65 |
| 2 | በአረፍተ ነገር ውስጥ የተተወ ባዶ ቦታ ተገቢ ፍቺ ባለው ቃል በማሟላትና በመተካት እንዲማሩባቸው ሁነው የቀረቡ | 31 | 19.75 |
| 3 | የቃላትን ፍች ከዓ.ነገሩ በመነሳት እንዲገምቱ የሚጠይቁ | 14 | 8.92 |
| 4 | ከተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ አንጻር በአውድ የቀረቡ | 51 | 32.48 |
| 5 | የተለመዱ አገላለጾች (መሸጋገሪያ) ቃላት | 15 | 9.55 |
| 6 | ፈሊጣዊ አነጋገሮች | 16 | 10.19 |
| 7 | ጥምር ቃላት | 7 | 4.46 |
| ድምር | | 157 | 100 |

ከሰንጠረዥ 4. መረዳት እንደሚቻለው አውድን አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ የቃላት ተግባራት አጠቃላይ 157 ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ 51 (32.48%) ከፍቺ መመሳሰልና መቃረን አንጻር የቀረቡ ናቸው፡፡ የቃላትን ፍቺ ለማስተማር ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ያላቸውን ቃላት በማቅረብ ማለማመድ ይቻላል፡፡ የቃላትን ፍቺ በተመሳሳይም ሆነ በተቃራኒ ለማስተማር ሲፈለግ ትምህርቱ አውዳዊ አቀራረብን የተከተለ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ፍቻቸውን

ከአውዳቸው በቀላሉ ለመተንበይ ያስችላል (Wallace, 1988) በማለት ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም አውድን መሰረት አድርገው ከቀረቡት የቃላት ተግባራት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን ለሚጠይቁ የቃላት ትምህርቶች ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጣቸው መረጃው ያሳያል፡፡ አቀራረባቸውም ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ወይም በማዛመድ መልክ እንዲመልሱ በማድረግ የቀረቡ ናቸው፡፡

## *አስረጅ 5*

*መልመጃ ሁለት*

*ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ'ለ" ካለት በመምረጥ አዛምዱ፡፡*

| "ሀ " | "ለ" | |
|---|---|---|
| ፩. ወገግታ | ሀ. ቦታ፣ ሁኔታ | |
| ፪. ቀዳሚ | ለ. ሀያ አምስት ሳንቲም | |
| ፫. መገለጥ | ሐ. ምሳለ | |
| ፬. አውራጅ | መ. መታየት | |
| ፭. ማብሰር | ሠ. አቀንቃኝ | |
| ፮. ስሙኒ | ረ. መጀመሪያ | |
| ፯. አውድ | ሰ. ፀዳል | |
| ፰. አብነት | ሸ. መንገር | (ገጽ፣ 21) |

ከላይ በአስረጅነት የቀረበው ተግባር በተመሳሳይ ፍቺ ቃላትን እንዲያዛምዱ የሚያደርግ ሲሆን በተመሳሳይም ሆነ በተቃራኒ ቃላትን በአውድ አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ሰፊ ሽፋን እንደተሰጣቸውና የተሻለ አቀራረብ እንዳላቸው በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ መልክ የቀረቡ ሌሎች የቃላት ተግባራትን አባሪ አንድ አስረጅ 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 13፥ 19፥ 23፥ 24 እና 30 ላይ እናገኛለን፡፡

በአረፍተ ነገር ተደግፌው ከቀረቡት ውስጥ የቃላትን ፍቺ ከአርፍተ ነገሩ በመነሳት እንዲገምቱ የሚያደርጉ 14 (8.92%) ተግባራት እንዳሉ መረጃው ያስረዳል፡፡ የተግባራቱ አቀራረብም ከአረፍተ ነገሩ ጽንሰ ሀሳብ በመነሳት ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

## *አስረጅ 6*

*መልመጃ አንድ*

*በሚከተለት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡*

፩. ሄኖክ ለእናት ሀገር ጥሪ ወደ ድንበር ገሰገሰ፡፡

፪. እሱባለው ብእሩን አልሰጥም አለ፡፡

፫. ኢትዮጵያ የህዳሴ ግዴብ ሙሊት በሰላም መጠናቀቁን አስመልክታ ለአለም ሀገራት ደስታዋን አበሰረች፡፡

፬. ለሁለም ነገር የሚሻለው በህብረት መቆም ነው፡፡

፭. ስነቃል በባህርዩ ተለዋዋጭ ነው፡፡

፮. በስርአት የሚሰደሩ ዴምፆች ስብስብ ቃል ይባላል፡፡ (ገጽ፣ 97)

እንዲሁም የቃላትን ፍቺ በአረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ የሚጠይቁ 23 (14.65%)ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ ተካተዋል፡፡ በቀረቡት ቃላት የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን በመመስረት ፍቻቸውን እንዲያሳዩ የሚያዙ ናቸው፡፡

## *አስረጅ 7*

*መልመጃ ሁለት*

*በሚከተሉትን ቃላት አውዳዊ ፍቺ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ስሩ፡፡*

| | |
|---|---|
| ፩. ባህል | ፮. ፋይዳ |
| ፪. ጠላት | ፯. ሀሴት |
| ፫. ንዋይ | ፰. ሙስና |
| ፬. አሸን | ፱. ዋና |
| ፭. አዛውንት | ፲. አባይ (ገጽ፣ 97) |

ሌላው በአረፍተ ነገር ውስጥ የተተወ ባዶ ቦታ ተገቢ ፍቺ ባለው ቃል በማሟላትና በመተካት እንዲማሩባቸው ሁነው የቀረቡ 31(19.75%) ያህል ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ ተካተዋል፡፡

እነዚህ ተግባራት በአረፍ ተነገር ወይም በአንቀጽ መልክ የተዘጋጁ ሲሆኑ በውስጣቸው የተጓደሉ ቃላትን በማሟላት ወይም በመተካት የሚመለሱ ሁነው ቀርበዋል፡፡

## *አስረጂ 7*

### *መልመጃ አንድ*

***ከዘህ በታች በሰንጠረዣ የቀረቡትን ቃላት አውዲዊ ፍቻቸውን መሰረት አድርጋችሁ በባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት አረፍተነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዳጎስ | ወላፈን | ሳንካ | ሀገረ ሰብዒዊ |
| መሻሻል | አዘቦት | ቤተ ምርምር | ማእረግ |

፩. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከበሩ------------------ ክብረ በአላት መካከል የወላይታ ህዛብ የዘመን መለወጫ “ጊፋታ” አንዱ ነው፡፡

፪. የእሳቱ--------------- ዳር ያሉትን ሰዎች ሁሉ ገረፋቸው፡፡

፫. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ባለፈው አመት ላስመዘገቡት አመርቂ ውጤት ------------ ያል ሽልማት ተበረከተላቸው፡፡

፬. የአንዲት ሀገር ማሕበራዊ ኑሮ-------------የሚችልው ሕዝቡ በትምህርት የታነጸ ከሆነ ነው፡፡

፭. ኮቪድ 19 (ኮሮና ቫይረስ) ለሀገራችን እድገት -------------- ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡

፮. በሣይንስና ቴክኖሎጂ ጥበብ የበለጸጉት ሀገሮች አሁን ከደረሱበት የእድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት የ------------------ ጥናታቸውን በማጠናከራቸው ነው፡፡

፯. ዘምዘም በበአላት ቀን ይቅርና ለ-----------------ቀን የምታዘጋጀው ምግብ ጣት ያስቆረጥማል፡፡

፰. ወንጀለኞችን በቁጥጥር ስር ያዋለው ፖሉስ የ-------------ዕድገት አገኘ፡፡

(ገጽ፣ 111)

እስካሁን ከላይ በአረፍተ ነገር መልክ የቀረቡትን አስረጅዎች ስንመለከት የቃላትን ፍቺ በአረፍተ ነገራዊ አውድ በማስገባት ፍቻቸውን እንዲገነዘቡ የተደረገበት ሁኔታ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ Harmer (1991) ቃላትን በተናጥል ከማቅረብ ይልቅ በአረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ማቅረብ ቃላትን ለረጅም ጊዜ ሳይረሱ እንዲቆዩ ለማድረግ ያግዛል የሚለውን ሃሳብ በተገቢው ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያመላክታል፡፡ አቀራረባቸውም የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ በገቡበት ቦታ ለመገመት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች ይዘው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም የቃላትን ፍቺ አረፍተ ነገራዊ አውድን መሰረት አድርገው እንዲማሩ መደረጉ ፍቻቸውን ከአገባባቸው እንዲገምቱና በቀላሉ እንዲረዱ ስለሚያደርግ መማሪያ መጽሃፉ በዚህ ረገድ የተሻለ አቀራረብ እንዳለው መረጃው ያመላክታል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ቃላቱ የሚገኙባቸው አረፍተ ነገሮች ርዝማኔ ነው፡፡ ምክንያቱም ቃላቱ የሚቀርቡባቸው አረፍተ ነገሮች ከመጠን በላይ አጥረው ወይም ረዝመው የቃላቱን ፍቺ ለመገመት የሚያስቸግሩ መሆን የለባቸውም፡፡ አረፍተ ነገሮቹ ከአምስት እስከ አስር ቃላትን የያዙ ቢሆኑ የቃላትን ፍቺ ለመገመት ያመቻሉ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ከአምስት በታች ወይም ከአስር በላይ ቃላትን የሚይዙ ከሆኑ የቃላቱ ብዛት እያነሰ ወይም እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለትንበያ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል (Nation and Coady, 1988) በማለት ገልፀዋል፡፡

ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቃላት ትምህርቶቹ የቀረቡባቸው ዐረፍተ ነገሮች መጠን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተካተው ከቀረቡት የቃላት ተግባራት ውስጥ ሁሉም ስለተገኙ  የተሻሉ ሆነው እንደቀረቡ በተደረገው ሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## *አስረጂ 8*

### *መልመጃ አንድ*

*በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡*

፩. ሄኖክ ለእናት ሀገር ጥሪ ወደ ድንበር <u>ገሰገሰ</u>፡፡

፪. እሱባለው <u>ብዕሩን</u> አሌሰጥም አለ፡፡

፫. ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሙለት በሰላም መጠናቀቁን አስመልክታ ለአለም ሀገራት ደስታዋን አበሰረች፡፡

፬. ለሁሉም ነገር የሚሻለው በህብረት መቆም ነው፡፡

፭. ስነቃል በባህርዩ ተለዋዋጭ ነው፡፡

፮. በስርአት የሚሰደሩ ድምፆች ስብስብ ቃል ይባላል፡፡ (ገጽ፣ 97)

ከቀረበው አስረጅ መረዳት እንደሚቻለው ከላይ ከተጠቀሰው መለኪያ ውጪ የሆኑት በ‹‹፫›› በቀረበው ጥያቄ ላይ ሲሆን 11 በሆነ ቃላት አረፍተ ነገሩ እንደተዋቀረ በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተረፈ ሌሎች በአረፍተ ነገር መልክ የቀረቡት የቃላት ተግባራት ከ5-10 ባሉ ቃላት የተገነቡ ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች የቃላቱን ፍቺ በቀላሉ መገመት እንዲችሉ ከማድረግ አንጻር ጉልህ ድርሻ ስለሚኖረው በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው፡፡

ፈሊጣዊ አነጋገሮች የተዋቀሩባቸው ቃላት በተናጥል ከሚያስተላልፉት መልዕክት ውጪ በህብረት የሚይዙት ፍቺ ስላላቸው ሊወሳሰቡ ይችላሉ፡፡ ይህንን ውስብስብነት ለመቀነስ ፈሊጦችን በአውድ አሰደግፎ ማቀርብ የተሻለ እንደሚሆን Didrichs (2005) ገልጸዋል፡፡

***አስረጂ 9***

***መልመጃ አራት***

***በ "ሀ" አምድ ስር ላሉ ፈሉጣዊ አነጋገሮች በ "ለ" አምድ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡***

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ቃሉን ሰጠ | ሀ. ሊቅ፣ አዋቂ፣ ተመራማሪ |
| ፪. ቀንበር ሰበረ | ለ. የሰሚ ሰሚ፣ ጭምጭምታ |
| ፫. ነጭ ለባሽ | መ. ሀጢያት |
| ፬. የቀለም ቀንድ | ሠ. ስማኝ፣ አዲምጠኝ |
| ፮. ደዌ ነፍስ | ረ. ህግ ተላለፈ |
| ፯. ውሃ መውቀጥ | ሰ. የመንግስት ሰላይ |
| ፰. የልጅ አዋቂ | ሸ. ከንቱ ልፋት |
| ፱. ድንጋይ ኳሱ | ቀ. አስተዋይ፣ ቁምነገረኛ |
| ፲. ጆሮ ስጠኝ | በ. ደፋር፣ ለምንም ነገር የማይበገር |
| | ተ. ፈሪ፣ እርብትብት |
| | ቸ. የቀለም መበጥበጫ |

ጥምር ቃላት፣ በጥመራ የሚፈጠሩ ፈሊጦችና የተለመዱ አገላለጾች (የመሸጋገሪያ ቃላት) ተግባር ተቀርጾላቸው በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ እንደተካተቱ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡ ለዚህም አስረጂ 6. መመልከት ይቻላል፡፡

*አስረጂ 10.*

*መልመጃ አንድ*

*በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ጥምርቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡*

| | | |
|---|---|---|
| መቅረፀ-ድምጽ | ሰላማዊ ሰልፍ | አውራ ጎዳና |
| ብርድ ልብስ | ቤተ-መንግስት | ትምህርት ቤት |
| ብረት ምጣድ | ሸክላ ድስት | አየር መንገድ |

፩. ኢትዮጵያውያን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ስላስድሰታቸው------------------አካሀዱ፡፡

፪. አሜሪካ ኢምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ-------------------ይዞ መግባት አይቻልም፡፡

፫. እናቴ ዶሮ ወጥ የምትሰራበት----------------------ገዛች፡፡

፬. ሀሴት የገብስ ቆሎ ለመቁላት ከጎረቤቷ----------------------ተዋሰች፡፡

፭. ጽዱ እና ውብ የሆነው የአንድነት ፓርክ መገኛ ቦታው--------------------ነው፡፡

፮. ከአዲስ አበባ ወደ ሀዋሳ የሚወስደው------------------በመፍረሱ እየተጠገነ ነው፡፡

፯. የኢትዮጵያ-------------------------ሰራተኞች ስራቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነው፡፡

ከላይ የቀረበው አስረጂ በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ጥምር ቃላት በመምረጥ ባዶ ቦታውን እንዲያሟሉ የሚያዝ ተግባር ነው፤ ስለዚህ መማሪያመፅሀፉ በጠንካራ የሚታይ ነው፡፡ናቸው

### 4.1.4.2. ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

የቃላት ዝምድና ከሚታይባቸው መንገዶች አንዱ ፍቺ ነው፡፡ ቃላትን ከፍቺ ተዛምዶ አንፃር ማደራጀትና ማቅረቡ የጠለቀ የቃላት ዕውቀት እንደሚያላብስ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡ ይህንን ዝምድና ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል፡፡

በመሆኑም የተለያዩ የፍቺ ዝምድናዎችን ለማሳየት ቃላትን በተመሳስሏቸው፣ በተቃርኗቸው፣ በከታች ተከታች ግንኙነታቸውና አብሮ ተሰላፊነታቸው እንዲሁም በድምጽ መጥበቅና መላላት ቃላት ከሚያስከትሉት የፍቺ ለውጥ አንፃር ያላቸውን አቀራረብ በዝርዝር ለማየት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተደግፎ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡ ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ**

| ተ.ቁ | የተግባራ ዓይነት | የተግባራ ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ቃላትን በተመሳሳይና በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ የተመለከቱ | 51 | 62.96% |
| 2 | የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት የተመለከቱ ተግባራት | - | - |
| 3 | በድምጽ መጥበቅና መላላት የተለያየ ፍቺ መስጠትን | - | - |
| 4 | የቃላት አብሮ ተሰላፊነት የተመለከቱ ተግባራት | 7 | 8.64 |
| 5 | በዓ፣ነገር በማስደገፍ የቃላትን ፍቺ ለማስተማር የቀረቡ | 23 | 28.4% |
| ጠቅላላ ድምር | | 81 | 100% |

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብን የተመለከተ 81 ተግባራት ውስጥ 51(62.96%) የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን ለማሳየት የቀረቡ በመሆናቸው ከፍተኛ ሽፋን እንደተሰጣቸው ከላይ ቃላትን በአውድ አስደግፎ ከማቅረብ ጋር ተያይዞ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም ከፍቺ ተዛምዶ አንጻር የቀረቡ የቃላት ተግባራትን ስንመለከት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺን በማስተማር ረገድ በመማሪያ መጽሐፉ

ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጣቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የተግባራቱ አቀራረብም በአውድ ተደግፈው፣ ፍቺቻውን እንዲሰጡ ተደርገውና ፍቺቻውን እንዲያዛምዱ ተደርገው የቀረቡ በመሆናቸው የተሻለ አቀራረብ አላቸው፡፡ በተመሳሳይና በተቃራኒ የቀረቡ የቃላት ተግባራት አባሪ አንድ አስረጂ 1፥ 2፣ 3፥ 4፥ 23 ፥ 24 እና 26 ላይ ስለሚገኙ ለዚህ ማሳያ ይሆናሉ፡፡

ከተመሳስሎና ተቃርኖ በመቀጠል ከፍቺ አንፃር ትኩረት የተሰጣቸው በአረፍተ ነገራዊ አውድ በማስደገፍ የቃላትን ፍቺ የሚጠይቁ ተግባራት ሲሆኑ 23(28.4%)ክንውኖች ይዘዋል፡፡ እነዚህ የቃላት ተግባራት በአረፍተ ነገር ውስጥ የተተወ ባዶ ቦታ ተገቢ ፍቺ ባለው ቃል በማሟላትና በመተካት እንዲማሩባቸው ሁነው የቀረቡ፣ የቃላት ፍቺ በአረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ የሚጠይቁና የቃላትን ፍች ከአርፍተ ነገሩ በመነሳት እንዲገምቱ የሚጠይቁ የቃላት ተግባራት መሆናቸውን ቀደም ብሎም አውድን መሰረት በማድረግ ከቀረቡት ጋር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የቃላት አብሮ ተሰላፊነትን የሚያመለክቱ ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ እንደተካተቱ በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሎአል፡፡ አብሮ ተሰላፊ ቃላትን ለማስተማር አንዱን ቃል በማቅረብ የሌላውን ቦታ ክፍት ትቶ ተማሪዎች እንዲሞሉት በማድረግ ማለማመድ ይቻላል (McCarthy, 1990) በማለት ያስረዳሉ፡፡ ሌላው በድምጽ መጥበቅና መላላት የተለያየ ፍቺ መስጠትን የተመለከቱ ተግባር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ምንም ተግባር እንዳልተካተቱ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡ ይህ የመማሪያ መጽሐፉ ችግር እንደሆነ ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሃፉ ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብን የተመለከቱ የቃላት ትምህርቶች አብዛኛውተካተው እንደቀረቡ በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን የቃላት የከታች ተከታች ግኙኝነት የሚመለከቱ ተግባራት አለመካተታቸው በቃላቱ መካከል ያለውን ግኑኝነትና የፍቺ ዝምድና እንዳይረዱ ስለሚያደርግ እንደ ክፍተት የሚታይ ነው፡፡

## 4.1.4.3. የቃላት እርባታና ምስረታን መሰረት ያደረጉ የቃላት ትምህርቶችን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደት ላይ ያተኮሩ የቃላት ትምህርቶች ለተማሪዎች ማቅረቡ የቃላቱን ትርጉም ለመረዳትም ሆነ አፍልቆ መጠቀም እንዲችሉ መሰረት ይጥልላቸዋል (Gairns and Redman,1986) ብለዋል፡፡ እንዲሁም Ur (2006) የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታመንበት የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ሌላው ስልት የቃላትን የእርባታና ምስረታ ስርአት

በመከተል ማቅረብ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጽሃፉ የቃላት እርባታ ምስረታ ሥርዓትን መሰረት አድርጎ የቀረቡ የቃላት ትምህርቶችን በተመለከተ የሰነድ ፍተሻ ተካሂዷል፡፡ ይህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ተደግፎ ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 6፡ የቃላትን እርባታና ምስረታ ሥርዓትን መሰረት አድርገው የቀረቡ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | የተግባር ዓይነት | የተግባርብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ቃላትን በተለያየ መደብና ጾታ እያረቡ መፃፍ | - | - |
| 2 | የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን መመስረት እና ነጠላስሞችን ወደብዙ ቁጥር መለወጥ | 10 | 100 |
| 3 | ቃላትን በተለያየ ቅርጽ በመፃፍ ማራባት እንዲሁም ሌሎች ቃላትን መመስረት | - | - |
| ጠቅላላ ድምር | | 10 | 100 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማየት እንደሚቻለው የቃላት እርባታና ምስረታ ሥርዓትን መሰረት አድርገው የቀረቡ ተግባራት በጠቅላላው 10 ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ቃላትን በተለያየ መደብና ጾታ እያረቡ መፃፍ እና ቃላትን በተለያየ ቅርጽ በመፃፍ ማራባት እንዲሁም ሌሎች ቃላትን መመስረት የተመለከቱ ተግባራት በመጽሃፉ ያልተካተተ መሆኑ በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር ነጠላ ቁጥሮችን ወደ ብዙ ቁጥር መለወጥን የተመለከቱ 10(100%) የቃላት ተግባራት ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ ተካተው ቀርበዋል፡፡ በቃላት ላይ የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር በቋንቋ ውስጥ በአንፃራዊ መልኩ ጥቂት ቁጥር ያላቸውን የቃላት አፈጣጠር ሂደቶች በመከተል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላት መፍጠር ይቻላል (McCarthy, 1990) ብለዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተግባራት በቃላት ትምህርት ስር መቅረባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላት እየመስረቱ እንዲማሩባቸው እና ነጠላስሞችን ወደ ብዙቁጥሮች ከማድረግ አንጻር የሚደገፍ ነው፡፡

*አስረጅ 11*

***መልመጃ አንድ፡***

*የሚከተለትን ስሞች "-ኣት" የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ወደ ብዙ ቁጥር ለውጡ፡፡*

| ተራ ቁጥር | ነጠላ | ብዙ |
|---|---|---|
| ፩. | አመት | |
| ፪. | ዲያቆን | |
| ፫. | ወር | |
| ፬. | ካህን | |
| ፭. | ቃል | |

***መልመጃ ሁለት***

*የሚከተሉትን ምሳለዎች መነሻ በማድረግ ከታች የተደረደሩትን ነጠላ እና ብዙ ቁጥር አመልካች ስሞች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ስሩ፡፡*

ምሳለ፡- ልጅ - ነጠላ

የሁሴን ልጅ በሥነ ምግባር የታነፀ ነው፡፡

ልጆች --- ልጅ-ኦች

የኛ ሰፈር ልጆች በትምህርታቸው ጎበዞች ናቸው፡፡

፩. ሴት

ሴቶች

፪. ላም

ላሞች

፫. ተማሪ

ተማሪ ዎች

፬. መምህር

መምህራን

፭. ዘመን

ዘመናት

(ገጽ፣ 35)

**የሚከተሉትን ቃላት ተጠቅማችሁ ገቢርናተገብሮ አረፍተነገሮችን መስርቱ።**

1. ገደለ

ተገደለ

2. ውድድር

ተወደደ

3. ልብስ

ተለበሰ

4. ቀመሰ

ተቀመሰ

5. ጥብስ

ተጠበሰ

6. ጨረሰ

ተጨረሰ

7. ፈለገ

ተፈለገ

ከላይ በአስረጅነት የቀረበው የቃላት ተግባር ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ የሚያዝ እና ነጠላስሞችን ወደ ብዙ ቁጥርእንዲለውጡ የሚያዝ ነው። በአጠቃላይ እስካሁን ያየናቸው የቃላት ተግባራት በተለያየ አግባብ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቃላት እርባታና ምስረታን መሰረት በማድረግ የቃላት ትምህርቶቹ የቀረቡበት ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች ምሳሌዎችን መሰረት በማድረግ የቃላትን ቅርጽ በመቀያየር የተለያዩ ቃላትን እንዲመሰርቱ፣ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ የሚያድረጉ ናቸው።

የቃላት እርባታና ምስረታን መሰረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች ማቅረቡ የቃላቱን ትርጉም ለመረዳትም ሆነ አፍልቆ መጠቀም እንዲችሉ መሰረት እንደሚጥልላቸው በምዕራፍ ሁለት ላይ ተጠቁሟል። በመሆኑም እንደነዚህ ዓይነት ተግባራት በቃላት ትምህርት ስር መቅረባቸው ተገቢ ከመሆኑም በላይ የመጽሐፉን ጠንካራ ጎን የሚያሳይ ነው።

### 4.1.4.4. ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ፈሊጦች፣ ጥምር ቃላትና መሸጋገሪያ ቃላት በቃላዊ ሐረጎች ስር የሚመደቡ እንደሆኑና ለትምህርትነት መቅረባቸው ደግሞ ተማሪዎች በቀላሉ እንዲያስታውሱ ከማስቻሉም በላይ በንግግር ጊዜ በነጠላ ቃላት ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸው ተጠቅሷል፡፡ እንዲሁም ቃላት በትውስታ ማህደር የሚቀመጡት ነጠላ ሁነው ብቻ ሳይሆን የሀረግ አካል ሁነውም ጭምር እንደሆነ (Larsen, 2017) ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ቀደም ብሎ ከላይ እንደተገለጸው በርእሰ ጉዳዮቹ ዙሪያ የቃላት ተግባራት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መካተቱን በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ፈሊጣዊ አነጋገሮች በቋንቋ ውስጥ ካላቸው የተለየ ባህሪና ከሚሸከሙት የተለየ ፍቺ አንፃር ተማሪዎች አውቀው እንዲጠቀሙባቸው መደረጉ የቃላት ዕቀውታቸውን ያጎለብትላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ጥምር ቃላትን በማቅረብ ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ፣ በማጣመር እንዲያዛምዱ እንዲሁም ሁለት የተለያዩ ቃላትን በማጣመር አዳዲስ ቃላት እንዲመሰርቱ ወዘተ የሚያደርጉ ተግባራትን ቀርጾ ለትምህርትነት ማቅረብ የተሻለ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሌላው የመሸጋገሪያ ቃላትን አገልግሎት ከመረዳትና ቃላቱን  ከንግግርና ከፅህፈት ጋርም በማያያዝ ተማሪዎች ሲጽፉና ሲናገሩ እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችሉ ተግባራትን በመቅረጽ ከማለማመድ አንፃር የቀረበ የቃላት ተግባር መኖሩ በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን የተመለከቱ የቃላት ትምህርቶች መቅረባቸው መማሪያ መጽሀፉ በዚህ ረገድ ጠንካራጎን እንዳለው፡፡ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.1.4.5. ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብን የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ተማሪዎች መግባባት እንዲችሉ በተገቢ ሁኔታ በቃላት ትምህትርት መታገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ በማቅረብ ማስተማር የመማር ሂደቱን የተቃና ያደርገዋል (Lewis, 1993) በማለት ገልጸዋል:: ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጽሐፉ

ውስጥ የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ተጣምሮ የቀረቡበትን ሁኔታ ለማወቅ የሰነድ ፍተሻ ለማድርግ ተሞክሯል፡፡ ይህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል

**ሰንጠረዥ 7፡ ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ**

| ተ.ቁ | የተግባራ ዓይነት | የተግባራ ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | አንብቦ መረዳት ጋር | 44 | 72.13% |
| 2 | ከመጻፍ ክሂል ጋር | 17 | 27.87 |
| 3 | ከማድመጥ ክሂል ጋር | - | - |
| 4 | ከመናገር ክሂል ጋር | - | - |
| ጠቅላላ ድምር | | 61 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ 7 የቀረበው አስረጅ ቃላትን ከክሂሎች ጋር ማቅረብን የተመለከቱ ተግባራትን የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ የቃላት ተግባራት የተለቀሙት መማሪያ መጽሐፉ ይዘቶችን ባቀረበበት (አንብቦ መረዳት፣ ቃላት፣ መጻፍ፣ ማድመጥ፣ መናገርና ሰዋሰው) በማለት ከፋፍሎ ባስቀመጠበት አግባብ ሲሆን በክሂሎቹ ስር የቀረቡትን የቃላት ተግባራት በመቁጠር የተወሰዱ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ቃላትን ከክሂሎት ጋር አጣምሮ ማቅረብን የተመለከቱ አጠቃላይ 61 ተግባራት ያሉ ሲሆን 44(72.13%) ያህሉ አንብቦ መረዳት ስር የቀረቡ ናቸው፡፡ እንደ Eyraud (2000:2) ገለጻ አብዛኛው የቃላት እውቀት የሚጨበጠው በክሂሎች (በማንበብ፣ በማዳመጥ፣ በመናገርና በመፃፍ) ነው፡፡ በተለይ ከንባብ ጋር አጣምሮ ማቅረብ ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ይህም ከምንባቡ የወጡ የቃላት ተግባራትን በማዘጋጀት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ በማድረግ አንብቦ መረዳታቸውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ለዚህም ይመስላል በማንበብ ክሂል ስር የቃላት ተግባራት ከፍተኛውን ቁጥር ይዘው የተገኙት፤ ምክንያቱም ቃላትን ለማስተማርና ፍቺቻውን ከቀረበው ጽሑፍ በመፈለግ የሚሰሩበት ሁኔታ ለመፍጠር ምንባብ አመቺ ክሂል

እንደሆነ ከቀረበው ገለጻ መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንፃር መማሪያ መጽሐፉ የቃላትን ትምህርት ከንባብ ክሂል ጋር በማጣመር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እንዳቀረበ መረጃው ያሳያል።

ሌላው በጽህፈት ክሂል ስር የቀረቡት የቃላት ተግባራት ስንመለከት 17(27.87%) ናቸው።ከነዚህም ዉስጥ የተለያዩ ቃላትን እና መስተጻምሮችን ወይም መሸሀጋገሪያ ቃላት በመጠቀም ባዶ ቦታዎችን አሟልተው እንዲጽፉና ፈሊጣዊአነጋገሮችን ከምንባቡ በማውጣት ትርጉማቸውን እንዲፅፉ የሚያዙ ናቸው፡፡

*አስረጅ 12*

***መልመጃ ሁለት፤***

***በሚከተለው ሰንጠረዣ ውስጥ ያለ ውስብስብ ቃላትን ተጠቅማችሁ ከታችያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ።***

| | | |
|---|---|---|
| ይፈጥርላቸዋል | ተማሪዎቻቸው | አገልግሎታቸውን |
| ይገነዘቡበታል | ኑሯቸውን | ከተከታተልናቸው |
| መልእክቶችን | እየጨፈጨፉ | ምጣኔ ሀብታዊ |

፩. የአንድ ሀገር-----------እድገት በዘጎች ኑሮ ላይ ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል።

፪. ሰዎች ደኖችን-------------------የአካባቢ መራቆት እንዲፈጠር ያደርጋሉ።

፫. ደብዳቤ ----------------------------ለማስተላለፍ ያገለግላል።

፬. ሰዎች ለሰዎች መልካም ነገሮችን ሲያደርጉ የህሊና እርካታ----------------።

፭. በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን-----------ለማሻሻል ለት ተቀን በርካታ ስራዎችን ይሰራሉ።

፮. አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ------------------ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ።

፯. መምህራን ለ--------------ሁልጊዘ አርአያ መሆን አለባቸው።

፰. አረጋውያንን ትኩረት ሰጥተን ካዳመጥናቸው እና-------------ጠቃሚ ምነገሮችን ያስጨብጡና

ከላይ በአስረጂነት የቀረቡት የቃላት ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ ዉስጥተካተው እናገኛቸዋለን፡፡እነዚህ ተግባራት በመጻፍ ኪህል ስር የቀረቡ ሲሆኑ በሰንጠረዥ ውስጥ የተለያዩ ቃላት ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን አሟልተው እንዲጽፉ የቀረቡ ተግባሮች እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመፃፍ ክሂል ይዘት ስር የቀረቡትን ሌሎች የቃላት ተግባራት ስንመለከት በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች የተለያዩ መሸጋገሪያ ቃላትን ወይም ሐረጋት በመጠቀም አሟልተው እንዲጽፉ የሚያዙ እንደሆኑ ማረጋገጥተችሏል፡፡

***አስረጅ 12. ተግባር፡- በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከዘሀ በታች ከቀረቡት መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት መካከል በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡***

ከዚህ በማያያዝ በመቀጠል ከዚህ ቀጥሎ እስከዚህ ድረስ በሌላ ጊዜ ወደፊት

፩. ተጋባዡ እንግዳ መጻሕፍት የማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለፃ አደረጉ፤----- ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት በራስ አባባል ማስታወሻ መያዝ ጠቃሚ እንደሆነ ተናገሩ፡፡

፪. እስካሁን ያለው የንባብ ልምዳችን ብዙ የሚያኮራን ላይሆን ይችላል፤--------ግን አስፈሊጊነቱን ስለተረዳን ጠንክረን ሌናሻሽለው እንችላለን፡፡

፫. የጤና ባለሙያው የኤች አይ ቪ ኤድስን የመተላለፊያ መንገዶች በሚመለከት ዋነኛ የሆኑትን በዝርዝር አቀረቡ፤-------------በዚህ ጉዳይ ላይም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይተው ገለፃ በመስጠት ንግግራቸውን ጨረሱ፡፡

፬. ሁለም ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በተሰማራበት ተግባር ለሀገሩ እድገት ማበርከት አለበት፤------------------የተሰሩት ስራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

፭. አጭር ልቦለድን በሚመለከት የአላባውያኑን ምንነት ተምረናል፤---------መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋትን እንማራለን፡፡

(ገጽ፣ 46)

አስረጅውን ስንመለከት የጽህፈት ክሂል የቃላት ትምህርትን ከክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብን በተመለከተ Lewis (1993) የተለያዩ የቃላት ተግባራትን በማቅረብ እንዲያደምጡ፣ ያደመጡትን

እንዲጽፉ፣ እንዲሁም ፍቺዎቻቸውን በቃላቸው እንዲናገሩ በማድረግ የተግባቦት ችሎታቸውን ማሳደግ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ ቃላትን ከንባብና ከጽህፈት ክሂል ጋር አጣምሮ በማስተማር ረገድ የተሻለ አቀራረብ እንዳለ፣ እንዲሁም በማድመጥና በመናገር ክሂል ይዘት ስር ምንም ዓይነት የቃላት ተግባራት እንዳልቀረበ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ከማድመጥና ከመናገር ክሂል ጋር የቃላት ትምህርትን አጣምሮ ከማቅረብ አንጻር መማሪያ መጽሀፉ ውስንነት ይታይበታል፡፡

## 4.1.4.6. የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የቃላት ትምህርትን ማቅረብና ተማሪዎችን ማለማመድ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የጎላ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል፡፡ እንዲሁም ተማሪው መምህሩን ወይም ጓደኛውን ጠይቆ መረዳት በማይችልበት ወቅት መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ችግሩን ሊፈታ ስለሚችል የቃላቱን ፍቺ እንዴት መፈለግ እንዳለበት የሚጠቁም የቃላት ተግባር አካቶ ማስተማር እንደሚያስፈልግ (Gairns and Redman 1986) ገልጸዋል፡፡

ከዚህ አንፃር መማሪያ መጽሐፉ የሚገኝበት ሁኔታ ለማወቅ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ በመዝገበ ቃላት አሰደግፎ ማለማመድ የሚመለከት የቃላት ተግባር እንደተካተተ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

*አስረጅ 14.*

*ተግባር ሁለት፤ ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡*

ሀ. መነመነ

ለ. ደለደለ

ሐ. በረከት

መ. ኮተኮተ

ሠ. ትኩረት

(ገጽ፣52]

*አስረጂ 13*

*መልመጃ ሁለት ፤*

***ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በደብተራችሁ አስፍሩና ለመምህራችሁ አሳዩ።***

፩. ትንቢት ፭. አዛውንት

፪. መባቻ ፮. ቀጠሮ

፫. ማግስት ፯.ማነጽ ገፅ 70.

፬. በለተ

ከላይ የቀረበው አስረጂ በዚህ ተግባር ስር የሚካተት ሲሆን የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከመዝገበ ቃላት በመፈለግ ሰርተው እንዲያሳዩ እና ከምንባቡ የወጡ ቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚያዙ ናቸው።ይህ ደግሞ ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው እንዲሰሩ እና አጠቃቀሙንም እንዲለምዱ እዲሁም የቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ማለት ቀጥተኛ ፍቺ መሆኑን እንዲረዱ ያደርጋቸዋል።

## 4.1.4.7. የቃላት ትምህርት መመሪያዎች አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

የቃላት ትምህርትን የሚመለከቱ ተግባራት ተማሪዎች እንዲተገብሯቸው ወይም እንዲሰሯቸው ሲቀርቡ በማያሻማ መመሪያና ምሳሌዎች ተደግፈው መሆን እንዳለበት ነው። ተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸውን የአመለካከትና የአሰራር (የባህርይ) ለውጥ እንዲያመጡ ከተፈለገ የሚቀረቡት የቋንቋ ተግባራት መመሪያዎች ትእዛዛቸው ቋንቋ ነክ ጉዳዮችን የሚያወሱ ሊሆኑ ይገባል። አቀራረባቸውም ግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ለልምምድ የሚያበቋቸው መሆን እንዳለበት ምንውየለት(2005) Alderson (1995)ን ጠቅሰው ገልጸዋል።

ከዚህ አንፃር መመሪያዎቹ ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ በተካሄደው የሰነድ ፍተሻ አብዛኛው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ተግባራት እንዲከናወኑ የሚያዙት መመሪያዎች የግልጽነት ችግር የለባቸውም። ነገር ግን የተወሰኑ የቃላት ተግባራት ላይ የቀረቡት

መመሪያዎች ከግልጽነት አኳያ ውስንነት እንዳለባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ምክንያቱም የቃላት ተግባራቱ የተዘጋጁት ከቀረቡት ምንባቦች ሁኖ ሳለ መመሪያው ግን በምንባቡ መሰረት እንዲመልሱ የሚያዙ አይደሉም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸው 12 የሚደርሱ የቃላት ተግባራት በመማሪያ መጽሐፉ ተካተው እናገኛለን፡፡

*አስረጅ 14*

*ተግባር አንድ፡-መልመጃ ሁለት*

*በ "ሀ" አምድ ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ"አምድ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምድ፡፡*

| "ሀ" | "ለ" | |
|---|---|---|
| ፩. መገናኛ ብዙሃን | ሀ. ዋጋ | |
| ፪. መታነጽ | ለ. መሰደድ፣ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ | |
| ፫. ክስተት | ሐ. ተጫዋች | |
| ፬. እሴት | መ. አዲስ ነገር | |
| ፭. ሞግዚት | ሠ. መልዕክት ማሰራጫ | |
| ፮. መፍለስ | ረ. ተንከባካቢ | |
| ፯. ተዋናይ | ሰ. መቀረጽ፣ መገንባት | (ገጽ፣ 74) |

**አስረጂ 15**

*መልመጃ ሁለት*

*ለሚከተለት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ፡፡*

ሀ. በከለ ለ. ሸፈነ ሐ. መሸሸት መ. ጠንቅ ሠ. ዝቃጭ ገፅ 102.

በአስረጅነት ከላይ የቀረቡት የቃላት ጥያቄዎች ‹‹የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ እና ህገወጥ ዝውውር በከተማችን ፥ የአየር ንብረት እና የአከባቢ ብክለት ›› ከሚሉት ምንባቦች የወጡ ናቸው፡፡ መመሪያው መሆን የነበረበት ምንባቡን መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ማዘዝ

ነው፡፡ ነገር ግን የቀረበው መመሪያ በደፈናው ተግባሩ እንዲያከናወን ወይም በቀደመው ዕውቀታቸው እንዲመልሱ የሚደርግ በመሆኑ ግልጽነት ይጎለዋል፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው ክፍተቶች ያሉ ቢሆንም አበዛኞቹ የቃላት ተግባራት ግን ግልጽ በሆኑ መመሪያዎችና ምሳሌዎች ተደግፈው የቀረቡ መሆናቸው መረጃው ያመላክታል፡፡ እንዲሁም ፍቺን መሰረት ያደረጉ ከምንባቡ የወጡት የቃላት ጥያቄዎች ከግልጽነት በተጨማሪ አመላካች ሁነው እንደቀረቡ የሰነድ ፍተሻው ያሳያል፡፡ ምክንያቱም አብዛኛው አውድን መሰረት ያደረጉ የቃላት ተግባራት ከተካተቱት ምንባቦች የተዘጋጁ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡

## 4.1.5. የቃላት ትምህርትን በተመለከተ የመማሪያ መጽሃፉና የመርሃ ትምህርቱ ተጣጥሞሽ የሚያሳዩ መረጃዎች ትንተና

በመጀመሪያ ደረጃ ይህ አዲሱ የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ መማሪያ መጽሃፍ ለየት የሚያደርገው መርሃ ትምህርቱ በማስተማሪያ መጽሃፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ አብሮ ተካቶ አልቀረበም፡፡ ይህም በደካማ ጎን ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ምክንያቱም መምህራን እቅድ ለማዘጋጀት ከሚጠቀሙበት ሰነድ አንዱ መርሃ ትምህርት ሲሆን በማስተማሪያ መጽሃፉ ላይ ባለመገኘቱ ከሱ እያገናዘቡ ለመስራት ይቸገራሉ፡፡ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ያሉ አውደ ርእሶች በሙሉ በማሰተማሪያ ምንባብነት በመማሪያ መጽሃፉ ላይ የወጡ ናቸው፡፡ ይዘቶቹ በሁለት መንፈቅ አመት ተከፍለው የቀረቡ ሲሆን ይህም በመማሪያ መጽሃፍ ላይ በተመሳሳይ ተግባራዊ ሁኗል፡፡

መርሃ ትምህርት በተግባር ሊገለጽ የሚችል የመማር ማስተማር ክንውን ማሳያና የስርአተ ትምህርት አካል ሲሆን በተግባር የሚታየውም መገለጫው በሆነው መማሪያ መጽሃፍ አማካኝነት ነው፡፡ ይህም የመርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሃፉ የጠበቀ ግንኙነት ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ትልቅ ድርሻ እንዳለው (Richard, 1987) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የቃላት ትምህርቶችን በተመለከተ በመማሪያ መጽሃፉና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ ለማረጋገጥ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል፡፡

ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ውስጥ የሚነሱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከመማሪያ መጽሀፉ ጋር መናበብ መቻል አለባቸው፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ የተጠቀሱት ይዘቶች የመስፋትና የመጥበብ ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በመርሃ ትምህርቱ ተገቢነት ያላቸው የቃላት

ትምህርት አላማዎች ተመርጠው በግልጽ ከሰፈሩ በኋላ ግብ ማስመቻ የሚሆኑ ተስማሚ ይዘቶች ይመረጥላቸዋል፡፡ ይህ ተግባራዊ የሚደረገው ደግሞ በመማሪያ መጽሃፉ አማካኝነት እንደሆነ ይታወቃል፤

በመቀጠል በመርሃ ትምህርቱ ‹‹ብቃት›› የሚለውን ተግባራዊ ለማድረግ የተመሳሳይና የተቃራኒ ቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ፤ የቃላትን ፍቺ በተለያዩ አውዶች ውስጥ ይጠቀማሉ፤ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ይጠቀማሉ፤ ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን አንብበው ይጠቀማሉ ፤ እንዲሁም ሀሳባቸውን ለመግለፅ ዘይቤ ይጠቀማሉ ፤ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ ነጠላና ብዙ ቁጥር በትክክል ይጠቀማሉ ወዘተ የሚሉት የቃላት ትምህርት አላማዎች ‹‹ብቃት›› ላይ ቀርበው እናገኛለን፡፡

በተጨማሪም የመማር ስልቶች ላይም ከተቃራኒያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ፣ የቃላትን ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ማድረግ ፣ የመሸጋገሪያ ቃላትንና አጣማ ቃላትን እንደሚጠቀሙ ማድረግ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሀሳባቸውን ለመግለፅ ዘይቤያዊ አገላለፆችን እንዲጠቀሙ ማድረግ አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ ነጠላና ብዙ ቁጥርን እንዲጠቀሙ ማድረግ የሚሉት የቃላት ትምህርቶች በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተገለጹበት አግባብ እንዳለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህን ጠቅለል አድርገን በመርሃ ትምህርቱ ተካተው በመማሪያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት አቅረቦት ስር ያሉትን ተግባራት በቁጥር በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## ሰንጠረዥ 8፡ በመርሃ ትምህርቱ ተካተው በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ የቃላት ተግባራት ብዛት በቁጥር

| ተ.ቁ | በመርሃ ትምህርቱ የተካተቱ የቃላት ትምህርቶች | በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ የቃላት ተግባራት ብዛት በቁጥር | በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ የቃላት ተግባራት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1 | የቃላት እርባታና ምስረታ ስርአትን መሰረት አድርገው የቀረቡ ተግባራት | 17 | 6.16 |
| 2 | ዘይቤያዊ ቃላት | 6 | 2.17 |
| 3 | ከፍቺ ተዛምዶ አንጻር የቀረቡ የቃላት ተግባራት | 81 | 29.35 |
| 4 | የቃላትን ፍቺ ከማስተማር አንጻር ከቀረቡት ምንባብ አውዶች የወጡ የቃላት ተግባራት | 50 | 18.12 |
| 5 | መሸጋገሪያ ቃላት | 15 | 5.43 |
| 6 | ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ለማስለየት የቀረቡ የቃላት ተግባራት | 51 | 18.48 |
| 7 | ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች | 16 | 5.79 |
| 8 | የቃላትን ፍካሬያዊ ፍቺ ለማስተማር የቀረቡ | 11 | 3.99 |
| 9 | አዳዲስ ቃላትን ለማመሳከር መዝገበ ቃላትን እንዲጠቀሙ የሚያደርግ | 29 | 10.51 |
| ጠቅላላ ድምር | | 276 | 100 |

የቃላት እርባታና ምስረታ መሰረት አድርገው የቀረቡ የቃላት ተግባራት በጠቅላላው 17(6.16%) ሲሆኑ የተለያዩ ቅጥያዎችን በመጨመር አዳዲስ ቃላትን እንዲመሰርቱ የሚለው የቃላት ተግባራት እንዳለ በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል፡፡ በተለያየ መደብና ጾታ እንዲያረቡ የሚያድረጉና የቃላትን ቅርፅ በመቀያየር የተለያዩ ቃላትን እንዲመሰርቱ የሚሉት ተግባራት በሰንጠረዥ 6 የተገለጸ ሲሆን በመማሪያ መፅሀፉም ሆነ በመርሀ ትምህርቱ አልቀረበም፡፡ የቃላት እርባታና ምስረታ ስርአትን መሰረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች ማቅረቡ የቃላቱን ትርጉም ለመረዳትም ሆነ አፍልቆ መጠቀም እንዲችሉ መሰረት እንደሚጥልላቸው ተጠቁሟል፡፡ በዚህ ረገድ መማሪያ መጽሃፉና መርሃ ትምህርቱ ተጣጥሞሽ እንደሌላቸው በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከፍቺ ተዛምዶ አንጻር 81(29.35%) የቃላት ተግባራት እንዳሉ ከላይ የቀረበ ሲሆን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ለማስለየት 51(18.48%) የቃላት ተግባር እንደተካተቱም ታውቋል፡፡ ከነዚህ

ውስጥ ፍቺቻውን እንዲያዛምዱ ተደርገው የቀረቡ የቃላት ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ እንዳሉ በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ‹‹አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ ይጠቀማሉ በሚል  የቀረቡ›› በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተጠቀሰው አላማ በዚህ ስር የሚካተት ይሆናል፡፡ በመሆኑም መርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሃፉ በዚህ ረገድ እንደሚጣጣሙ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም የቃላትን ፍቺ በተለያዩ አውዶች ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡ በማለት በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተገለጸ ሲሆን በመማሪያ መጽሀፉም የቃላትን ትምህርት አውድን አስደግፎ ማቅረብን የተመለከቱ የቃላት ተግባራት አጠቃላይ 50(18.12%) እንዳሉ፣ እነዚህም ምንባቦችን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ የቃላት ተግባራት እንደሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር ተጣጥሞሽ እንዳላቸው እንረዳለን፡፡

በአንጻሩ ደግሞ አዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመማር ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ፍቺ ለማወቅ መዝገበ ቃላትን እንዲጠቀሙና ፣ መዝገበ ቃላት አጠቃቀምን ተግባራዊ ማድረግ ወዘተ በማለት በመማሪያ መፅሀፍ ላይየተጠቀሱ የቃላት ትምህርቶች እናገኛለን፡፡ እነዚህ ከመዝገበ ቃላት ጋር ተያይዘው የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች በመርሀ ትምህርቱ ላይ እንዳልተካተቱ ተረጋግጧል፡፡ ተማሪዎች መዝገበ ቃላት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የሚያሳይና የአጠቃቀም ጥበቡን በማለማመድ ላይ ትኩረት አድርጎ የቃላቱን ፍቺ እንዴት መፈለግ እንዳለባቸው የሚጠቁም የቃላት ተግባር አካቶ ከማስተማር አንፃር  በመርሃ ትምህርቱ ላይ ሳይቀርብ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ መካተቱ በዚህ ረገድ ተጣጥሞሽ እንደሌላቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡

ጥምር ቃላትን እንደሚጠቀሙ በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተገለጸ አላማ እንደሌለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የቃላት ትምህርቶች ተግባራት ተቀርጾላቸው በመማሪያ መፅሀፉ እንደቀረቡ በሰነድ ፍተሻው ማርጋገጥ ተችሏል፡፡ መማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ የሚመሰረተው በመርሃ ትምህርቱ አላማ ላይ ነው፡፡ አላማውን ተግባራዊ ማድረግ ካልቻለ ግን በሁለቱ ሰነዶች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ መሆኑን ያመላክታል፡፡ የዚህም ውጤት በትምህርት ስኬታማነት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር መረዳት ይቻላል (Dubin and Olishtian, 1992) በማለት ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም የመሸጋገሪያ ቃላትን አገልግሎታቸውን ከመረዳትና ቃላቱን ከንግግርና ከፅህፈት ጋርም በማያያዝ ተማሪዎች ሲጽፉና ሲናገሩ እንዲጠቀሙባቸው የሚስችሉ ተግባራትን

በመቅረጽ ማለማመድ የተመለከቱ ተግባራት በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ርእሰ ጉዳዩን አስመልክቶ በመቅረቡ ተጣጥሞሽ ያላቸው መሆኑን የተገኘው ውጤት ያስረዳል፡፡

እንዲሁም በመርሃ ትምህርቱ ላይ ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮች አንብበው ይጠቀማሉ፥ ሀሳባቸውን ለመግለፅ ዘይቤ ይጠቀማሉ፡፡ ሀሳባቸውን ለመግለፅ የቃላትን ፍካሬያዊ ፍችን ይጠቀማሉ ወዘተ በማለት የቀረቡት የቃላት ትምህርት አላማዎች በመማሪያ መጽሀፉ ተግባር ተቀርጾላቸው የተካተቱ መሆናቸውን በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል፡፡ ፈሊጣዊ አነጋገሮች በቋንቋ ውስጥ ካላቸው የተለየ ባህርይና ከሚሸከሙት የተለየ ፍቺ አንፃር በመርሃ ትምህርቱ ላይ መካተቱ ተማሪዎች አውቀው እንዲጠቀሙባቸው በመማረያ መጽሃፉም ተግባራት ተቀርጾላቸው መቅረቡ ተጣጥሞሽ እንዳላቸው በሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ከማስተማር አንጻር በመርሃ ትምህርቱ ተካቶ በመማሪያ መጽሃፉም እንደተካተተ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች መማሪያ መጽሃፉ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር መጣጣሙን ወይም መስማማቱን ማረጋገጥን እንደዋነኛ ስራቸው አድረገው መውሰድ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም መርሃ ትምህርት ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስለሚጠቁም መማሪያ መጽሃፉም በዚያ ላይ ካልተመሰረተ የመማር ማስተማሩን ሂደት በስርአት ለመምራት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡

ከዚህ አንጻር መማሪያ መጽሀፉ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር አብዛኛው ቦታ ላይ ተጣጥሞሽ እንዳላቸው ከላይ በመረጃ አስደግፎ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብና ከማለማመድ አንጻር በመማሪያ መፅሀፉ ላይተካቶ በመርሀ ትምህርቱ ያልተካተተ ፤ይሁን እንጂ መሸጋገሪያ ቃላትን ለይተው በአገባብ ደረጃ እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንጻር፣ የፈሊጦችን ትርጉም አውቀው በክፍልም ከክፍል ውጪ ባለው ማህበራዊ አጠቃቀም ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር፣ እንዲሁም የቃላትን እማራዊና ፍካራዊ ፍቺን ከማስለየት አንጻር ተጣጥሞሽ እንዳላቸው የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተተኳሪውን መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን ከሙህራኑ ሀሳብ ጋር በማዛመድ የተገኙ ውጤቶች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

የቃላት ትምህርት ይዘት መምረጫ መስፈርት አስመልክቶ የቃላት ድግግሞሽ መጠን፣ ተስተማሪነት፣ የፍቺ ሽፋን፣ በቅርበት መገኘት፣ የተማሪዎች ፍላጎትና የብስለት ደረጃ ወዘተ የሚሉትን ከግምት በማስገባት መምረጥ እንደሚቻል (Gairns and Redman, 1986 and McCarthy, 1990) ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶች እነዚህን የቃላት መምርጫ ዘዴዎችን መሰረት በማድረግ መመረጣቸውን ለማረጋገጥ የሰነድ ፍተሻ ተደርጓል፡፡

በጥናቱ ውጤትም ሙህራኑ ከሰነዘሯቸው መስፈርቶች መካከል አንድ ቃል ሰፊ የአገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ባይኖረውም እንኳ ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርቡ ምንባቦች ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት ሁኔታ (በቅርበት የመገኘት) መስፈርት ግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡ ሌሎች ማለትም የቃላቱ ተዘውታሪነት በድግግሞሽ ጥናት የመለየት፣ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ አሰሳ ጥናት የማካሄድ፣ የቃላቱን የተስተማሪነት ደረጃ የመለየት ወዘተ በሚሉት መስፈርቶች ላይ ተመርኩዞ የቃላት ትምህርትን የመምረጥ ጉዳይ ተገቢ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተ የተለያዩ የቃላት ትምህርት ማደራጃ ስልቶች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ በፍቺ ተዛምዶና በቅርጽ ተመሳስሎ የሚሉትን መሰረት በማድረግ ማደራጀት እንደሚቻል በዋናነት ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርቶቹ እንዴት እንደተደራጁ ለማረጋገጥ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ከፍቺና ከቅርጽ አንጻር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንደተደራጁ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ግን የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

ከቃላት ማቅረቢያ መንገዶች አንጻር ቃላትን በአውድ አሰደግፎ ማቅረብ፣ በፍቺ ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ፣ የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን ተመርኩዞ ማቅረብ፣ ቃላዊ ሀረጎችን

ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ፣ በመዝገብ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ እንዲሁም የቃላት ትምህርትን ግልጽ በሆኑ መመሪዎች ማቅረብ የሚሉት ቀርበዋል፡፡

ቃላትን በአውድ አስደግፎ ከማቅረብ አንጻር 50(18.12%) የቃላት ተግባራት እንዳሉና ከነዚህም ውስጥ በተመሳስሎና በተቃርኖ የቀረቡት ከፍተኛ ሽፋን እንደተሰጣቸው መረጃው ያሳያል፡፡ እንዲሁም ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካኝነት ማቅረብን በሚመለከት 81(29.35%) ተግባራት መካከልየቃላት አብሮተሰላፊነትን የሚያሳይ እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ከፍቺ አንጻር የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነትን፤የድምጽ መጥበቅና መላልት የተለያየ ፍቺ መስጠትን ፤ የሚያሳዩ ተግባራት በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ እንዳልቀረቡ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡

ፈሊጦች፣ ጥምር ቃላት፣ እንዲሁም መሸጋገሪያ ቃላት፤ ቃላዊ ሀረጎች ስር እንደሚመደቡ እነዚህን ቃላት ለትምህርትነት ማቅረብ ደግሞ  በቀላሉ ሊታወሱ ከመቻላቸውም በላይ ተማሪዎች በነጠላ ቃል ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸው፣ እንዲሁም በቋንቋው በሚገባ መግባባት እንዲችሉም እገዛ እንደሚያደርግላቸው ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ትምህርቶቹ በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ተግባራት ተቀርጾላቸው ለትምህርትነት እንደቀረቡ በሰነድ ፍተሻ ተረጋግጧል፡፡

ቃላትን ከክሂሎት ጋር አጣምሮ ማቅረብ በተመለከተ በአጠቃላይ 61(22.1) ተግባራት ያሉ ሲሆን እነዚህ የቃላት ተግባራት ከአንብቦ መረዳት ጋር እና ከመጻፍ ክሂል ጋር ተጣምረው የቀረቡ ናቸው፡፡ ከማድመጥና ከመናገር ክሂል ጋር ግን የቀረቡ የቃላት ትምህርቶች እንደሌሉ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል፡፡

በመዝገበ ቃላት አስደግፎ የቃላት ትምህርትን ማቅረብና ማለማመድ አስፈላጊ እንደሆነና የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ትምህርት የማንኛውም መርሀ ትምህርት ዋና አካል መሆን እንዳለበት በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የጎላ ሲሆን ተማሪው መምህሩን ወይም ጓደኛውን ጠይቆ መረዳት በማይችልበት ወቅት መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ችግሩን ሊፈታ እንደሚችልም

ተጠቁሟል፡፡ስለዚህ የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሃፉ የተካተቱ ተግባራት እንዳሉ መረጃው ያሳያል፡፡

የቃላት ትምህርት ተግባራት ግልፅና በተብራራ መመሪያዎች ተደግፈውና አስፈላጊውን ምሳሌ የያዙ ሁነው ሊቀርቡ እንደሚገባ Eyraud (2000:3) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የቃላት ተግባራቱ የቀረቡባቸው መመሪያዎች ሲፈተሹ አብዛኛው ግልጽና የማያሻሙ ሁነው የቀረቡ ሲሆን ጥቂት መመሪያዎች ግን ግልጽነት እንደሌላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመማሪያ መጽሃፉና መርሃ ትምህርት መካከል ያለውን ተጣጥሞሽ አስመልክተው Dubin and Olishtian (1992፡168) ሲገልጹ የማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች መማሪያ መጽሃፉ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር መጣጣም ወይም መስማማት እንደሚገባው ማረጋገጥን እንደዋነኛ ስራቸው አድረገው መውሰድ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም መርሃ ትምህርት ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስለሚጠቁም መማሪያ መጽሃፉ በዚያ ላይ ካልተመሰረተ የመማር ማስተማሩን ሂደት በስርአት ለመምራት አስቸጋሪ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆነም የቃላት ትምህርት ይዘትን አስመልክቶ መማሪያ መጽሃፉና መርሃ ትምህርቱ አብዛኛው ቦታ ላይ የተጣጣሙ ናቸው፡፡ እንደሚጣጣሙ፣ ነገር ግን የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር በመማሪያ መፅሀፉ ተጠቅሶ በመርሀትምህርቱ ውስጥ አልተጠቀሰም፡፡ የፈሊጦችን ፍቺ ከማስተማር፣ የመሸጋገሪያ ቃላትን አገልግሎት ከማስተማር፣ እንዲሁም የቃላት ፍካራዊ እና እማሬያዊ ፍቺ ከማስተማር አንጻር በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተጠቅሶ በመማሪያ መጽሃፉ ውስጥም የተካተቱ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ተጣጥሞሽ እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተተኳሪውን መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን አብይ አላማ ከግብ ለማድረስ አራት ዝርዝር አላማዎች የጥናቱን ዋና አላማ መሰረት አድርገው ተዘጋጅተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለትም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ሙህራንን ሃሳቦች የያዙ በርካታ ድርሳት በስፋት ተቃኝተዋል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገናኙ ጥናታዊ ጽሁፎችም ተዳሰዋል፡፡

በምዕራፍ ሶስት ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሰነድ ፍተሻ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ መረጃውን ለመሰብሰብም ተተኳሪው መማሪያ መጽሃፍና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ በሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ በማስቀመጥ በገለጻ ስልት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በምዕራፍ አራት ከቀረበው ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው በደቡብ ምዕራብ ክልል በ2015 ዓ.ም ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ታስቦ የተዘጋጀው አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አንፃር ሲታዩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው የቀረቡ በመሆኑ በጠንካራ ጎን የሚነሳ ነው፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርቶችን ቋንቋ ለጠቅላላ ዓላማ ለማስተማር ታስቦ ለሚነደፍ መርሃ ግብር እንዲውሉ ከሰነዘሯቸው መስፈርቶች መካከል አንድ ቃል ሰፊ የአገልግሎት ሽፋንና ስርጭት ባይኖረውም እንኳ ለቋንቋ ማስተማሪያነት በሚቀርቡ ምንባቦች ውስጥ የተለየ አስፈላጊነት ይዞ ሲገኝ የሚመረጥበት ሁኔታ (በቅርበት የመገኘት) መስፈርት ግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡ ሌሎች ማለትም የቃላቱ ተዘውታሪነት በድግግሞሽ ጥናት የመለየት፣ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ አሰሳ ጥናት የማካሄድ፣ የቃላቱን የተስተማሪነት ደረጃ

የመለየት ወዘተ የሚሉት መስፈርቶች ላይ ተመርኩዞ የቃላት ትምህርትን የመምረጥ ጉዳይ ተገቢ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተ ቅርጽና ፍቺን መሰረት አድርጎ በርካታ ተግባራት እንደተደራጁ መረጃው ያስረዳል፡፡ ነገር ግን ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ቃላትን ማደራጀት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያመለካታል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የቃላት ትምህርት አደረጃጀት የመማር እድገቱን የጠበቀ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ከቀላል ወደ ከባድ ቀስ በቀስ እያደጉ የሚሄዱ በመሆናቸው በጠንካራ ጎን የሚጠቀስ ነው፡፡

በተጨማሪም ከፍቺ አንጻር በአረፍተ ነገራዊ አውድ የቀረቡት የቃላት ተግባራት የቃላትን ትርጓሜ በገቡበት ቦታ ለመገመት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች ይዘው ቀርበዋል፡፡ ሌላው ፈሊጦችን፣ ጥምር ቃላትንና መሸጋገሪያ ቃላትን በተመለከተ  ሽፋን ተሰጥቷቸው በመቅረባቸው መማሪያ መጽሐፉ በዚህ ረገድ ትኩረት  እንደተሰጣቸው መረጃው ይጠቁማል፡፡ እነዚህ የቃላት ትምህርቶች ከመረጣው ጀምሮ ታስቦባቸው እንደተደራጁና እንደቀረቡ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ መማሪያ መጽሀፉ ድክመት እንደለለበት የጥናቱ ውጤት ያስረዳል፡፡

ከአረፍተ ነገራዊ አውድ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ የአረፍተ ነገሮች እርዝማኔ ነው፡፡ በዚህ መልክ የቀረቡት የቃላት ተግባራት አብዛኛው ከመለኪያው አንጻር ምንም ችግር የሌለባቸው ሲሆኑ በአንድ የቃላት ተግባር ላይ ግን ከአስራ አንድ ቃላት በላይ በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ በመዋቀራቸው ችግር እንዳለባቸው ተረጋግጧል፡፡ ሌሎቹ ግን ከ5-10 ባሉ ቃላት የተገነቡ በመሆናቸው በጠንካራ ጎን የሚነሳ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የቃላቱን ፍቺ በቀላሉ መገመት እንዲችሉ ከማድረግ አንጻር ጉልህ ድርሻ እንዳለውም ተገልጿል፡፡

ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካኝነት ማቅረብን በተመለከተ አብዛኛው በዚህ ሥር የቀረቡት በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱ መሆናቸው በጠንካራ ጎን የሚነሳ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ከፍቺ ዝምድና አንጻር የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነትን ፤በድምጽ መጥበቅናመላላት የተለያየ ፍቺ መስጠትን ፤የቃላት አብሮ ተሰላፊነት የሚያሳዩ ትምህርቶች እንዳልቀረቡ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ ረገድ መማሪያ መጽሃፉ ድክመት እንዳለበት የጥናቱ ውጤት ያስረዳል፡፡

ቃላትን ከክህሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብን በተመለከተ አብዛኛው የቃላት ትምህርት በአንብቦ መረዳት ላይ እንደቀረቡና የተወሰኑት ደግሞ ከመጻፍ ክሂል ጋር አብረው እንደተካተቱ ማረጋገጥ ተችሏል። ከማዳመጥና ከመናገር ክሂል ጋር ግን የቀረቡ የቃላት ተግባራት ባለመኖራቸው በዚህ ረገድ መማሪያ መጽሃፉ ውስንነት እንዳለበት ጥናቱ ያመላክታል።

የቃላትን ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንጻር ተማሪዎች የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብን አውቀው እንዲጠቀሙ የሚያደርግ የቃላት ተግባር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካቷል። በአንጻሩ ደግሞ የቃላት ትምህርቱ የቀረቡባቸው መመሪያዎች በተመለከተ አብዛኞቹ በተገቢ ማብራሪያዎችና ምሳሌዎች በመደገፍ ግልጽ ሁነው የቀረቡ በመሆናቸው በጠንካራ ጎን የሚነሳ ነው። ጥቂት መመሪያዎች ግን ከግልጽነት አንጻር ክፍተት እንዳለባቸው መረጃው ያስረዳል።

በመጨረሻም መማሪያ መጽሀፉና መርሃ ትምህርቱ መካከል ያለው የቃላት ትምህርት በተመለከተ አብዛኛው ተጣጥሞሽ እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብና የአጠቃቀም ጥበቡ እንዲያውቁ ከማድረግ፣ የተለመዱ አገላለጾችን (መሸጋገሪያ ቃላትን) ለይተው እንዲጠቀሙ ከማድረግ፣ የፈሊጦችን ፍቺ አውቀው እንዲጠቀሙ ከማድረግ፣ እንዲሁም የቃላትን እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲለዩ ከማድረግ አንጻር በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ቀርበው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያልተካተቱ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ተጣጥሞሽ እንደሌላቸው በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል።

## 5.2. አስተያየት

ከዚህ በላይ በማጠቃለያው የተገለጹትን የጥናት ውጤቶች መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጽሀፉ የታዩ ጠንካራ ጎኖች እንደተጠበቁ ሁነው ክፍተት በታየባቸው የመጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ የሚከተሉትን አስተያየቶች ለመሰንዘር ተሞክሯል።

ሀ. የቃላት መረጣ ሲካሄድ በተቻለ መጠን ቋንቋ ለጠቅላላ ዓላማ ለማስተማር ታስቦ ለሚነደፍ መርሃ ግብር እንዲውሉ በመስኩ ምሁራን ለተሰነዘሩት የቃላት መምረጫ መስፈርቶች ተገቢ ትኩረት ቢሰጥ፤ እንዲሁም ለትምህርትነት የሚቀርቡት የቃላት ተግባራት

ማስተማሪያ ምንባቦች ውስጥ ብቻ ባይወሰኑ፣ ከምንባቡ ውጭም ተገቢ የሆነ አውድ ተፈጥሮላቸው ቢቀርቡ፤

ለ. የቃላት ትምህረት አደረጃጀትን በተመለከተ ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ቃላትን ማደራጀት የሚለው መስፈርት የተሰጠው ሽፋን አነስተኛ በመሆኑ ሚዛናዊ አድርጎ ለማደራጀት ቢሞከር፤

ሐ. በመርሀ ትምህርት ላይ ቃላትን በተለያየ መደብና ጾታ እያረቡ መጻፍ የሚመለከቱ ተግባራት ቢካተቱ፤እንዲሁም የድምፅ መጥበቅና መላላት የሚሉ ተግባሮች ቢካተቱ፤

መ. በመርሀ ትምህርት ላይ ቃላትን በተለያየ ቅርጽ በመጻፍና በማራባት እንዲሁም ለሎች ቃላትን መመስረት የሚሉትን ተግባራት መካተት ቢችሉ፤

ሠ. የቃላት የከታች ተከታች ፍቺ ዝምድናን የሚያሳዩ የቃላት ተግባራት ተነድፈው ቢካተቱ፤

ረ. ከማድመጥና ከመናገር ኪሂል ጋር የቃላት ትምህርትን አጣምሮ ከማቅረብ አንጻር ድክመቱ ቢስተካከል፤

ሰ. ሁሉም የቃላት ትምህርት መመሪያዎች እያንዳንዱን የአሰራር መንገድ የሚጠቁሙ ግልጽና የተብራሩ ምሳሌዎችን ያካተቱ ቢሆኑ፤ በተወሰኑ የቃላት ተግባራት ላይ የቀረቡ መመሪያዎች ግልጽ ቢሆኑ፤

ሸ. መማሪያ መጽሀፉ መርሀ ትምህርቱ ላይ የተመረኮዘ እንዲሆን ጥረት ቢደረግ፤ ማለትም መማሪያ መጽሀፍ የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር መጣጣሙን ወይም መስማማቱን ማረጋገጥ ቢችሉ የታዩ ክፍተቶችን መቅረፍ ይቻላል፡፡

ቀ. በመጽሃፉ በምዕራፍ ሦስት ስር የቃላት ተግባራት የሚል  የለዉም ማለትም ሰዋሰው ብቻ ይገኙበታል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ምንውየለት ደነቀው፡፡ (2005)፡፡ ‹‹በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍት የቃላት ትምህርት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና›› ለማስተርስ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ሞላ አጽብሃ፡፡ (2003)፡፡ ‹‹በትግራይ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና›› ለማስተርስ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2000)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡ (*2ኛእትም)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ እሌኒ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ ሽዋዬ፡፡ (1981)፡፡ ስነ ልሳን ቋንቋ ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያልታተመ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር እና የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡ (2007)፡፡ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪው መጽሃፍ 8ኛ ክፍል፡፡ ኤች ዋይ ማተሚያ ቤት፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር እና የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡ (2007)፡፡ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህሩ መምሪያ 8ኛ ክፍል፡፡

ንጋቱ አሰፋ፡፡ (2000)፡፡ ‹‹በሲዳምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሀቶች ምርመራ›› ለማስተርስ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

አንበሴ በቀለ፡፡ (1993)፡፡ ‹‹በኦሮሚያ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ትንተና›› ለማስተርስ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡

አፈወርቅ ይስሀቅ፡፡ (2008)፡፡ *‹‹ጋሞ ጎፋ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፈ ፈት እና ኢ-አፈ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላት የመማር ብልሀቶች ትንተና››* ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (*ያልታተመ*)፡፡

የኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ (1993)፡፡ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ (1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ፡፡* አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

Alizadeh,I.(2016). Vocabulary Teaching Techniques: A Review of Common Practices. *International Journal of Research in English Education.*

Allen, V.F. (1983). *Techniques in Teaching Vocabulary*. Oxford: Oxford University Press.

Bauer, L. (1998). *Vocabulary*. London and New York: Routledge.

Biber,D. Conard,S. and Reppen,R. (1998). *Corpus Linguistic: Investigating Language Structure and Use*. Cambridge University Press.

Carter, R. and McCarthy, M. (1988). *Vocabulary and Language Teaching.*New York: Longman.

Creswell, J.W. (2012). *Educational Research*: Planning, Conducting, and Evaluating Quantitative and Qualitative Research. (4th ed). Pearson Education Inc.

Cunningsworth, A. (1995). *Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials.*Oxford: Heinemann International.

Curtis, M.E. and Longo, A.M. (2001). Teaching Vocabulary to Adolescents to Improve Comprehension. *Reading Online, 5(4). Available;* http;//www. Reading online. Org/articles/ art-index Asp? HREF-Curtis/ index htm.

Diedrichs, J. (2005). Teaching Vocabulary*:* The Study of a Case. Curitiba.

Dubin, F. and Olshtain. (1992). *Course Design: Developing Programmers' and Materials for Language Learning* ($6^{th}$ed). Cambridge University Press.

Elyas.T. and Alfaki.I (2014).Teaching Vocabulary: *The Relationship between Techniques of Teaching and Strategies of Learning New Vocabulary Items.*Canadian Center of Science and Education.

Eyraud, K. (2000). The word wall Approach: Promoting L2 Vocabulary learning .*English Teaching Forum.Vol.38,* No. 3, pp.1-11.

Ferreira,F. (2007) How to Teach Vocabulary Effectively An Analysis of The Course Book Eyes and Spies. Praia.

Gairns, R. and Redman S. (1986). *Working with Words: A Guide to Teaching Vocabulary.* Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* New York: Longman Group Ltd.

Hunt, A. and Belgar D. (2002). Current Research and Practice in Teaching Vocabulary. *Methodology in Language Teaching: an Anthology of Correct Practice.* Cambridge: Cambridge University Press.

Jill, H. and Charles H. (2008) *Introduction to Teaching English.* Oxford University Press.

Larsen, K. (2017). Vocabulary and EFL Textbooks. Master's Thesis Department of Foreign Languages. University of Bergen.

Lewis, M. (1993). *The Lexical Approach*. London: Commercial Color Press.

McCarten, J. (2007). Teaching Vocabulary; *Lesson From The Corpus Lesson for The Classroom*. www.cambridge.org.

McCarthy, M. (1990). *Vocabulary.* Oxford: Oxford University Press.

McCrostie, J. (2007). Examining Learner Vocabulary Note Books. *ELT Journal*, 61(3).

Nation, P. (2000). Designing and improving a language Course. *English Teaching Forum.Vol3.* No. 4m pp2-11.

Nation, P. and Coady, J. (1988) Vocabulary and Reading. *Vocabulary Teaching Looking Behind The Word. ELT Journal*. V.50, No.1, pp, 52-58.

Nattinger, J.R. and Decarrico, J.S. (1992). *Lexical Phrases and Language Teaching.* Oxford: Oxford University Press.

Nunan, D. (1991). *Language Teaching Methodology.* A Text Book for Language Teachers. Edinburgh Pearson Education Ltd.

Nurullah, M.(2014). A Comparative Study of Teaching Vocabulary Through Pictures and Audio-visual Aids to Young Iranian EFL Learners.*Journal of Elementary Education Vol.24*, No. 1.

Pikulski and Templeton, S. (2004). Teaching a Developing Vocabulary: *key to long-term Reading Success.* http:// www.eduplace. Com /state/ author/ pick temp.

Rajaee, M. (2013).The Effect of Strategy Training on The Vocabulary Development of ESL Learners in Public High School of Iran. *Theory and Practice in Language Studies, Vol.3*.

Richards J.C. (1987).*The Context of Language Teaching.* Cambridge University Press.

Richards J.C. (2009). *Curriculum Development in Language Teaching.* (12thed). Cambridge University Press.

Scrivener, J. (1998). *Learning Teaching.* Oxford: Macmillan Publishers Limited.

Seffar, s. (2014). An Exploratory Study of Vocabulary Learning Strategies of Moroccan University Students. *(IOSR-JRME).Vol.4.*Issue.

Seno, M.(2007). Teaching Vocabulary to Secondary School Students Through Games. Master of Arts Programmed Thesis. Seljuk University.

Su, L. (2010). Vocabulary Learning Beliefs, Strategies and Language learning Out Comes. AUTEC R.No.091179.

Ur, P. (2006). *A course in Language Teaching: Practice and Theory*. (17th ed).Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, M. (1988). *Teaching vocabulary*. Oxford: Heinemann Educational Books Ltd.

Ying, Y.S. (2001). Acquiring Vocabulary Through a context Based Approach.*"English* Teaching Forum. Vol. 39, No.2, pp.18-21.

# አባሪዎች

*አባሪ አንድ*

*አስረጅ 1*

***መልመጃ አንድ፤ ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበውላችኋል በአረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት አውዳዊ ፍቻቸውን አመልክቱ።***

ሀ. ባተሌ
ለ. ማነቆ
ሐ. መጎናፀፍ
መ. መና
ሠ. ማሰላሰል
ረ. እውን

ገፅ 9.

*አስረጅ 2.*

***መልመጃ ሁለት ክፍል ሶስት በቀረበው ምንባብ መሰረት በ "ሀ" አምድ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ"ለ" አምድ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።***

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. መባከን | ሀ. መሰናክል |
| ፪. እፁብ ድንቅ | ለ. ወጣት |
| ፫. መደመም | ሐ. መልፋት |
| ፬. ማጋበስ | መ. መሰብሰብ |
| ፭. ጉብዛና | ሠ. ወጣ ያለ |
| ፮. አረጋዊ | ረ. መደነቅ |
| ፯. አፈንጋጭ | ሰ. አስገራሚ |
| ፰. እንቅፋት | ሸ. ወጣትነት |
| | ቀ.የእዴሜ ባለፀጋ |

(ገጽ፣ 9)

*አስረጅ 3.*

*መልመጃ አንድ፤*

*ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበውላችኋል። አረፍተ ነገር በመመስረት አውዳዊ ፍቻቸውን አመልክቱ።*

| | |
|---|---|
| ሀ. ጓዳ | ሠ. ዝና |
| ለ. እማወራ | ረ. መጠለል |
| ሐ. አባወራ | ሰ. ባሌትና |
| መ. ማበርከት | ሸ. ሙሴሙሴ ገፅ 9. |

*አስረጅ 4.*

*መልመጃ ሁለት*

*በ "ሀ" አምዴ ለተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በ'ለ" ካለት በመምረጥ አዛምዱ።*

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ወገግታ | ሀ. ቦታ፣ ሁኔታ |
| ፪. ቀዳሚ | ለ. ሀያ አምስት ሳንቲም |
| ፫. መገለጥ | ሐ. ምሳላ |
| ፬. አውራጅ | መ. መታየት |
| ፭. ማብሰር | ሠ. አቀንቃኝ |
| ፮. ስሙኒ | ረ. መጀመሪያ |
| ፯. አውድ | ሰ. ፀዳል |
| ፰. አብነት | ሸ. መንገር ገጽ፣ 21) |

*አስረጅ 5*

*መልመጃ ሁለት*

*ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ አዳዲስ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃቱቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሰረት ፍቻቸውን ስጡ፡፡*

ምሳሌ፡-

ዋልጌ፡- ባለጌ

ወሸካታ፡- ለፍላፊ

ሀ. ቀዬ　　　　ሠ. አንከርፍፌ

ለ. ትከረክማለች　　　　ረ. ክፈፍ

ሐ. ቦሃ　　　　ሰ. ኦጽላስ

መ. እየገደፉ　　　　ገፅ 31.

*አስረጅ 6*

*መልመጃ ሶስት*

*ከዚህ በታች ከምንባቡ የወጡ ቃላት በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ቃላት በመምረጥና ባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት አረፍተ ነገሩን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጉፍታ | ማገር | ቀዬ | የቂም ዶሴ | ዋልጌ |
| ፊት ማሳየት | ወሸካታ | ልሀቀት | ጥሩር | የምንለጠለጥበት |

፩. አዛውንቶችን የማያከብር ልጅ በማህበረሰቡ___ተብሎ ሊነቀፍ ይችላል፡፡

፪. ልጆች ሲያጠፉ በጎረቤቶቻቸው ቢገሰጹ______ አይቋጥሩም፡፡

፫. የዘምዘም ____________ ሰማያዊ እና ለስላሳ ነው፡፡

፬. ብዙ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ከኖሩበት _____ሊሰደዱ ይችላሉ፡፡

፭. ያለ የሌለውን ነገር የሚለፈልፍ ሰው _ተብሎ በሰዎች ሊገሰጽ ይችላሉ፡፡

፯. የአእምሮ ____________ መኖር አካባቢንና ሀገርን ያሳድጋል፡፡

፯. ለልጅ _______________ ልጅን ማቅበጥ ነው ብለው ያስባሉ፡፡

፰. ወታደሮቹ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ -------------ለበሱ፡፡

(ገጽ፣ 32)

**አስረጅ 7.**

**መልመጃ አንድ፤ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ጥምርቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| መቅረፀ-ድምጽ | ሰላማዊ ሰልፍ | አውራ ጎዳና |
| ብርድ ልብስ | ቤተ-መንግስት | ትምህርት ቤት |
| ብረት ምጣድ | ሽክላ ድስት | አየር መንገድ |

፩. ኢትዮጵያውያን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ስላስደሰታቸው------------------አካሄዱ፡፡

፪. አሜሪካ ኢምባሲ ቅጥር ግቢ ውስጥ-------------------ይዞ መግባት አይቻልም፡፡

፫. እናቴ ዶሮ ወጥ የምትሰራበት----------------------ገዛች፡፡

፬. ሀሴት የገብስ ቆሎ ለመቁላት ከጎረቤቷ----------------------ተዋሰች፡፡

፭. ጽዱ እና ውብ የሆነው የአንድነት ፓርክ መገኛ ቦታው---------------------ነው፡፡

፮. ከአዲስ አበባ ወደ ሀዋሳ የሚወስው------------------በመፍረሱ እየተጠገነ ነው፡፡

፯. የኢትዮጵያ-------------------------፡፡

ሰራተኞች ስራቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነው፡፡

ገፅ 33.

*አስረጅ 8.*

*መልመጃ ሁለት በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ውስብስብ ቃላትን ተጠቅማችሁ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ።*

| | | |
|---|---|---|
| ይፈጥርላቸዋል | ተማሪዎቻቸው | አገልግሎታቸውን |
| ይገነዘቡበታል | ኑሯቸውን | ከተከታተልናቸው |
| መልዕክቶችን | እየጨፈጨፉ | ምጣኔ ሀብታዊ |

፩. የአንድ ሀገር-----------እድገት በዘጎች ኑሮ ላይ ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል።

፪. ሰዎች ደኖችን--------------------የአካባቢ መራቆት እንዲፈጠር ያደርጋሉ።

፫. ደብዳቤ ----------------------------ለማስተላለፍ ያገለግላል።

፬. ሰዎች ለሰዎች መልካም ነገሮችን ሲያደርጉ የህሊና እርካታ----------------።

፭. በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን-----------ለማሻሻል ሌት ተቀን በርካታ ስራዎችን ይሰራሉ።

፮. አንድንድ መስሪያ ቤቶች ------------------ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ።

፯. መምህራን ለ--------------ሁልጊዚ አርአያ መሆን አለባቸው።

፰. አረጋውያንን ትኩረት ሰጥተን ካዳመጥናቸው እና-------------ጠቃሚ ምነገሮችን ያስጨብጡናል።

ገፅ 33.

*አስረጅ 9.*

*መልመጃ አንድ፡ የሚከተለትን ስሞች “-ኣት” የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ወደ ብዙ ቁጥር ለውጡ፡፡*

| ተራ ቁጥር | ነጠላ | ብዙ |
|---|---|---|
| ፩. | አመት | |
| ፪. | ዲያቆን | |
| ፫. | ወር | |
| ፬. | ካህን | |
| ፭. | ቃል | |

*አስረጂ 10.*

*መልመጃ ሁለት*

*የሚከተሉትን ምሳለዎች መነሻ በማድረግ ከታች የተደረደሩትን ነጠላ እና ብዙ ቁጥር አመልካች ስሞች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ስሩ፡፡*

ምሳለ፡- ልጅ - ነጠላ

የሁሴን ልጅ በሥነ ምግባር የታነፀ ነው፡፡

ልጆች --- ልጅ-ኦች

የኛ ሰፈር ልጆች በትምህርታቸው ጎበዞች ናቸው፡፡

፩. ሴት

ሴቶች

፪. ላም

ላሞች

፫. ተማሪ

ተማሪ ዎች

፬. መምህር

መምህራን

፭. ዘመን

ዘመናት

(ገጽ፣ 35)

*አስረጅ 11.*

*መልመጃ አራት*

*ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ስጡ።*

፩. ሀብቷ ቀና

ሀ. እድለኛ ሆነች ለ. ታጨች

ሐ. ሀብታም ሆነች መ. ገንዘብ አገኘች

፪. ጥራዛ ነጠቅ

ሀ. ግልብ ለ. ያልተማረ

ሐ. ጥልቅ ትምህርት የሌለው መ. ሁሉም

፫. የአዞ እንባ

ሀ. የለበጣ ሀዘን ለ. እውነተኛ ሀዘን

ሐ. መከፋት መ. ማልቀስ

፬. አይነ ልም

ሀ. ቆንጆ ለ. ምቀኛ

ሐ. ተንኮለኛ　　　　　　　　　　　　　　　　መ. የዋህ

ድ. አገም ጠቀም

ሀ. ሁሉን መጥቀም　　　　　　　　　　　　　　ለ. ያዝ ለቀቅ

ሐ. ዓይንአፋር　　　　　　　　　　　　　　　መ. ሄድ መጣ

(ገጽ፣ 45)

*አስረጅ 12.*

***መልመጃ አንድ፤ በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከዚህ በታች ከቀረቡት መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሀረጋት መካከል በመምረጥ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከዚህ በማያያዝ | በመቀጠል | ከዚህ ቀጥሎ | እስከዚህ |
| ድረስ | በሌላ ጊዜ | ወደፊት | |

፩. ተጋባዡ እንግዳ መጻሕፍት የማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለፃ አደረጉ፤-----ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት በራስ አባባል ማስታወሻ መያዝ ጠቃሚ እንደሆነ ተናገሩ፡፡

፪. እስካሁን ያለው የንባብ ልምዳችን ብዙ የሚያኮራን ላይሆን ይችላል፤--------ግን አስፈሊጊነቱን ስለተረዳን ጠንክረን ልናሻሽለው እንችላለን፡፡

፫. የጤና ባለሙያው የኤች አይ ቪ ኤድስን የመተላለፊያ መንገዶች በሚመለከት ዋነኛ የሆኑትን በዝርዝር አቀረቡ፤-------------በዚህ ጉዳይ ላይም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይተው ገለፃ በመስጠት ንግግራቸውን ጨረሱ፡፡

፬. ሁሉም ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በተሰማራበት ተግባር ለሀገሩ እድገት ማበርከት አለበት፤-----------------የተሰሩት ስራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

፭. አጭር ሌቦለድን በሚመለከት የአላባውያኑን ምንነት ተምረናል፤---------መሸጋገሪ ቃላትን ወይም ሀረጋትን እንማራለን፡፡

(ገጽ፣ 46)

*አስረጂ 13.*

*መልመጃ አንድ*

*በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ኢ-ተዘውታሪ በ "ለ" ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው ጋር ኣዛምዱ።*

| "ሀ" | "ለ" | |
|---|---|---|
| ፩. ለሆሳስ | ሀ. የአበባ ወቅት | |
| ፪. ለበጣ | ለ. ድርስ እርጉዛ | |
| ፫. ሙዋጥ | ሐ. ጌሾ ያልበዛበት ለጋ ጠጅ | |
| ፬. ቆንዳላ | መ. ድምጽ አልባ፣ ሹክሹክታ | |
| ፭. በተሀ | ሠ. አዘጋጅ፣ አሰናዳ | |
| ፮. ወረግቡ | ረ. ሹሩባ | |
| ፯. ከወነ | ሰ. የጆንያ መስፊያ መርፌ | |
| | ሸ. ፌዝ፣ ሹፈት፣ ቀልድ | (ገጽ፣ 47) |

*አስረጂ 14.*

*መልመጃ ሁለት ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ።*

ሀ. መነመነ

ለ. ደለደለ

ሐ. በረከተ

መ. ኮተኮተ

ሠ. ትኩረት

(ገጽ፣ 52)

*አስረጅ 15.*

*መልመጃ አንድ*

*የሚከተሉትን ቃላት እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ በሰንጠረዡ ውስጥ በቀረበው ምሳሌ መሰረት አስቀምጡ፡፡*

| ቃል | እማሬያዊ ፍቺ | ፍካሬያዊ ፍቺ | |
|---|---|---|---|
| ንብ | ማር አምራች በራሪ ፍጡር | ታታሪ፣ ትጉህ፣ ሰራተኛ | |
| ዱባ | | | |
| ቋንጣ | | | |
| አንበሳ | | | |
| ተልባ | | | |
| እንጀራ | | | |

(ገጽ፣ 59)

*አስረጅ 16.*

**ተግባር፤ የሚከተሉትን ቃላት ተጠቅማችሁ ገቢርና ተገብሮ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

፩.ገደለ

ተገደለ

፪. ወደደ

ተወደደ

፫. ለበሰ

ተለበሰ

፬. ቀመሰ

ተቀመሰ

፭. ጠበሰ

ተጠበሰ

፮. ጨረሰ

ተጨረሰ

፯. ፈለገ

ተፈለገ

(ገጽ፣ 60)

*ኣስረጅ 17.*

*መልመጃ ኣንድ*

*በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ኣረፍተ ነገር ሰርታችሁ ኣመልክቱ።*

ምሳሌ፡- እርግብ

እማሬያዊ ፍቺ፡- እርግብ በራሪ የወፍ ዝርያ ናት።

ፍካሬያዊ ፍቺ፡- ቤተልሄም እርግብ ናት።

፩. መሬት

፪. ምስጥ

፫. ጉቶ

፬. እርጥብ

፭. ምልጭ

፮. እሳት

*ኣስረጅ 18.*

*መልመጃ ሁለት*

*ቀጥል የቀረቡትን ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በደብተራችሁ ኣስፍሩና ለመምህራችሁ ኣሳዩ።*

፩. ትንቢት

፪. መባቻ

፫. ማግስት

፬. በለተ

፭. ኣዛውንት

፮. ቀጠሮ

፯. ማነጽ

(ገጽ፣ 70)

*አስረጅ 19.*

***መልመጃ ሁለት***

***በ "ሀ" አምድ ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ"አምዬ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዛምዱ።***

| **"ሀ"** | **"ለ"** | |
|---|---|---|
| ፩. መገናኛ ብዙሃን | ሀ. ዋጋ | |
| ፪. መታነጽ | ለ. መሰደድ፣ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ | |
| ፫. ክስተት | ሐ. ተጫዋች | |
| ፬. እሴት | መ. አዲስ ነገር | |
| ፭. ሞግዚት | ሠ. መልእክት ማሰራጫ | |
| ፮. መፍለስ | ረ. ተንከባካቢ | |
| ፯. ተዋናይ | ሰ. መቀረጽ፣ መገንባት | (ገጽ፣ 75) |

*አስረጂ20.*

***መልመጃ ሁለት***

***በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺየሚሆኑትን ምረጡ።***

፩. የትምህርት ቤቱን ደጃፍ ከረገጠች ድፍን ሁለት አመት ሊሆናት ነው።

ሀ. ሰፈር ለ. በራፍ ሐ አደባባይ መ. ክፍል

፪. ስለትምህርቷ ሲነሳ ደስተኛ እንዳልሆነች የሚሸሽኝ አይኗ ያሳብቃል።

ሀ. ይናገራል ለ.ይደብቃል ሐ. ይስቃል መ. ይለምናል

፫. እንደጋራ ፊቷ የተቆለለ ስራ ካላለቀ የቁጣ መአት ይወርድባታል።

ሀ. የተሰበሰበው ለ. የተበተነው ሐ. የተከመረው መ. ሀናሐ

፬. የሌጅነት ፊቷ እየተመጠጠ መሆኑን ሰውነቷ ይጠቁማል፡፡

ሀ. እያማረበት ለ. እየፈካ ሐ.ወዙ እየጠፋ መ. እየደረቀ

፭. ከሰውነት ጎዳና የወጣው ፊቷ የመወየብ ምልክት ቢታይበትም ጠይምና መልከመልካም ናት፡፡

ሀ. የመቅላት ለ. የመዋብ ሐ. የመገርጣት መ. የመክሳት

፮. የዕለት ከዕለት ህይወቷ ቤተሰቡን መንከባከብ እንደሆነ በዛለው ድምጿ ነገረችኝ፡፡

ሀ. በደከመ ለ. በበረታ ሐ. ባማረ መ. በቀጠነ

፯. በርካታ የቤና እኩዮች ከተማን እንዱናፍቁ አስገድቸዋሌ፡፡

ሀ. ባልደረቦች ለ. ቤተሰቦች ሐ. ዘመዶች መ. መሰሎች

፰. ልጅን ከተማ ያለ ዘመድ ጋር ልኮ ማስተማር የተለመደ ነው፡፡

ሀ. አስገብቶ ለ. ሰዶ ሐ. አስተላልፎ መ. አምጥቶ

፱. የሚደርስባትን የቁጣ ውርጅብኝ ሸሽት ያለ እረፍት ስትባትል ትውላለች፡፡

ሀ. ስትለፋ ለ. ስትሰራ ሐ. ስትደክም መ. ሁለም

፲. ጻሀይ ገና በለጋነቷ አምስት አባላት ያለውን ቤተሰብ ስራ ተሸከመች፡፡

ሀ. በህፃንነቷ ለ በወጣትነቷ ሐ. በጮርቃነቷ መ. በቀንበጥነቷ

(ገጽ፣ 79]

**አስረጅ 21.**

***መልመጃ ሶስት***

**በምንባቡ ውስጥ ያሉ ፈሉጣዊ አነጋገሮችን በማውጣት ትርጉማቸውን ጻፉ፡፡ (ገጽ፣ 79]**

**አስረጅ 22.**

***መልመጃ አራት***

***በ "ሀ" አምድ ስር ላለ ፈሉጣዊ  አነጋገሮች በ "ለ" አምድ ስር ካሉት ፍችዎቻቸው ጋር አዙምደ፡፡***

| "ሀ" | "ለ" | |
|---|---|---|
| ፩. ቃለን ሰጠ | ሀ. ሊቅ፣ አዋቂ፣ ተመራማሪ | |
| ፪. ቀንበር ሰበረ | ለ. የሰሚ ሰሚ፣ ጭምጭምታ | |
| ፫. ነጭ ለባሽ | ሐ. ሀጢያት | |
| ፬. የቀለም ቀንድ | መ. ስማኝ፣ አድምጠኝ | |
| ፭. የወሬ ወሬ | ሠ. መሰከረ | |
| ፮. ደዌ ነፍስ | ረ. ህግ ተላለፈ | |
| ፯. ውሃ መውቀጥ | ሰ. የመንግስት ሰላይ | |
| ፰. ድንጋይ ኳሱ | ቀ.  አስተዋይ፣ ቁምነገረኛ | |
| ፲. ጆሮ ስጠኝ | በ. ደፋር፣ ለምንም ነገር የማይበገር | |
| | ተ. ፈሪ፣ እርብትብት | |
| | ቸ. የቀለም መበጥበጫ | (ገጽ፣ 80) |

***አስረጅ 23.***

***መልመጃ አንድ***

***ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልሱ፡፡***

፩. ጉዳት

ሀ. ህመም		ለ. መከፋት		ሐ.ጥቅም		መ. ችግር

፪. የግል

ሀ. የጋራ		ለ. የሰው		ሐ. የአንድ		መ. የነጠላ

፫. ጥፋት

ሀ. ክፋት ለ. ልማት ሐ. እድገት መ.ሀብት

፬. እኩይ

ሀ. ሰናይ ለ. መጥፎ ሐ. አስቸጋሪ መ. ሀይለኛ

፭. ቅንነት

ሀ. መልካምነት ለ. ጥሩ ሐ.ሰናይ መ. ክፋት

፮. ሙቅ

ሀ. ለሰስ ያለ ለ. ቀዛቃዛ ሐ. የሚያቃጥል መ. የማይታኝክ

፯. ህቡ

ሀ. ድብቅ ለ. ስውር ሐ. ሚስጥራዊ መ. ግልጽ

፰. ሁከት

ሀ. ሰላም ለ. ብጥብጥ ሐ. ነውጥ መ. ሽብር

፱. ቧልት

ሀ. ፌዝ ለ. ቀልድ ሐ. ቁምነገር መ.ተረብ

፲. ኢምንት

ሀ. ቅንጣት ለ. ትንሽ ሐ. ጥቂት መ. ብዙ

*አስረጅ 24*

***መልመጃ ሁለት:***

***ከታች በአረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒ ፍቺየሚሆኑትን ከሰንጠረዡ እየመረጣችሁ ተኩ።***

| | | |
|---|---|---|
| ተጎጂ | ንፉግ | ያፋጥናሉ |
| መቀራረብ | መጥፎ | ሕይወት |
| ምድረ በዳ | ወረዙ | ጥብቅ |

፩. የኤሌሳቤጥ አባት ለጋስ ናቸው።

፪. በዝናብ እጥረት የተነሳ መሬቱ ደረቀ።

፫. የነሙስጠፋ መንደር ነዋሪዎች የመስኖ ተጠቃሚ ናቸው።

፬. ልማዲዊ እና ጎጂ ድርጊቶች የአንድን ሀገር እድገት ያጓትታሉ።

፭. የእንጦጦ ጫካ ወደ መዝናኛነት ተቀይሯል።

፮. የቤተሰብ መራራቅ ለህፃናት ስነ ልቦና ጉዳት አለው።

፯. የክፍላችን አለቃ ፀባየ ሰናይ ነው።

፰. የሁለቱ አረፍተ ነገሮች ቁርኝት ልል ነው።

(ገጽ፣ 82]

**አስረጅ 25.**

**መልመጃ ሶስት፡-**

**ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል ልዩ የሆነውን ምረጡ።**

፩. ሀ. ተልባ ለ. ሱፍ ሐ. ኑግ መ. ሽንብራ

፪. ሀ. ክራር ለ. ዋሽንት ሐ. በገና መ. ማሲንቆ

፫. ሀ. ደቦል ለ. ሙጭሊት ሐ. ውርንጭሊ መ. ቡችላ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፬. | ሀ. ጀበና | ለ. ድስት | ሐ. ቅል | መ. እንስራ |
| ፭. | ሀ. ጎመን | ለ. ሰሊጥ | ሐ. ማንጎ | መ. ቆስጣ |
| ፮. | ሀ. ጋቢ | ለ. ፎጣ | ሐ. ነጠላ | መ. ኩታ |
| ፯. | ሀ. ሞፈር | ለ. ቀንበር | ሐ. ድግር | መ. መንሽ |
| ፰. | ሀ. ጤፍ | ለ. ዘንጋዳ | ሐ. ማሽላ | መ. በቆሎ |
| ፱. | ሀ. ባዝራ | ለ. ቂብ | ሐ. ጊደር | መ. ኮረዳ |
| ፲. | ሀ. ሒስ | ለ. ትችት | ሐ. ነቀፋ | መ. ዘለፋ |

(ገጽ፣ 83]

*አስረጅ 26.*

*መልመጃ አንድ*

*በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡*

፩. ሄኖክ ለእናት ሀገር ጥሪ ወደ ድንበር ገሰገሰ፡፡

፪. እሱባለው ብእሩን አልሰጥም አለ፡፡

፫. ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሙሊት በሰሊም መጠናቀቁን አስመልክታ ለአለም ሀገራት ደስታዋን አበሰረች፡፡

፬. ለሁለም ነገር የሚሻለው በህብረት መቆም ነው፡፡

፭. ስነቃል በባህርዩ ተለዋዋጭ ነው፡፡

፮. በስርአት የሚሰደሩ ዴምፆች ስብስብ ቃል ይባላል፡፡

አስረጅ 27.

*መልመጃ ሁለት*

*የሚከተሉትን ቃላት አውዲዊ ፍቺ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ስሩ።*

| | |
|---|---|
| ፩. ባህል | ፮. ፋይዳ |
| ፪. ጠላት | ፯. ሀሴት |
| ፫. ንዋይ | ፰. ሙስና |
| ፬. አሸን | ፱. ዋና |
| ፭. አዛውንት | ፲. አባይ |

*አስረጅ 28.*

*መልመጃ ሶስት*

*የሚከተሉትን ቃላት መዛገበ ቃላት ተጠቅማችሁ ፍቺቻውን ስጡ።*

| | |
|---|---|
| ፩. ተደራሲ | ፮. ህፀጽ |
| ፪. ታዳሚ | ፯. ምንዳ |
| ፫. አብነት | ፰. አልፋ |
| ፬. ፋና | ፱.ኩታገጠም |
| ፲. አደብ | |

(ገጽ፣ 97]

*አስረጅ 29.*

*መልመጃ ሁለት*

*ለሚከተለት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ።*

ሀ. በከለ ለ. ሸፈነ ሐ. መሸሸት መ. ጠንቅ ሠ. ዝቃጭ

(ገጽ፣ 102]

*አስረጅ 30.*

*መልመጃ አንድ*

***ከዘህ በታች በሰንጠረዥ የቀረቡትን ቃላት አውዲዊ ፍቻቸውን መሰረት አድርጋችሁ በባዶ ቦታው ውስጥ በማስገባት አረፍተነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዳጎስ | ወላፈን | ሳንካ | ሀገረ ሰብአዊ |
| መሻሻል | አዘቦት | ቤተ ምርምር | ማእረግ |

፩. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከበሩ------------------ ክብረ በአላት መካከል የዳውሮ ህዝብ የዘመን መለወጫ “ቶክ በኣ” አንዱ ነው፡፡

፪. የእሳቱ--------------- ዳር ያሉትን ሰዎች ሁሉ ገረፋቸው፡፡

፫. የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ባለፈው አመት ላስመዘገቡት አመርቂ ውጤት ------------ ያለ ሽልማት ተበረከተላቸው፡፡

፬. የአንዲት ሀገር ማሕበራዊ ኑሮ-------------የሚችለው ሕዝቡ በትምህርት የታነጸ ከሆነ ነው፡፡

፭. ኮቪዶ 19 (ኮሮና ቫይረስ) ለሀገራችን እድገት -------------- ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡

፮. በሣይንስና ቴክኖልጂ ጥበብ የበለጸጉት ሀገሮች አሁን ከደረሱበት የእድገት ደረጃ ላይ ሊደርሱ የቻሉት የ------------------ ጥናታቸውን በማጠናከራቸው ነው፡፡

፯. ዘምዘም በበአላት ቀን ይቅርና ለ-----------------ቀን የምታዘጋጀው ምግብ ጣት ያስቆረጥማል፡፡

፰. ወንጀለኞችን በቁጥጥር ስር ያዋለው ፖሊስ የ-------------እድገት አገኘ፡፡

(ገጽ፣ **111]**

አስረጅ 31

**መልመጃ ሶስት**

**በ"ሀ" ስር የቀረቡትን ያሌተለመዱ ቃላት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ፩. ሞግዚት | ሀ. መንቀጥቀጥ |
| ፪. ገርበብ | ለ. መከልከል |
| ፫. ስርቅታ | ሐ. መባከን |
| ፬. ማሞናደል | መ. ማቃጠል |
| ፭. መክላት | ሠ. ተንከባካቢ |
| ፮. ቅራተኛ | ረ. ከፊት |
| ፯. መዋተት | ሰ. ከብት ጠባቂ |
| ፰ መፋጀት | ሸ. ማቀማጠል |
| | ቀ.ሀቅታ |
| | በ. ማስወገድ |

(ገጽ፣ 112]

*አስረጅ 32.*

***መልመጃ አንድ***

***ከዘህ በታች በሰንጠረዥ ከቀረቡት አያያዥ ቃላት መካከል ተገቢ የሆኑትን በመምረጥ ከታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡***

| | | |
|---|---|---|
| እንዲሁ | ግን | አለበለዚያ |
| ስለሆነ | ነገር ግን | ወይም |
| ስለ | ቢሆንም | ይሁንእንጂ |

፩. ያሬድ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ----------------------- ማጥናት አይወድም፡፡

፪. ጀማል ይመጣ-----------------------------አላወኩም፡፡

፫. ልጁ ታማኝ-------------------------------አምነዋለሁ፡፡

፬. ሀምዛ ብዙ አጥንቶ ነበር፤------------------ፈተናውን አላለፈም፡፡

፫. የገና ጨዋታ ማየት ደስ ይለኛል፤ መጫወት-------------------------አልችልም።

፯. ማንበብ አለብህ------------------------ፈተናውን ልትወድቅ ትችላለህ።

፯. መጽሐፉን መግዛት--------------------ከቤተመጽሐፍት መዋስ ትችላለህ።

፰. ውጭው በጣም ---------ሚቀዘቅዝ ጃኬት አመጣሁልህ።

(ገጽ፣ 127]

*አስረጂ 33.*

*መልመጃ አንድ*

*በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ፃፉ።*

1. የሰማይ ስባሪ የሚያክል ዳቦሰጠኝ።

2. አጫውተኝ እንጂ ተራራው!

3. ህይወት ያለው በድን

4. ብዕር አለቀሰ።

5. እጁ በረዶ ሆነ።

6. ሄለን እብድ ይመስል ጨርቋን ጣለች።

ገፅ(126)

## አባሪ ሁለት

### አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስምንተኛ ክፍል አንደኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት

**ምዕራፍ አንድ፡ የሥራ ሥነ- ምግባር (9) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በአትኩረት አድምጠው ይመልሳሉ፡፡
- የሥራ ስነ- ምግባርን ጽንሰ ሀሳብ ይገልጻሉ ፡፡
- አዳዲስ ሀሳቦችን አካተው ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- የስራ ስነ ምግባር አመላካች ነገሮችን ይገልጻሉ፡፡
- የመጀመሪያ ቋንቋን ትክክለኛ የሰዋሰው አወቃቀር ይጠቀማሉ ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃመሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ በጥሞና አዳምጠው በተነገረበት አውድ መሰረት ይመልሳሉ<br>➢ ቋንቋን በተለያ ሁነቶች ውስጥ ይጠቀማሉ<br>➢ አጠቃላይ ጭብጡን ለመረዳት በለሆሳስ ያነባሉ<br>➢ አዲስ ሀሳብ አካተው ጽሁፍ ይጽፋሉ<br>➢ ተዘውታሪ ቃላትን በተለያ አውዶች ይጠቀማሉ<br>➢ የቋንቋውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው ድርሰት ይጽፋሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡-ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>ለምሳሌ ፡- **የስራ ስነ- ምግባር ምንድነው ?**<br>**የማዳመጥ ጊዜ፡-**መምህሩ የሚያነብላቸውን አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ፡- ጠንካራ የስራ ባህል<br>**ድህረ ማዳመጥ** ባዳመጡት መሰረት ትክክለኛ መልስ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡<br>በተለያዩ አውዶች ውስጥ ቋንቋውን በመጠቀም እንዲወያዩ ማድረግ ( የስራ ስነምግባር፣ ጠንካራ የስራ ባህል)<br>**ቅድመ ንባብ፡-** ተማሪዎችን ስለርዕሱ መጠየቅ<br>ለምሳሌ፡-ስለስራ ስነ-ምግባር ምን ታውቃላችሁ ?<br>**በንባብ ጊዜ፡-** አጠቃላይ ጭብጡን ለማግኘት ይቻል ዘንድ በለሆሳስ እንዲያነቡ በማድረግ ፤ የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ የጠበቀ ጥያቄ በመሀል ላይ መጠየቅ ፡፡<br>**ድህረንባብ፡-** በምንባቡ አጠቃላይ ሀሳብ መሰረት የተሰጣቸውን ጥያቄ እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡<br>የስራ ስነ- ምግበርን በተመለከተ የራሳቸውን ሀሳብ ጨምረው እንዲጽፉ ማደርግ፡፡<br>ተዘውታሪ ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>የቋንቋውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ ለምሳሌ ጠንካራ ሰራተኝነት ምንድነው?<br>➢ ስልጠንካራ ሰራተኛ ምንነት ነጥብ በነጥብ መጠየቅ<br>➢ የሞያ ስነ- ምግባርን በተመለከተ አጠቃላይ ሀሳብን የያዘ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br><br>➢ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ተዘውታሪ ቃላትን በተለያዩ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ |

**ምዕራፍ ሁለት ባህላዊ ቅርስ (12 ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፡-**

- የሌሎችን ሀሳብ በአትኩሮት ያዳምጣሉ፡፡
- ከምንባቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- የባህላዊ ቅረስን ምነነት ያብራራሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ በበጥሞና የሌሎችን ሀሳብ እያዳመቱ ይመልሳሉ<br>➢ የተለያዩ ውስብስብ ሁነቶችን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ይተርካሉ<br>➢ ስዕሉን አንብበው መልዕክቱን በተመለከተ ዘገባ ያቀርባሉ<br>➢ በ3 አንቀጽ አከራካሪ ድርሰት ይጽፋሉ<br>➢ አዳዲስ ቃላትን በተለያዩ አውድ ውስጥ ይጠቀማሉ | • ማዳመጥ<br>• መናገር<br>• ማንበብ<br>• መጻፍ<br>• ቃላት<br>• ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>**ለምሳሌ ባህላዊ ቅረስ ምንድነው ?**<br>የማዳመጥ ጊዜ፡-<br>መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ በጥሞና አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ፡ የሶፉመር ዋሻ<br>**ድህረ ማዳመጥ** የሌሎችን ሀሳብ በአትኩሮት አዳምጠው እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡<br>ውስብስብ ሁነቶችን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዲተርኩ ማድረግ ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ** ተማሪዎችን ስለርዕሱ መጠየቅ<br>ለምሳሌ ስለባህላዊ ቅርስ ምን ታውቃላችሁ ?<br>**በንባብ ጊዜ፡- በምንባብ ውስጥ ያለውን** የስዕል ሀሳብ ላይ መልመጃዎችን በማዘጋጀት እንዲሰሩ ማድረግ፤<br>የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ የጠበቀ ጥያቄ በመሀል ላይ መጠየቅ ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** ስዕሉን በተመለከተ አንብበው ስለምን እንደሚያነሳ መጠየቅ ( ስዕል ያስፈልጋል ) ፡፡<br>በሶስት አንቀጽ አከራካሪ ድርሰት እንዲጽፉ ማድረግ<br>አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አውድ ውስጥ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>የቋንውን ተገቢ መዋቅር ጠብቀው እንዲጽፉ ማድረግ፡፡ | ➢ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ ባላዊ ቅረስ ምን ማለት ነው ?<br>➢ስለአንድ ባህላዊ ቅረስ እነዲተርኩ ማድረግ<br>➢ስልቀረበላቸው የባህላዊ ቅርስ ስዕል ማጠቃለያ እንዲሰጡ ማድረግ<br>➢ስለ ባህላዊ ቅርስ አከራካሪ ድርሰት እንዲጽፉማድረግ<br>➢አዳዲስ ቃላትን በተለያ አውድ ውስጥ እንዴት እንደሚጠቀሙመጠየቅ<br>➢ከዓ.ነገር ውስጥ የአሁን ጊዜን እንዲለዩ ማድረግ |

**ምዕራፍ ሶስት፡- ሰባዊ እሴቶች (12) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት፡-**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው ጽሁፍን ይመዝናሉ፡፡
- ስለሰዎችን ማክበር ምንነት ያብራራሉ ፡፡
- ከሌሎች ጋር ምልልስ ያደርጋሉ ፡፡
- የሰባዊ እሴቶች አላባውያንን ይዘረዝራሉ ፡፡
- ባለአራት አንቀጽ ጽሁፍን ይመዝናሉ፡፡

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው መልዕክቱን ይመዝናሉ ፡፡<br>➢ ከሌሎች ጋር ምልልስ ያደርጋሉ<br>➢ የጽሁፉን ሀሳብ ከራሳቸው ጋር ያዋህዳሉ<br>➢ ከጽሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላት ያወጣሉ<br>➢ አራት አንቀጽ ያለው አመዛዛኝጽሁፍ ይጽፋሉ<br>➢ ተዘውታሪ ቃላትን ተጠቅመው ሀሳባቸውን ይገልጻሉ<br>➢ ነጠላ እና ብዙ ቁጥርን በትክክል ይጠቀማሉ፡፡ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>**ለምሳሌ፡-** ሰባዊ እሴት ማለት ምን ማለት ነው ?<br>**የማዳመጥ ጊዜ** ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ፡- አክብሮት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-** የማዳመጥ ተግባርን እያከናወኑ የሚያዳምጡትን ፅሁፍ እንዲገመግሙ ማድረግ፡፡<br>ከሌሎች ሰዎች ጋር ስለሰባዊ እሴቶች ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ** ተማሪዎችን ስለርዕሱ በመጠየቅ አንዲገምቱ ማድረግ<br>**የንባብ ጊዜ** ጸሁፉን መረዳት ይችሉ ዘንድ እንዲያነቡ ማድረግ በመሃል ጥያቄ መጠየቅ<br>**ድህረ ንባብ** ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ተረድተው እንዲመልሱ ማድረግ ( የቃላት ሰንጠረዥ ያስፈልጋል )<br>ሰባዊ እሴትን በተመለከተ ባለ አራት አንቀጽ ፅሁፍ ይጽፋሉ፡፡<br>ሀሳባቸውን ለመግለጽ ውስብስብ ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>ነጠላ እና ብዙ ቁጥር ቃላትን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>○ ለምሳሌ ሰባዊ እሴት ምን ማለት ነው ?<br>➢ ሰውን ማበር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>➢ ከጽሁፍ ውስጥ አዳዲስ ቃላትን እንዲያወጡ ማድረግ<br>➢ ቢያንስ ሶስት ሰውን ማክበሪያ ዘዴዎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>➢ የብዙቁጥር ቅርጾችን እንዲለዩ ማድረግ<br>○ እንዳለባቸው ጽሁፍ እነዲጽፉ ማድረግ<br>➢ |

**ምዕራፍ አራት ፡ አጭር ልብ-ወለድ (12) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪክ ይናገራሉ ፡፡
- ስለአጭር ታሪክ ምንነት ይገልጻሉ ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡
- የአጭር ልቦለድን አላባውያነ ይዘረዝራሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ተመሳሳይ ታሪክ ይናገራሉ ፡፡<br>➢ እርስ በእረስ መመሪያ ይሰጣጣሉ<br>➢ አንብበው ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ይለያሉ<br>➢ በጽሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ<br>➢ ያልተለመዱ ቃላትን ለተለያ አላማ ይጠቀማሉ<br>➢ ሀረጎችን በዓ. ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ታሪክ በመንገር የቀደመ እውቀታቸውን መቀስቀስ ፡፡<br>**በማዳመጥጊዜ**፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ አጭር ጽሁፍ<br>**ድህረ ማዳመጥ፡ -የማዳመጥ ተግባሩን ካከናወኑ በኋላ** ተመሳሳይ ታሪኮችን እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>አንድኛቸው ለሌላኛቸው መመሪያ እንዲሰጣጡ ማድረግ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ፡-** ስለ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ምንነት ተማሪዎችን መጠየቅ፡፡<br>**በንባብ ጊዜ፡- ተማሪዎች ከምንባብ ውስጥ** አዳዲስ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲለዩ ማድረግ ፤ የተማሪዎችን የአቅም ደረጃ የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** አዳዲስ ፈሊጣዊ አንጋገሮችን ከምንባቡ ውስጥ እያወጡ ፈቺ አንዲሰጡ ማድረግ፡፡ ( መዘገበ ቃላት ያስፈልጋል )<br>በጽሁፍ ውስጥ መሸጋገሪያ ቃላትን መጠቀም ፡፡<br>ያልተለመዱ ቃላትን ለተለያዩ አላማ መጠቀም፡፡<br>ሀረግን ተጠቅሞ ዓ. ነገር መመስረት ፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ለምሳሌ የአጭር ልቦለድ ክፍሎች ምንድናቸው?<br>➢ የአጭር ልቦለድ አላባውያንን እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ አዳዲስ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን እንዲለዩ ማድረግ<br>➢ የሽግግር ቃላትን እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ያልተለመዱ ቃላትን ለተለያየ አላማ እንዲጠቀሙ ማድረግ<br>➢ ሀረግን ተጠቅመው ዓ .ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ |

**ምዕራፍ አምስት፡የህዝብ ብዛት (9) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-**

- በአትኩሮት አዳምጠው ጽሁፍን ይገልጻሉ፡፡
- ስለህዝብ ብዛት ምንነት ይገልጻሉ ፡፡
- ተራኪ ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- የህዝብ ብዛት በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን ተጸዕኖ ይተነትናሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-<br>➢ በጥሞና አዳምጠው ጽሁፍን ይመዝናሉ ፡፡<br>➢ ውስብስብ መረጃዎችን ይጠይቃሉ<br>➢ በጥልቀት አንብበው ምክንያት እና ውጤት ትስስሮችን ይገልጻሉ<br>➢ ተራኪ ጽሁፍ ጽፈው ይመዝናሉ<br>➢ ሀሳባቸውን የቃላትን እማሪያዊ ፍቺ ተጠቅመው ይገልጻሉ<br>➢ ገቢርና ተገብሮ ዓ. ነገሮችን ይጠቀማሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>ምሳሌ:-የህዝብ ብዛት ማለት ምን ማለት ነው ?<br>**የማዳመጥ ጊዜ** ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ፡- የውልደት ምጣኔ<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን ጽሁፍ መልዕክት የመመዘን ተግባር እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡<br>ስለ ህዝብ ብዛት እና ጥልቀት ስላላቸው መረጃዎች እንዲወያዩ ማድረግ ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ፡-** አዲስ ሀሳብ እንዲፈጥሩ ማድረግ<br>**ምሳሌ፡- የምክንያት እና የውጤት ግኙነት**<br>**የንባብ ጊዜ፡-** ከጽሁፍ ውስጥ በምክንያት እና ውጤት የተሳሰሩ ጽሁፎችን ማውጣትየተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥን ጥያቄ በመሀል መጠየቅ፡፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው የምክንያት እና ውጤት ግንኙነትን እየተመለከቱ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ማድረግ ( ስዕል ያስፈልጋል )<br>ተራኪ ጽሁፍ እንዲለማመዱ እና እንዲመዝኑ ማድረግ፡፡<br>እማሬያዊ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>ገቢርና ተገብሮ ሀሳቦችን ተጠቅመው ዓ. ነገር እንዲፅፉ ማድረግ፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>○ ለምሳሌ የውልደት ምጣኔ ምንድ ነው ?<br>➢ ከሌላ ሰዎች የተገኙ የተወሳሰቡ መረጃዎችን መጠየቅ<br>➢ የምክንያት እና ውጤት ግንኙነትን አንዲለዩ ማድረግ<br>➢ ተራኪ ድርሰት አንዲጽፉ እና እንዲለማመዱ ማድረግ<br>➢ እማሪያዊ ፍቺዎችን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ ገቢርና ተገብሮ ሀሳቦችን እንዲለዩ ማድረግ |

**አባሪ ሶስት**

**አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ)ስምንተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቅ አመት መርኃ ትምህርት**

**ምዕራፍ ስድስት፡ በረሃማነት** (9) **ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-**

- አዳምጠው ጽሁፍን በመተንትን ይገመግማሉ፡፡
- የበረሃማነት ምንነትን ይገልጻሉ ፡፡
- በትክክል አንብበው ጽኁፉን በአጭሩ ያቀርባሉ፡፡
- በረሃማነት እና የዐየር ንብረት ለውጥ የሚያሣድረውን ተጽዕኖ ይተነትናሉ ፡፡

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው እየተነተኑ ይመዝናሉ ፡፡<br>➢ የተሰጣቸውን ርዕስ መሰረት አድርገው በራሳቸው በመተማመን ይናገራሉ<br>➢ የተሰጣቸውን ጽሁፍ በትክክል በማንበብ ማጠቃላያ ይሰጣሉ<br>➢ የገላጭ ጽሁፍን መዋቅር ይመዝናሉ<br>➢ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ፍካሬያዊ ፍቺ ይጠቀማሉ<br>➢ ተግባር ተኮር ዓ. ነገር ይጽፋሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ፡- በረሃማነት ምንድነው ?<br>**በማዳመጥ ጊዜ ፡-** መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ የአፈር መሸርሸር<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን ጽሁፍ መልዕክት የመመዘን ተግባር እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡<br>• የበረሃማነትን ምንነት በተመለከተ ተወያይተው በራስ በመተማመን እንዲናገሩ ማድረግ ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ፡-** የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት<br>**ምሳሌ** ስለበረሃነት ምን ታውቃላችሁ<br>**በንባብ ጊዜ፡- ማንባቡን** በትክክል እንዲያነቡ በማድረግ የጽሁፉን መልዕክት ማጠቃለያ እንዲያቀርቡ ማድረግ፤<br>ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው በማጠቃላያ ሀሳቦች ላይ የተነሱ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡<br>( ስዕል ያስፈልጋል )<br>የገላጭ ጽሁፍን መዋቅር መመዘንን እንዲለማመዱ ማድረግ ፡፡<br>እማሬያዊ ቃላትን ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ፡፡<br>ተግባር ተኮር ዓ. ነገር እንዲመስርቱ ማድረግ | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ለምሳሌ የአፈር መሸርሸር ምክንያት ምንድነው ?<br>➢ የበረሃማነት ወጤቶች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ<br>➢ ስለበረሃማነት የማጠቃለያ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ስለውልደት አንዳንድ ነጥቦች እንዲያነሱ ማድረግ<br>➢ የቃላትን ፍካሬያዊ ፍቺዎች ተጠቅመው ስሜታቸውን እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ ተግባር ተኮር ዓ. ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ |

**ምዕራፍ ሰባት፡ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ(9) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- መረጃ ሰጭ ጽሁፍን በጥልቀት አዳምጠው ጽሁፍን ተግባራዊ ያድርጋሉ ።
- የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት እና ሚያስከትለውን ውጤት ይገልጻሉ ።
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ።
- የዓ. ነገሮችን ተግባር እያወዳደሩ ያነጻጽራሉ ።

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ መረጃ ሰጪ ጽሁፉን አንብበው ተግባራዊ ያደርጋሉ ።<br>➢ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ይስማማሉ<br>➢ ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን አንብበው ይጠቀማሉ<br>➢ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የክፍል ደረጃውን ያማከለ ጽሁፍ ይጽፋሉ<br>• ለቃላት ተቃራኒ ፍቺይሰጣሉ<br>• ተግባር ዓ. ነገሮችን እያወዳደሩ ያነጻጽራሉ | ➢ማዳመጥ<br>➢መናገር<br>➢ማንበብ<br>➢መጻፍ<br>➢ቃላት<br>➢ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>**ምሳሌ** ፡- የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንድነው ?<br>በማዳመጥ ጊዜ ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳምጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>**ለምሳሌ፡-** የህጻናት መብት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-** ከአዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲተቹ ማድረግ ።<br>ስለህጻናት መብት ተወያይተው ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>**ቅድመ ንባብ፡-** የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት፡፡<br>**ምሳሌ፡-**ስለህጻናትጉልበት ብዝበዛ ምንታውቃላችሁ?<br>**የንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎችን በማህል በማህል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** ያልተለመዱ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ከምንባቡ ውስጥ በመፈለግ እንዲገልጹ ማድረግ ። (የቃላት ሰንጠረዥ እና ስዕል ያስፈልጋል )<br>የክፍል ደረጃውን ያማከለ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>ቃላትን ከተቃራኒያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግየ ዓ. ነገርሮችን እንዲያወዳድሩ እና እንዲያነጻጽሩ ማድረግ፡፡ | ➢ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ለምሳሌ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንድነው ?<br>➢ስለ ህጻናት መብት እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ፈሊጣዊ አገላለጾችን እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ስለኅጻናት መብት እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢የቃላትን ተቃራኒ እንዲያዛምዱ ማድረግ<br>➢የ ዓ. ነገሮችን ተግባር እንዲገልጹ ማድረግ |

**ምዕራፍ ስምንት፡ ሰላም (9) ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-**

- ጽሁፍን አንብበው ይተነትናሉ፡፡
- የሰላምን አስፈላጊነት ይገልጻሉ ፡፡
- የጽሁፉን ዋና ሀሳብ ያጠቃልላሉ፡፡
- በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ስርዐተ ነጥቦችን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ጽሁፉን ይተነትናሉ ፡፡<br>➢ ሀሳቡን እነደገና በማዋቀር ለአድማጮች ግልጽ እንዲሆንላቸው ያደርጋሉ<br>➢ አንብበው የጽሁፉን ዋና መልዕክት በማጠቃለል ያቀርባሉ<br>➢ በጽሁፍ ውስጥ ተገቢውን ስርዐተ ነጥብ ይጠቀማሉ<br>➢ ለተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ውስብስብ ዓ. ነገሮችን ይመሰርታሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>**ምሳሌ ፡-** ሰላም ምንድን ነው ?<br>**በማዳመጥ ጊዜ** ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ ፡- የሰላም መኖር ለእድግት ያለው አስተዋጽኦ<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-** የአዳመጡትን ጽሁፍ ተገንዝበው ከውስጥ የወጡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡ ያዳመጡትን የጽሁፉን ሀሳብ ግልፅ በሆነ መንገድ እንደገና እንዲያዋቅሩ ማድረግ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ** የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት ፡፡<br>**ምሳሌ ፡-** ስለሰላም ምን ታውቃላችሁ<br>**ንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-**የምንባቡን ዋና ሀሳብ በማጠቃለል እንዲያነቡ ማድረግ፡፡ ( የስረዐተ ነጥብ ሰንጠረዥ ያስፈልጋል )<br>የሥረዓተ ነጥብ ምልክቶችን በፅኁፍ ውስጥ በትክክለኛው ቦታ በማስገባት እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡<br>ውስብስብ ዓ. ነገሮችን እንዲመሰርቱ ማድረግ፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ለምሳሌ የሰላም መኖር ለእድገት ያለው አስተዋጽያ ምንድነው ?<br>➢ የሠላምን ምንነት እንዲገልጹ ማድረግ<br>➢ ስለሰላም የማጠቃለያ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ስለሰላም ጥቂት ነጥቦች እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ የተለመዱ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንዲያብራሩ ማድረግ<br>➢ የውስብስብ ዓ. ነገሮችን የተለያዩ ክፍሎች እንዲለዩ ማድረግ |

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡ የአየር ንብረት** (9) **(ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የጽሁፍን ሀሳብ አዳምጠው ይገመግማሉ፡፡
- ስለ አየር ንብረት ምንነት ያብራራሉ ፡፡
- ለተለያየ አላማ ያነባሉ፡፡
- የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ውጤት ያብራራሉ፡፡

| ብቃት | ይዘት | የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ አዳምጠው ጽሁፉን ይመዝናሉ ፡፡<br>➢ በተሰጣቸው ርእስ በክፍል ውስጥ ይስማማሉ<br>➢ ለተለያየ አላማ ያነባሉ<br>➢ ጽሁፉን ተመልክተው ጥልቅ ገለጻ ያካሂዳሉ<br>➢ ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ<br>➢ ድርብ ድብልቅ ዓ. ነገሮችን ይመሰርታሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | • **ቅድመ ማዳመጥ**፡- ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ ፡፡<br>ምሳሌ ፡- የአር ንብረት ምንድነው ?<br>• በማዳመጥ ጊዜ ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ፡- የአየር ንብረት<br>**ድህረ ማዳመጥ** መልዕክቱን የተመለከቱ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግ ፡፡<br>• በተሰጠው ርዕስ ላይ በክፍል ውስጥ ተወያይተው ስምምነት ላይ መድረስ /የአየር ንብረት ለውጥ በሚል ርእስ ይከራከራሉ፡፡<br>**ቅድመ ንባብ፡-** የቀደመ እውቀታቸውን በመጠየቅ ማነቃቃት<br>**ምሳሌ**ስለአየር ንብረት ለውጥ ምን የምታውቁትነገር አለ<br>**የንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው ከምንባብ የወጡ የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ ( ስዕል ያስፈልጋል )<br>ስዕልን ተመልክተው ጥልቅ ትንታኔ እንዲሰጡ ማለማመድ፡፡<br>ላልተለመዱ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት፡፡<br>ውስብስብ ዓ. ነገር እንዲመሰርቱ ማድረግ ፡፡ | ➢ ካዳመጡት ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>➢ ለምሳሌ የአየር ንብረት ለውጥ ምንድነው ?<br>➢ የአየር ንብረትን ለመከላከል መፍትሄው ምን እነደሆነ መጠየቅ<br>➢ ስለአየር ንብረት የማጠቃለያ ጽሁፍ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ከስዕል የተገነዘቡትን ዘርዝረው እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ያልተለመዱ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንዲያብራሩ ማድረግ<br>➢ ውስብስብ ዓ. ነገሮች ምንነት መጠየቅ |

**ምዕራፍ አስር፡ ተውኔት (12) (ክፍለ ጊዜ)**

**የሚጠበቅ ውጤት**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የጽሁፍን ሀሳብ አዳምጠው ይተነትናሉ፡፡
- ስለ ተውኔት ምንነት ትንታኔ ይሠጣሉ ::
- የተውኔት አላባውያንን ይዘረዝራሉ፡፡
- የጽሁፉ ውስጥ የተለያዩ አያያዞችን ይጠቀማሉ፡፡

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የመማር ስልቶችና መርጃ መሳሪያዎች** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-<br>➢ ለጽሁፉ ተንታኔ ይሰጣሉ ::<br>➢ ጽሁፉን ይተርካሉ<br>➢ ጽሁፉን አንብበበው<br>➢ የትወናው አካል ይሆናሉ<br>➢ ተመሳሳይ የተውኔት ጽሁፍ ያዘጋጃሉ<br>➢ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ዘይቤ ይጠቀማሉ<br>➢ በጽሁፍ ውስጥ የተለያዩ አያያዦችን ይጠቀማሉ | ➢ ማዳመጥ<br>➢ መናገር<br>➢ ማንበብ<br>➢ መጻፍ<br>➢ ቃላት<br>➢ ሰዋሰው | **ቅድመ ማዳመጥ፡-** ጥያቄ በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲመልሱ ማድረግ፡፡<br>ምሳሌ ፤ ተውኔት ምንድነው ?<br>በማዳመጥ ጊዜ ፡- መምህሩ የሚያነብላቸውን አጭር ምንባብ አዳመጠው ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡<br>ለምሳሌ፡- አጫጭር ጨውውት<br>**ድህረ ማዳመጥ፡-** ያዳመጡትን ፅሁፍ መልዕክት ከተረዱ በኋላ ከውሱ የወጡ ተግባራትን እንዲሰሩ ማድረግ ::<br>ጽሁፉን እንዲተርኩ ማድረግ<br>**ቅድመ ንባብ** ፡-የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት በጥያቄ መቀስቀስ<br>ተውኔት ምንድነው<br>**የንባብ ጊዜ፡-** በለሆሳስ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡<br>ተማሪዎችን በመሀል በመሀል ደረጃውን የጠበቀ ጥያቄ መጠየቅ፡፡<br>**ድህረ ንባብ፡-** ምንባቡን አንብበው የትወናው አካል እንዲሆኑ ማድረግ፡፡ ( ብዙ የተውኔት ጽሁፎች ያስፈልጋል )<br>ተመሳሳይ የተውኔት ጽሁፎች እንዲያዘጋጁ ማድረግ ::<br>ከጓደኞቻቸው ጋር የተውኔቱን ጽሁፍ እንዲተረጉሙ ማድረግ፡፡<br>ከሌሎች ሰዎች ጋር ሀሳባቸውን ለመግለጽ ዘይቤያዊ አገላለጽ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>የተለያዩ አያያዦችን በጽሁፍ እንዲጠቀሙ ማድረግ :: | ➢ ካዳመጡት ውሰጥ ጥያቄ መጠየቅ<br>ለምሳሌ የተውኔት አይነቶች ምን ምንናቸው ?<br>➢ ጥያቄዎችን እንዲመልስ ማድረግ<br>➢ የተወሰኑ የተውኔት ክፍሎችን እንዲተርኩ ማድረግ<br>➢ የተውኔት አይነቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>➢ የተውኔቱን ጭብጥ እንዲጽፉ ማድረግ<br>➢ ሀሳባቸውን እንዴት በዘይቤ አገላለጽ እንደሚጽፉ መጠየቅ<br>➢ አያያዦችን እንዴት እንደሚጠቀሙ መጠየቅ |

# ማረጋገጫ

‹‹በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በ2015 ዓመተ ምህረት ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት በማንኛውም አካል ያልተሰራና ወጥ የራሴ ሥራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትን በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

አንሻ መሃመድ

________________

መስከረም 2016